ጥያቄ! ጥያቄ! ጥያቄ!
መልስ በጠፋበት ዘመን

መላክ ቢ.

የሰዶማውያኑ የጉብኝት ፕሮግራም በቅድስት አገር ኢትዮጵያ ሊሳካ አይችልም!

"የማይታፈን ጪስ" ሆኖ ብቅ ያለው ኢሳትና፤ ከአነጋጋሪው የቦርዱ ውሳኔ ጀርባ ያሉ እውነታዎች!

ጃፈር ሰዒም

ቀመረ ከዋክብት-
ሐሳበ ጠቢባን ወጠባባት

አሸናፊ ዘ-ደቡብ

የቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባዔና ሰሞነኛ ውሳኔዎች

ሪታ ፓንክረስ፦ ከነቤተሰባቸው ዕድሜያቸውን ለኢትዮጵያ የሰጡ ባለውለታ




መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 59 ሰኔ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99


## የዘውግ ፖለቲካ ምንነት

ፕ/ር መሳይ ከበደ
(ከአሜሪካ በተለይ ለግዮን መጽሔት)



## "ሃይማኖትና ብሔርን መሰረት ያደረጉ፤ ባንኮችን ማበረታት ትልቅ ስሕተት ነው"

"ዲያስፖራው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ እንዲሳተፍ ከፈለገ ..."

"የውጭ ባንኮች ቢመጡ ለሁሉም በር መክፈት ያለብን አይመስለኝም"

አቶ ክቡር ገና

ግዮን

14



“ሃይማኖትና ብሔርን መሰረት ያደረጉ፣ ባንኮችን ማበረታት ትልቅ ስሕተት ነው”

አቶ ክቡር ገና




ቁጥር 58 ዕትም

ግዮን

ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ
ሰኔ 8
ይጠብቁን!

እስር ቤት የተዘጋጀው የአንዳርጋቸው ጽጌ መጽሐፍ ለሕትመት በቃ!

------ 2 -----

የቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባዔና ሰሞነኛ ውሳኔዎች፤
በደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት ኃላፊ ብፁዕ አባ ያዕቆብ ከስራ ታገዱ!

------ 3 -----

የሰዶማውያኑ የጉብኝት ፕሮግራም በቅድስት አገር ኢትዮጵያ ሊሳካ አይችልም!

------ 4 ----

ጥያቄ! ጥያቄ! ጥያቄ!
መልስ በጠፋበት ዘመን

መላክ ቢ.

------ 5 ---

ሰይጣናዊ ተልዕኮ ያነገቡት፤ የግብረ ሰዶማውያኑን ጉብኝት በፅኑ እንቃወማለን!

------ 8 ---

ለዛ

------ 11 ---

የመምህርነት ሙያን ወደ ቀደመ ክብሩ እንዴት እንመልሰው?

ፍቅርተ ተሾመ

------ 12 ---

ቀመረ ከዋክብት- ሐሳበ ጠቢባን ወጠባባት

አሸናፊ ዘ - ደቡብ

------ 13 ---

በእንቁላሉ በቀጣሽኝ

ብሩክ አስቻለው

------ 18 ---

ኢትዮጵያ ዛሬ አርበኛ ትውልድ ትፈልጋለች!

ጥላሁን መሸሻ

------ 19 ---

ኢትዮጵያ የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ምን ግዜም አያስፈልጋትም!

መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

------ 21 ---

ይታፈን ጪስ” ሆኖ ብቅ ያለው ኢሳትና፣ ከአነጋጋሪው የቦርዱ ውሳኔ ጀርባ ያሉ እውነታዎች!

ጃፈር ስዩም

------ 23 ---

ይድረስ ለኢሳት ባልደረቦች፣ በመላው አለም ለምትገኙ የኢሳት ደጋፊዎችና ለነጻ ሚዲያ መኖር የምትታገሉ ዜጎች ሁሉ

ታማኝ በየነ

------ 25 ---

“ኢትዮጵያ ዛሬ ከማንኛውም ጊዜ በላይ፤ እንደ ኢድ ጀምዐ አንድነትን ትፈልጋለች!”

ጠ/ሚ/ ር ዐቢይ አህመድ

------ 26 ---

ሪታ ፓንክረስ፡-ከነቤተሰባቸው ዕድሜያቸውን ለኢትዮጵያ የሰጡ ባለውለታ

------ 28 ---

9



የዘውግ ፖለቲካ ምንነት

ፕ/ር መሳይ ከበደ
(ከአሜሪካ በተለይ ለግዮን መጽሔት)

# እስር ቤት የተዘጋጀው የአንዳርጋቸው ጽጌ መጽሐፍ ለሕትመት በቃ!




በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ስማቸው በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ጥቂት ሰዎች መሀል አንዱ የሆኑት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አዲስ መጽሐፍ ለገበያ ቀርቧል፡፡

"ትውልድ አይደናገር፤ እኛም እንናገር" የተሰኘውና ለአንባቢያን በሚመች መልኩ እንደቀረበ ለዝግጅት ክፍላችን የገለጹትና በአሁኑ ወቅት እንግሊዝ አገር የሚገኙት አቶ አንዳጋቸው ጽጌ "መጽሐፉ ምን ይመስላል? የሚለውን ሁኔታ መስመር ለማስያዝ ከተጠቀምኩት የመንደርደሪያ ቻፕተር ውጭ፤ ሙሉ መጽሐፉን ለማንበብ እንዲቀል፣ ሁሉም ሰው በሚረዳው ዓረፍተ ነገር ለማቅረብ የቻልኩትን ሁሉ አድርጌያለሁ" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የቀድሞ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አመራር አባል የነበሩት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በወያኔ የፀጥታ ኃይሎች የመን ላይ ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ፤ አንድ ዓመት ከሶስት ወር የደህንነት መ/ቤቱ ስውር ቪላ ውስጥ ባለ አንድ ክፍል ውስጥ ከማንም ጋር ሳይገናኙ እንዲታሰሩ መደረጉ ይታወሳል፡፡ በጊዜው የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ኢህአዴግ ያለበትን ችግርና ሀገሪቱ ውስጥ ሊሆን ይገባዋል የሚሉትን ሀሳብ በፅሁፍ እንዲያቀርቡ፣ ላፕቶፕ አቅርበውላቸው በነበረበት ወቅት የመጀመሪያውን ጥናታዊ ጽሁፍ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ፣ ይህንን ታሪካዊ መጽሐፍ በዛችው ጠባብ የደህንነት ስውር ዕስር ቤት ውስጥ እንዳዘጋጁትና ፅሁፉን ለማጠናቀቅም አራት ወራትን እንደፈጀባቸው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለግዮን መጽሔት ገልፀዋል፡

የነጻነት ታጋዩ አቶ አንዳርጋቸው በወቅቱ በተሰጣቸው ላፕቶፕ ላይ መጽሐፉን ማዘጋጀት ቢችሉም የደህንነት ኃላፊዎቹ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ኮምፒውተሩን የወሰዱባቸው በመሆኑ ለዓመታት ይህንን ጽሁፍ ሳያገኙ ቀርተው ነበር ፡፡ ሆኖም በቅርቡ መጸሐፉ በእጃቸው ሊገባ የቻለበት አጋጣሚ በመፈጠሩ፣ የህትመት ብርሃንን ለማግኘት በቅቷል፡፡ "እስር ላይ እያለሁ ኮምፒውተሩን የወሰብኝ የደህንነት ሰው አሁንም ለመንግስት እየሰራ ነው" ፤ ያሉን አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ በእንግሊዝ ኤምባሲ በኩል ጽሑፉን በኢሜይል እንደላከላቸው ገልፀው፤ ግለሰቡ ይህን ማድረጉ በራሱ በእጅጉ እንዳስገረማቸው፣ ቀና ሰው በመሆኑ መጽሐፉን ሳያጠፋ ማስቀመጡ ማረጋጫ እንደሆነ አመላክተው፣ "በኃላፊነት ከእዚህ ግለሰብ በታች የሆነ ሰው መንግስት እየወሰደ ባለው የሰብዓዊ ጥሰትና ያልተገባ ጥቅም ክስ ለእስር ተዳርጓል፡፡ ምናባልባትም ኮምፒውተሩ በሰዓቱ በዚህ ሰው እጅ ላይ ቢወድቅ ጽሁፉ ሊገኝ አይችልም ነበር" ሲሉ ግርምታቸውን አጋርተውናል፡፡

664 ገጽ የሆነውና፣ በነጻነት አሳታሚነት ለገበያ የሚቀርበው "ትውልድ አይደናገር ፣ እኛም እንናገር" መጽሐፍ በ379 ብር ለገበያ የቀረበው መጽሐፍ አዲስ አበባ ከተማ ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ ያለውን የመቶ አመት ታሪክ፣ የሁሉንም ነዋሪዎች ከባሪያ እስከ አሳዳሪ ያለው አጠቃላይ የሕይወት ውጣ ውረድን የሚያስቃኝ ነው ተብሎ በመታመኑ ከወዲሁ የብዙዎችን ትኩረት የሳበ ሲሆን፣ አዲሱ ትውልድም በቂ ትምህርት ያገኝበታል የሚል ግምትን በበርካታ ፖለቲከኞችና ልሂቃን ዘንድ አሳድሯል፡፡

## ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ከፍትህ አካላት ጋር ተወያዩ

በአንድ ዓመት የስልጣን ዘመናቸው ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችና ሙያተኞች ጋር ሰፊ ውይይት ሲያደርጉ የቆዩት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ሀሙስ ግንቦት 28 ቀን 2011 ከፍትህ አካል አባላት ጋር ተወያይተዋል፡፡

ከመላ አገሪቱ ከተውጣጡ የፍትህ አካላት አባላት ጋር ሰፊ ውይይት ያደረጉት ጠ/ሚኒስትሩ በዚህች ሀገር ላይ ሕዝብ በህግ ፊት እኩል መዳኘትና ሙያተኞችም ቃል ኪዳን በገቡት መሰረት፣ ህግን የተመረኮዘ ግልፅና እውነተኛ አሰራር መሰረት ፍትህን በተገቢው መንገድ ማስፈን እንደሚገባቸው ተናግረዋል፡፡

በውይይቱ ላይ ከ3ሺህ በላይ ዳኞች፣ ዐቃብያን ሕግ፣ ጠበቆችና የፍትህ ዘርፍ አመራሮች እንደተገኙ ከጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት የመጣው መረጃ አመላክቷል፡፡

## ኢትዮጵያ የ74ኛው የተመድ ጉባኤ ም/ፕሬዝዳንት ሆና ተመረጠች

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ለ74ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ፕሬዝዳትና ምክትል ፕሬዝዳንት ሀገራትን ሲመርጥ ኢትዮጵያ የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆና ተመርጣለች፡፡

የፊታችን መስከረም ወር በሚካሄደው 74ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ ናይጄሪያ በፕሬዝዳንትነት ስትመራ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያን ጨምሮ 5 የአፍሪካ አገራት ደግሞ በምክትል ፕሬዝዳንትነት ስብሰባውን ይመራሉ ተብሏል፡፡ በ74ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ የዘላቂ ልማት ግቦች፣ የፖለቲካ ጉባኤ፣ የፋይናንስ ለልማት ስብሰባ፣ የአየር ንብረት ለውጥና ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ከፍተኛ ጉባኤ ዋነኛዎቹ ይሆናሉ ተብሏል፡፡

## በፖለቲካና በብሔር ልዩነት የሚናወጠው፤ የኢትዮጵያ ወንዶች ፕሪሚየር ሊግ ተቋረጠ

የኢትዮጵያ የወንዶች ፕሪምየር ሊግ ውድድር ሊገዜው እንዲቋረጥ የፌደሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ በ27ኛው ሳምንት መርሃ ግብር መካሄድ የነበረበት የኢትዮጵያ ቡና እና መቐለ 70 እንደርታ ጨዋታ በስጋት ምክንያት አለመካሄዱን ተከትሎ ሀሙስ ዕለት ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ በተጠቀሰው ቀን ቡድኖቹ በአዳማ ከተማ አበበ በቂላ ስቴዲየም ያለ ተመልካች በዝግ ስታዲየም እንዲጫወቱ የወሰነውን ውሳኔ መሻሩን ይፋ አድርጓል፡፡

ስራ አስፈፃሚው ከዚህም ባሻገር ቀጣይ የፕሪሚይር ሊግ ውድድሮች በተገቢው ሁኔታ እንዲካሄዱ፣ ከክለቦችና ባለድርሻ አካላት ጋር ተነጋግሮ ዘላቂ መፍትሄ እስከሚያበጅ ድረስ፤ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቋረጥ መወሰኑንና ተጨማሪ ወጪዎችንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርቡ ማናቸውንም ጥያቄዎች በፌደሬሽኑ የዲሲፕሊን የውድድር ደንብ መሰረት እንደሚታይ ገልጿል፡፡

# የቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባዔና ስምንኛ ውሳኔዎች፤

# በደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት ኃላፊ ብፁዕ አባ ያዕቆብ ከስራ ታገዱ !

የርክበ ካህናት ምልአተ ጉባኤው፣ ማክሰኞ፣ ግንቦት 27 ቀን 2011 ዓ.ም. ከየአህጉረ ስብከቱ የቀረቡ የርዳታ እና ድጎማ ጥያቄዎችን አድምጦ፣ የጉዳት መጠኑንና የሚያስፈልገውን ርዳታ ለውሳኔ በሚያመች መልኩ መዝነው የሚያቀርቡ የብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ኮሚቴ ሠይሞ የነበረ ሲኾን፣ ኮሚቴው ባቀረበው መሠረት፣ በድምሩ የ17 ሚሊዮን 900 ሺሕ ብር ርዳታና ድጎማ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት እንዲሰጥ ወስኗል፡፡

የርዳታ ጥያቄውን ላቀረቡት፡- በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት የፈራረሱ 11 የዛል አንበሳ አብያተ ክርስቲያን የሚገኙበት የዓዲግራት ሀገረ ስብከት አንድ ሚሊዮን ብር፤ በጎሠኞች ጥቃት የተፈናቀሉና የተጎዱ አብያተ ክርስቲያንና ምእመናን ለሚገኙባቸው የቤንሻንጉል ጉምዝ አንድ ሚሊዮን ብር፣ የምሥራቅ ወለጋ አንድ ሚሊዮን ብር፣ የሰሜን ሸዋ 300ሺሕ ብር እና የሰሜን ምዕራብ ሸዋ - ሰላሌ 200ሺሕ ብር እንዲሰጥ ወስኗል፡፡

ድጋፍ እንዲደረግላቸው ለጠየቁት፡- በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በግንባታ ላይ ለሚገኘው የመርጡለ ማርያም ካቴድራል 5 ሚሊዮን ብር፣ ለደብረ ሊባኖስ ገዳም የአባቶች ማረፊያ 2 ሚሊዮን ብር፣ ለባሌ ሀገረ ስብከት የአብነት ት/ቤት ቋሚ በጀት 200 ሺሕ ብር እና ለኢሉ አባቦር ሀገረ ስብከት የአብነት መምህራንና ተማሪዎች 200ሺሕ ብር ቋሚ በጀት እንዲመደብ ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል ቅዱስ ሲኖዶስ፣ በዚኹ የርክበ ካህናት ምልአተ ጉባኤው፣ የሦስት ዓመት የጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት ዘመናቸውን በውጤታማነት ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ፣ የቅርስ ጥበቃ እና ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር መምሪያ የበላይ ሓላፊ ሊቀ ጳጳስ እንዲኾኑ መድቧቸዋል፡፡ ምልአተ ጉባኤው ምደባውን ያደረገው፣ ብፁዕነታቸው ከጤና እክል ጋራ በተያያዘ ለክትትል እንዲመች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት እንደ ኾነ ተገልጿል፡፡

ከገቢ አኳያ፣ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ባስመዘገቡት 729 ሚሊዮን ብር ተቀማጭ፣ ምልአተ ጉባኤው ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና የቸራቸው ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ፣ በሀገረ ስብከታቸው መቐለ ዙሪያ፣ ከክልሉ መንግሥት በሊዝ መነሻ ዋጋ በወሰዱት 2070 ካሬ ይዞታ ላይ የሚያስገነቡት፣ ለመንበረ ጵጵስና፣ ለካህናት ማሠልጠኛ እና ለቢሮ የሚያገለግል ኹለገብ ሕንፃ ተጠቃሽ ወቅታዊ ሥራቸው ነው፡፡

ከማክሰኞ ግንቦት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የተመደቡበትን፣ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የቅርስ ጥበቃ እና ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር መምሪያ የበላይ ሓላፊነታቸውን የሚወጡት፣ አህጉረ ስብከታቸውን እንደያዙ መሆኑም ተነግሯል፡፡

የርክበ ካህናት መደበኛ ስብሰባው፣ በአጀንዳ ተ.ቁ(14) በተያዘው፣ አራተኛው ዙር የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተመለከተ፣ የቤተ ክርስቲያን አቋምና ቅድመ ዝግጅት ላይ በጥልቀት ተወያይቷል፡፡

ባለፉት ቆጠራዎች የተፈጸሙትን ግድፈቶች በማረም፣ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮቿንና ምእመናኗን በትክክል ለማስቆጠርና የውጤቱም ተጠቃሚ ለመኾን፣ በአፈጻጸሙ ዙሪያ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በየአህጉረ ስብከታቸውና በማእከልም ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋራ መከናወን ስለሚገባቸው የጥንቃቄና የቅሰቀሳ ተግባራት አቅጣጫና መመሪያ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል ቅዱስ ሲኖዶስ ብፁዕ አባ ያዕቆብን ከደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት አግዷል፡፡ በደቡብ አፍሪቃ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዋቅር መፈራረስ፣ ለምእመናን መከፋፈልና ነፍስ መጥፋት፣ ለሀብት ብክነትና ምዝበራ ተጠያቂ የኾኑት ሊቀ ጳጳሱ ብፁዕ አባ ያዕቆብ፣ እስከ መጪው ጥቅምት ምልአተ ጉባኤ ወደ ሀገረ ስብከቱ እንዳይሔዱ፣ ቅዱስ ሲኖዶስ አግዷል፡፡

እገዳው በሊቀ ጳጳሱ ላይ የተላለፈው፣ ቅዱስ ሲኖዶሱ፣ ቅዳሜ፣ ግንቦት 24 ቀን የርክበ ካህናት ምልአተ ጉባኤ የቀትር በፊት ውሎው፣ በአጣሪ ኮሚቴው በቀረበለት ሪፖርት ላይ ከተወያየ በኋላ ነው፡፡ከአራት ዓመት በፊት ከሀገረ ስብከቱ ታግደው የተመለሱት ሊቀ ጳጳሱ፣ የቀደመ ጥፋታቸውን ከማረም ይልቅ ብልሽታቸው እየተባባሰ መሔዱንና ይቀጥሉ ቢባል፥ የምእመናኑ መከፋፈል፤ የሰርጎ ገቦች ጣልቃ ገብነት እየከፋ ሄዷል ተብሏል፡፡

ሊቀ ጳጳሱ፣ ለምልአተ ጉባኤው አባላት ባሠራጩትና በንባብ ባሰሙት ምላሽ፣ የሪፖርቱን ግኝቶች በሙሉ አስተባብለዋል፤ በቃል በሰጡትም ማብራሪያ፣ ቀደም ሲል በድረ ገጽ ከተብጠለጠሉበት ያልተለየ ሪፖርት እንደኾነ በመጥቀስ አጣጥለዋል፤ “በጎ ሥራዬ አልታየልኝም፤” በማለት አከናወንኩ ያሏቸውን ተግባራት ዘርዝረዋል፤ “በኀጢአት ከማንም አልበልጥም፤ በጽድቅም ከማንም አልበልጥም” በማለት ጉዳያቸው ከታየላቸው አባቶች ተለይተው፣ ከሀገረ ስብከቱ መዛወር እንደማይፈልጉ መልእክት ያስተላለፉበትን የሚመስል አስተያየት አክለዋል፡፡

በስብሰባው ሥነ ሥርዓት መሠረት፣ የልዑካኑን ሪፖርትና የሊቀ ጳጳሱን ምላሽ በቅደም ተከተል ያደመጠው ጉባኤው፣ ብፁዕ አባ ያዕቆብ በውጭ እንዲቆዩ በማድረግ ሲወያይ፣ የተለያዩ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡ በአሉታዊ ነገሮች ላይ ያተኮረና የተሠሩ ሥራዎችን ያላካተተ ሪፖርት ነው፤ በሚል ሊቀ ጳጳሱን ደግፈው በረጅሙ የተናገሩ እንዳሉ ኹሉ፣ “ሀገረ ስብከቱ በኹሉም ነገር ተጎድቷል፤ በአግባቡ አልተዋቀረም፤ ሕጉ ተጠብቆ ሳይኾን በዘፈቀደና በሊቀ ጳጳሱ ውሳኔ ብቻ ነው እየተሠራ ያለው፤ ምንም ነገር የለም፤” በማለት በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲሰሙት የቆዩትን እውነታ ማንጸባረቁን የተናገሩ ብፁዓን አባቶችም ነበሩ፡፡

ሊቀ ጳጳሱ፣ የሀገረ ስብከትና የአድባራት ሓላፊዎችን ምደባ በማሰናከላቸው፣ ካህናትንና መምህራንን ቀጥረው ለማሠራት አቅም ያላቸው ኢትዮጵያውያን ምእመናን የተሟላ አገልግሎት እንደማያገኙ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በአግባቡ እንደማይማሩ፣ ከኹሉም በላይ ብፁዕ አባ ያዕቆብ ገንዘብ ካልተከፈላቸው እንደማይጎበኟቸው፣ ከጥቂቶች ጋራ በጥቅም ከመቆራኘት በቀር ለብዙኀኑ ደቡብ አፍሪቃውያን ትኩረት እንደነፈጓቸው፣ በዚህም ሳቢያ እየኮበለሉ የፕሮቴስታንትን ቸርች የሚያባዙና በቤታቸው መቅረትን የመረጡ እንደተበራከቱ፣ ሪፖርቱ በስፋት ያተተው በእጅጉ እንደነካቸው ገልጸዋል፡፡

ከሪፖርቱና ውይይቱ በመነሣት፣ ሊቀ ጳጳሱ በሀገረ ስብከቱ መቀጠል እንደሌለባቸው አጠቃላይ መግባባት መፈጠሩን ለመረዳት ተችሏል፤ የሚበዙት አባቶች አስተያየት፣ “ከጅምሩ ያጠፉት ነገር ስላለ የሚያስቀጥላቸው አይደለም፤ መዳን አይችሉም፤” የሚል ነው፡፡ ኾኖም፣ በሪፖርቱ አሉታዊው ነገር አመዝኗል፤ አንድ አቅጣጫ ብቻ ነው፤ እዚያው ተመልሰው እየሠሩ ይጠየቁ፤ ጉዳያቸውን ይከታተሉ፤ በሚሉ አባቶች ግፊት ውሳኔው ለጊዜው ወደ እግድ ተለውጧል፡፡

ቀሪውን በገጽ 27 ይመልከቱ

# የሰዶማውያኑ የጉብኝት ፕሮግራም በቅድስት አገር ኢትዮጵያ ሊሳካ አይችልም !

የግብረሰዶማውያኑ ጉዳይ ሰሞነኛ አገራዊ መነጋገሪያ ሆኗል፡፡ ድርጊቱን ስትፀየፍና ስታወግዝ በኖረች በዚህች "ቅድስት ምድር" እንኳን በይፋ ልንነጋገርበት ቀርቶ፣ ፈፅሞ በማንም አፍ የማይነገር "ነውር!" የሆነው ርዕስ እንደገና አነጋገሪ አጀንዳ ሆኖ መቀጠሉ ታላቅ ክስረት ነው፡፡ የምዕባራውያኑ ሠይጣናዊ የመንፈስ ወረራ የት እንደደረሰም ያየንበት አጋጣሚም ነው፡፡

ለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን የጉብኝት ፕሮግራም በማዘጋጀት የሚታወቀው፤ "ቶቶ ቱር" የተሰኘው አስጎብኚ ድርጅት፣ ከአራት ወራት በኂላ ለ14 ቀናት በኢትዮጵያ የሚቆይ የጉብኝት ፕሮግራም አዘጋጅቶ ምዝገባ መጀመሩ ከተሰማ በኂላ፣ ጉዳዩ ትልቅ አገራዊ አጀንዳ ሆኖ ማነጋገሩን ቢቀጥልም፤ ይህን ተከትሎ በአገር ዓቀፍ ደረጃ እየተያዙ ያሉ አቋሞችን በማየት ብቻ ፕሮግራሙ የሚሳካበት ሁኔታ እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አስጎብኚ ድርጅቱ ለሁለት ሳምንት በኢትዮጵያ ለሚቆየው ፕሮግራሙ 7 ሺህ 900 የአሜሪካን ዶላር እየጠየቀ መሆኑ፣ የፕሮግራሙ መርሀግብርም አርባ ምንጭን፣ ደቡብ ኦሞን፣ የጣና ገደማትን፣ ጎንደርን፣ ላሊበላና አክሱምን እንደሚያዳርስ ይፋ ማድረጉን ተከትሎ፣ በርካታ የሃይማኖትና ህዝባዊ ተቋማትን የሚያካትት ሰፊ ውግዘትና ተቃውሞዎች እየተስተጋቡ ነው፡፡

በተለይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ መንፈሳዊ ማህበራት ህብረት የጉዳዩን ክብደትና አደገኛት በሚያንፀባርቁ መልኩ የያዘው የውግዘትና የተቃውሞ አቋም ከሁሉም ጎልቶ እየታየ ሲሆን፣ የማህበራት ህብረቱ ሊቀመንበር የሆኑት ሊቀ ትጉሃን ደረጀ ነጋሽ፣ በተደጋጋሚ ለሚዲያ በሚሰጡት መግለጫ፤ የግብረሰዶማውያን ፕሮግራም ለማስቆም መንግስት ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣ የሃይማኖት አባቶችም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት እንዲንቀሳቀሱ እና ህዝቡም ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ በማሳሳብ ላይ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ህግ የወንጀል ተግባር መሆኑ በግልፅ ተቀምጦ የሚገኝን ድርጊት የሚፈፅሙ ሰዎች፣ አላማቸውን ለማስፈፀም ወደ ኢትዮጵያ ማማተራቸው በራሱ የወንጀል ጥሠት ተግባር እንደሆነ የገለፁት ሊቀ ትጉሀን ደረጀ "አርማችንን ይዘው ላሊበላ ላይ እንገኛለን በማለት መነሳታቸው፣ ከባድ ንቀትና ድፍረት ነው" ሲሉም የአስጎብኚ ድርጅቱን የጉዞ መርሃ ግብር አውግዘውታል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የሀገሪቷ ባህልና ቱሪዝም ዘግይቶም ቢሆን አቋሙን አንፀባርቋል፤ በዚህ ዙሪያ ፈጥኖ የአቋም መግለጫ አለመስጠቱ ግን በራሱ ብዙሃንን "ለምን? እና እንዴት?" የሚሉ ጥያቄዎችን እንዲያነሱ አድርጎ ቆይቷል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ መንፈሳዊነት የሚጫነው፣ ንጹህ ባህልና ወግ ያለው ከመሆኑ አኳያ እንደዚህ ዓይነቱን ተግባር የሚጸየፍ ጭምር መሆኑ እየታወቀ፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው መንግስታዊ ተቋም ከማንም በፊት ሰምቶ፣ ከሁሉም ፈጥኖ አቋሙን አለማንፀባረቁ በርግጥም አጠያያቂ ነው፡፡ ዘግይቶም ቢሆን ማውገዙን ግን የምንደግፈው እንጂ የምንተቸው አይደለም፡፡ በግብረሰዶማውያን ጉዳይ መንግስት ሲከተል የቆየው የተለሳለሰ አቋም ለዓመታት ባለበት የቆየ መሆኑን የታዘቡ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነም፤ መንግስት ሽርፍራፊ ዶላር ከሚወረውሩለት ምዕራባውያን ለጋሽ ሀገራት ጋር ላለመቀያየም ሲል ይህን ፀያፍ ድርጊት ከማውገዝና ከመከላከል ተቆጥቦ ቆይቷል፡፡ ይሁንና ሲሻቸው ከሚወረውሩልን የዶላር እርጥባን በላይ ለኢትዮጵያውያን ውድ ዋጋ ያለውን የባህልና የሀይማኖት እሴት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ መንግስት ከህዝብ ጎን መሆን ይጠበቅበት ነበር፡፡

የግብረ ሰዶማውያኑ ጉዳይ በእጅጉ በሚወገዝበትና በሚኮነንበት የኢትዮጵያ ምድር፣ አገራዊ አጀንዳ ሆኖ መታየቱና መንግስትም ህዝብን የሚያሳዝን አቋም ማንፀባረቁ ዛሬ የተጀመረ አይደለም፡፡ ከ6 እና7 ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ በተካሄደው የICSA ጉባኤ ወቅትም ለጉባኤው ከመጡት በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች ጋር የግብረሰዶማውያን ቡድንም ነበር፡፡ ይህ የቆሸሸና ያደፈ ርካሽ አጀንዳ ይዞ የመጣው የግብረሰዶማውያን ቡድን፣ በአዲስ አበባ "የጌይ ጉባኤ" ለማካሄድ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ሲሰማ "ያገባኛል!" ያሉ የሃይማኖት ተቋማትና ባህላቸውን አክባሪ ዜጎች ድርጊቱን ከማውገዝና ከመቃወም ባለፈ፤ በዚህ ዙሪያ ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት ፈቅደው ነበር፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ የወቅቱ ፓትሪያክ ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ጭምር የነበሩበት ቢሆንም ከመንግስት በተላለፈ ትዕዛዝ ጋዜጣዊ መግለጫውን እንዳይሰጡ ታግደዋል፡፡ መንግስት ግብረሰዶማውያን እንዳይወገዙ መከላከሉም በወቅቱ ብዙ አነጋግሯል፡፡

መንግስት ከኢትዮጵያዊነት ክብር ይልቅ በልመና የሚያገኘው ዶላር የሚበልጥበት መሆኑን ያሳየበት ይህ አጋጣሚ ህዝብን የሚወድ መንግስት በሀገሪቱ አለመኖሩን በግልፅ ከማሳየቱም በላይ፣ የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነትን መልክ ለማጥፋት በድብቅ የሚያሴር፣ በገዛ ሀገሩና ህዝቡ ላይ በጠላትነት የቆመ መንግስት መሆኑንም ያየንበት ሆኗል፡፡

የግብረሰዶማውያን ጉዳይ ከዚያ በፊትም ሆነ በኂላ በተለያዩ ጊዜያት አገራዊ አጀንዳ ሆኖ ብዙ አነጋግሯል፡፡ የሃይማኖት ማህበራትና ተሰሚነት ያላቸው ኢትዮጵያውንም ሲያወግዙት ቆይተዋል፡፡ የጸረ ግብረሰዶም ዘመቻዎቹ ሲከናወኑ የኖሩት ግን በማህበራት እና ግለሰቦች እንጂ፣ በመንግስትም በኩል ይህ ነው የሚባል ድጋፍ አልነበራቸውም፡፡ እንደውም ስለሰዶማውያኑ የወገኑ እንጂ የሀገርን ክብር ያስቀደሙ እርምጃዎችን የወሰደባቸው ጊዜያት የሉም ማለትም ይቻላል፡፡

የሆነው ሆኖ አሁን ጉዳዩ ሀገሪቱን የማጥፋ አጀንዳን ተላብሶ እንደገና መጥቷል፡፡ እጅግ ዘርፈ ብዙ በሆኑ ድብቅና ግልፅ ዘመቻዎች የባህል ወረራ በማድረግ ማንነታችን እንድንረሳና ቅድስናችን እንዲረስክስ ሲያሴሩብን የኖሩት ምዕራባውያን፣ በቶቶ አስጎብኚ ድርጅት በኩል ተመልሰው መጥተውብናል፡፡ እንደከዚህ ቀደሞቹ ሁሉ አሁንም ግን አላማቸው ከግብ የመድረሱ ጉዳይ ከአደጋ ነፃ አይሆንም፡፡ የሀገሪቱ መንግስት ሁለንተናዊ ድጋፍ ቢሰጣቸው እንኳ (በዚህ ወቅት እንደማይታሰብ መገመት ይቻላል) ዓላማቸው ግቡን አይመታም፡፡ ለምን? ቢሉ ይህ የኢትዮጵያ ምድር ነው፡፡

ቅድስናዋን ጠብቃ በክብር በኖረችው በዚህች አገር ሰዶማውያን ሲፈነጩ ከማየት ይልቅ ሞቱን የሚመርጥ፣ ለባህሉና እምነቱ ቀናዒ የሆነ ህዝብ እንጂ ማንነቷን በቡትቶ የሚሸጥ ህዝብ አይደለም የሚኖረው፡፡ እንደሰደድ እሳት ዓለምን ያዳረሰው የሰዶም ዘመቻ እስከዛሬም በአሸናፊነት ያልወጣው በህዝቡ ለማንነቱ ሟችነት ብቻ ነው፡፡ ምናልባት አዲሱ የጠ/ሚ/ር ዐቢይ መንግስት ህዝባዊ ዘመቻውን ይበልጥ አጠናክሮ ይመራው ይሆናል የሚል ተስፋ አለ፡፡ መንግስት ከእርዳታ ይልቅ ለኖረ ማንነታችን የላቀ ዋጋ እንደሚሰጥ ባለፉት አንድ አመታት ያሳየን በመሆኑ፣ ለአሁኑ ዘመቻም ተጨማሪ ጉልበት እንደሚሆን እንጠብቃለን፡፡ ቢሆንም ግን ስጋት አለን፡፡

ሰዶማውያኑን ይዤ በኢትዮጵያ ምድር ባንዲራዬን አውለበልባለሁ ብሎ በልበ ሙሉነት የተነሳው የቶቶ ድርጅትና ደጋፊዎቹ ምዕራባውያን አላማቸውን ለማሳካት የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ተናግረዋል፡፡ የድርጅቱ መስራችና ባለቤት የሆነው ዳንዌር የተባለ ሰው ከዚህ ሁሉ ውግዘት በኂላ "ወደ ኢትዮጵያ የምናደርገውን የጉዞ ፕሮግራም አንሰርዝም" በማለት መናገሩ፣ "ምን ተማምኖ ነው?" የሚል ጥያቄን ያጭራል፡፡ የኢትዮጵያ ባህልና ቱዝም ሚኒስትር መ/ቤት ጉዳዩን በጥንቃቄ እንዲከታተለው ማሳሰቡም "ምን ለመፍጠር አስቦ" እንድንል ያስገድዳል፡፡ ጉዳዩን ወደ አሜሪካ የውጪ ጉዳይ መ/ቤት እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ወደሆኑ ዓለም አቀፍ የዜና ተቋማት እንደሚወስደው በይፋ መናገሩም፣ ከጀርባው እነማን እንዳሉ ምልክት ይሰጣል፡፡ ነገርየው ተራ የቢዝነስ ጉዳይ ሳይሆን ለዘመናት ያላረፈው የምዕራባውያን ሠይጣናዊ ዘመቻ አንድ አካል እንደሆነ ከገባን ደግሞ፣ አሁንም በንቃት መቆምና መንግስትንም በህዝባዊው እንቅስቃሴ ከፊት እንዲቆም ማስገደድ ይኖርብናል፡፡ መንግስት መግለጫ ከማውጣት በዘለለ መልኩ በድብቅ የሚካሄዱ የግብረሰዶም እንቅስቃሴዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ወጥሮ መያዝም ወቅቱ ይፈቅድልናል፡፡

# ጥያቄ! ጥያቄ! ጥያቄ! መልስ በጠፋበት ዘመን

መላክ ቢ.

ኢትዮጵያ በጥያቄ ተወጥራለች። ከዚህም ከዚያም አቅጣጫ ሁሉም ጠያቂ ነው። የማይጠይቅ ባለሙያ፣ የማይጠይቅ ብሔረሰብ፣ የማይጠይቅ ተቋም፣ የማይጠይቅ ክልል የለም። መልስ ግን የለም። መልስ በጠፋበት ዘመን ጥያቄ በዝቷል። ጥያቄ ምላሽ ባጣ ቁጥር ተቃውሞ በርክቷል። ጥያቄዎች ሁሉ "አሁኑኑ ወስኑ፣ አሁኑኑ ውለዱ" አይነት ነገር መስለዋል። የሃገሪቱ ማለቂያ አልባ ጥያቄዎች ጎርፍ ፈጥረው የጠ/ሚ/ር ዐቢይን አስተዳደር ከቆመበት ስሩን ነቅለው እንዳያንገዳግዱት የሚሰጉ ብዙዎች ናቸው። "27 ዓመት ሙሉ ለጥ ብለው የከረሙ ሁሉ ጥያቄዎቻቸውን ለምን ዛሬ አነሱ?" ብለው የሚወቅሱም በርክተዋል። ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በቅ ባሉ ቁጥር ደግሞ ከራሳቸው ንግግር ውስጥ ሌሎች ጥያቄዎች እየተመዘዙ እየወጡ ማለቂያ አልባ ክርክሮች መነሻ ሆነዋል። "ክልል እንሁን፣ ልዩ ዞን እንሁን፣ ሃዋሳ የኛ ትሁን፣ አዲስ አበባ የኛ ትሁን፣ ደመወዝ ይጨመርልን፣ ጥቅማጥቅም ይሟላልን፣ ቤትና መኪና ይፈቀድልን፣ የህክምና ዘርፍ ችግር ይቀረፍልን፣ የትምህርት ዘርፍ ፖሊሲ ይለወጥልን" ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች አየሩ ላይ ይተራመሳሉ። ሚዲያዎች ጥያቄዎችን ይዘው ያወያያሉ፣ ዜና ይሰራሉ፣ ያናፍሳሉ፣ ያራግባሉ፣ ጥያቄዎች አልተመለሱም የሚሉ ቅሬታቸውን ይፋ ያደርጋሉ፣ ውጥረት የሚመስሉ ነገሮች ይከሰቱና ዳግም ይከስማሉ። ጥያቄ በዝቷል። መልስ ሰጪ ግን የለም። ወይም በቂ ምላሽ አገኘሁ ያለም የለም። ብዙዎች መንግስት ጥያቄዎችን የሚይዝበት እና ምላሽ የሚሰጥበት አግባብ ጤናማ አይደለም እያሉ ይተቻሉ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ጥያቄ መጠየቁ የሚጠበቅ ነው" እያሉ ነው። "ታፍኖ የኖረ ጥያቄ ሲከፈትለት ግር ብሎ ቢወጣ አይደንቅም" እያሉ ነው። ጠያቂዎቹ ደግሞ "ለመጠየቅ ስንል ሳይሆን፣ ለማስመለስ ነው የቆምነው" እያሉ ነው። በዚህ መሃል ሃገር የጥያቄ ጎተራ መስላለች።

## የፌሬዳሊዝም ጦስ ጥያቄዎች

ኢህአዴግ ሰባቱን የደቡብ ክልሎች አጥፎና ጨፍልቆ አንድ አደረጋቸው። እንደፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ አገላለጽ እነአቶ ታምራት ላይኔ በሂሊኮፕተር ወደደቡብ መጥተው "ከአሁን ጀምሮ ደቡብ ክልል አንድ ክልል ሆኗል" ሲሉ ማመን ቸግሮኝ ነበር ይላሉ። ኢህአዴግ ቋንቋን መሰረት ባደረገ የብሔር አከላለል ኢትዮጵያን ዘጠኝ ትናንሽ አደረጋትና ስሙን ፌዴራሊዝም ብሎ ጠራው። ይህ በብዙዎች እንደሚታመንበት የከፋፍለህ ግዛ፣ የግዛት ማስፋፋት እና መቁረስ ዓላማን ያነገበ የአስተዳደር አወቃቀር በጊዜው ተቃውሞ አስነስቶ ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተቀበረ ከባድ ቦምብ ሆኖ ዛሬ ድረስ ላላባራ ቀውስ ምክንያት የሆነው ይህ የሕወሓት ኢህአዴግ ስራ ሃገሪቱ ዛሬ ላለችበት የብሄር ቡጭቂያ እና የዘር ካርድ መዘዛ ዋናው መነሻ ነውም ተብሎ እየተኮነነ ነው።

እነዚያ ቀድሞ ራሳቸውን ችለው ህዝባቸውን ሲያስተዳድሩ የነበሩ የደቡብ አስተዳደራዊ አወቃቀሮች ፈርሰው፤ "የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል" ተብሎ ሲመደብ ምክንያት የተደረገው የየብሄሩ የህዝብ ቁጥር አንድ ክልል ለመመስረት በቂ አይደለም የሚል ነበር። ጋምቤላ፣ ሐረሪ፣ ሶማሊ፣ አፋር እና ቤኒሻንጉል በቆዳ ስፋት ካልሆነ በቀር በህዝብ ቁጥር ከአንዳንድ የደቡብ ህዝቦች ጋር ሲተያዩ ትንሽ ሆነው እያለ፣ ክልል መሆናቸው ያንገበገባቸው በህግ እና አስተዳደር ፊት እኩል የመሆን ጥያቄ አነሱ። ኢህአዴግ በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የፌዴራሊዝም አከላለሉን ሲተገብር ላይ ላዩን "ህዝቦቿ በመፈቃቀድ የሚገነቧትን ኢትዮጵያ እመሰርታለሁ" ብሎ ቢሆንም በተግባር ግን ህዝቦቿን ሳያስፈቅድ እየከፋፈለ እንዳይገናኙ የማድረግ ሴራም ሸርቦ እየጋታቸው ነበር።

**...የሕወሓት ኢህአዴግ ፌዴራሊዝም አወቃቀር ሲጀምር የታሰበበት እኩይ ዓላማ ይዞ ስለመነሳቱ ሳያነቅፉቸው የሚያወሩ ብዙዎች ናቸው። ሲደላ ረግጦ ለመግዛት፣ ሲከፋ በታትኖ ሃገር ለማፍረስ የታለመለት አካሄድ መከተሉን ሁሉም ይስማሙበታል...**

ሲዳማ የደቡብ ክልል ትልቅ ብሄርነቱን ፣ የቀድሞ አስተዳደራዊ መዋቅር ባለው ስም ግዛትነቱን መመሰረት አድርጎ ከዚህ "ባርነት" ብሎ ከሚጠራው አስተዳደር አርነት ለመውጣት "ሲአን" ን መስርቶ ብዙ ታግሏል። ሲ..አ.ን እና አባላቱ ከሃገር ተሰድደው እና ተወግረውም ጭምር ዝም እንዲሉ ተደርጓል። ዛሬ ሲዳማ "ክልል ልሁን" ብሎ ያነሳው ጥያቄ ህገመንግስታዊ ጥያቄ ነውና አሁን ድረስ የተቋጨ ውሳኔ ሳያገኝ በእንጥልጥል ላይ አለ። ቀስ ብሎም ክልል መሆን ብቻ ሳይሆን "ሐዋሳም የክልሌ ዋና ከተማ ሆና መመዝገብ አለባት" በማለት በአሁኑ አወቃቀር የደቡብ ክልል መናኸሪያ የሆነችውን ሐዋሳን የግሉ ለማድረግ ጥያቄ አቅርቧል።

ጥያቄው ሳይመለስ ወይም ሳይከለከል በመቆየቱም በክልሉ ከፍ ያለ ግጭት እንዲቀሰቀስ እና በዚያም ብዙሃን እንዲያልቁ፣ እንዲፈናቀሉ እና እንዲሸበሩ ምክንያት ሆኗል። ኤጀቶ የተባለ የወጣቶች ቡድን በህቡዕ ተደራጅቶ ድንገት በመገንፈል የክልሉን መስተዳደር ህንጻ እስከመውረር እና ባንዲራውን አውርዶ በራስ ባንዲራ እስከመተካትም የደረሰ ተግባር ተፈጽሟል። ሲዳማ ክልል ይሁን የሚለው ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ መስመር ላይ ቢሆንም፣ በዚያው ታኮ የተነሳው የሐዋሳ ጉዳይ አሁንም በክልሉ አለመረጋጋትን እየፈጠረ ይገኛል። ለዚህ ጉዳይ ግን አሁን ድረስ ቁርጥ ያለ ምላሽ መስጠት አልተቻለም። ሲዳማም ከነጥያቄው እና ያላባራ ተቃውሞው ጋር እነሆ አለ።

ሲዳማን ተከትሎ የክልል እንሁን ጥያቄ ያመጣው ወላይታ ነው። ወላይታ በሐዋሳ ባሉ ▶

ልጆቹ ላይ በሲዳማ አክራሪ ብሄርተኞች የተካሄደበትን ግድያ እና የደረሰበትን የዜጎች መፈናቀል መነሻ በማድረግ “ክልል ብንሆን ማንም አይደፍረንም” ብሎ ጥያቄውን አንስቷል፡፡ ከወዲሁ የወላይታ ብሄርተኝነት አቀንቃኞች ተደራጅተው የወላይታን ክልልነት ራሳቸው አውጀው አጽድቁልን እያሉ እየወተወቱ ነው፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ ጭምር በታገዘ ዘመቻ ወላይታ በአንድ ወቅት የራሱ የሆኑ አስተዳደራዊ መዋቅሮች እና ክልል የነበረው ህዝብ ሆኖ ሳለ ዛሬ እንደአንድ አናሳ ብሄር በብዙሃን ተውጦ እና ተወሽቆ ሊጠቀለል አይገባውም እያሉ ነው፡፡ ለዚህም ጉዳይ የተሰጠ ቁርጥ ያለ ምላሽ የለም፡፡ ጥያቄው ግን በተገኘው መድረክ እየተሰራ ልክ እንደሲዳማ ወጣት ቡድን “ኤጀቶ” ሁሉ ወላይታም “የላጋ” የሚባል ቡድን ፈጥሮ እየተሟገተ ነው፡፡

በቅርቡ በሶዶ ከተማ ላይ ሰፊ እና የቀድሞ መከላከያ ሰራዊት አባላት የሆኑ የብሔሩ አባላት የተካፈሉበት ግዙፍ ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደም ጥያቄዎቹን በሰላማዊ መንገድ አቅርቧል፡፡

ደቡብ በዚህ ብቻ ሳይሆን ብዛት ባላቸው የልዩ ዞን እንሁን እና ወረዳ እንሁን እንዲሁም ክልል እንሁን የሚሉ ጥያቄዎች ተጨናንቋል፡፡ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ኢህአዴግ በአንድ ውሳኔ ጠቅልሎ እና ጨፍልቆ አንድ ያደረገው ክልል ዳግም ለመበታተን ቋፍ ላይ ቆሟል፡፡ የሃብት ክፍፍል፣ የመብት አጠባበቅ፣ የውሳኔ አሰጣጥ ወዘተ ላይ በደል አለብኝ ያሉ ሁሉ ራሳችንን ብንችል ይበጀናል እያሉ ነው፡፡

የሕወሓት ኢህአዴግ ፌዴራሊዝም አወቃቀር ሲጀምር የታሰበበት እኩይ ዓላማ ይዞ ስለመነሳቱ ሳያነቅፋቸው የሚያወሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ሲደላ ረግጦ ለመግዛት፣ ሲከፋ በታትኖ ሃገር ለማፍረስ የታለመለት አካሄድ መከተሉን ሁሉም ይስማሙበታል፡፡ ኢህአዴግ ለ27 ዓመታት የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ተግባራትን ሲፈጽም ኖሮ፣ በጠመንጃ አፈሙዝ ስር ያፈናቸውን የራሱ ፍጡር የሆኑ ጥያቄዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የሚያልፍበት ዘመን እንደሌለ ያውቃል፡፡ የሰራውን መተት ራሱ ማፍረስ ስላቃተውም ተጨንቋል፡፡

በአማራ ክልል የቅማንት ህዝብ ተጨፍልቂያለሁና የብሔረሰብ አስተዳደር ያስፈልገኛል ብሏል፡፡ የራያ ህዝብ የአማራነት እና የቋንቋ እውቅና እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡ ኦሮሞ ቋንቋው የሆነውን አፋን ኦሮሞ የሃገሪቱ የስራ ቋንቋ እንዲሆን ጠይቆ ፍቃድ ያገኘ መስሏል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ከዛሬ ነገ ጦርነት ያማዝዛል ተብሎ የተሰጋበት የትግራይ እና አማራ ክልል የድንበር ጥያቄ አፍጥጦ ቁጭ ብሏል፡፡ አማራ እስከሁመራ የኔ ነው እያለ ነው፡፡ ወልቃይት፣ ራያ እና ሌሎችም ከተከዜ ወንዝ ማዶ ወዲህ ያሉ አካባቢዎች የኔ ናቸው እያለ ነው፡፡ ደራም ከኦሮሚያ ተላቅቆ የአማራ መሆን አለበት የሚል ጥያቄም በቅርብ ጊዜ መቀንቀን ጀምሯል፡፡ ግጭት ተከስቶም ሰው በዚህ ጦስ አልፏል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም እና ክልል ያመጡት ጦስ ሃገሪቱን በማያባራ ጥያቄ ውስጥ እንድትወደቅ አድርጓታል፡፡ ህዝብ እንደህዝብ እውቅና አልተሰጠኝም እያለ ነው፤ ህዝብ እዚህ መኖር አትችልም ሰፋሪ ነህ ተብሎ እየተባረረ ነው፡፡ ህዝብ ቋንቋዬን አልቻልክም እና ከዚህ ክልል ውጣ እየተባለ ነው፡፡ ህዝብ በሚሊዮኖች እየተፈናቀለ ነው፡፡ ሃገር ሁሌም እንደተወጠረ ፊኛ በጥያቄ ተነፍታ መፈንጃዋን ቀን የምትጠብቅ መስላለች፡፡ እንዲያም ሆኖ ምላሽ የለም፡፡ ምላሽ ለመስጠትም ሁኔታው ቀላል አይደለም፡፡ ምላሹ የሚያስከትለው ነውጥም ቀላል አይሆንም፡፡ በዚህ ውጥረት መካከል የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር ግራ የተጋባ መስሎ ዝም ብሏል፡፡

## የሕገመንግስት ጥያቄዎች

ኢህአዴግ “ከሰለጠነው ዓለም ኮማ ሳይቀር ተገልብጦ የተረቀቀ ዘመናዊ ሕገመንግስት” የሚለው የኢትዮጵያ ሕገመንግስት እንደፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም አገላለጽ መሰረቱን ሰው ያላደረገ፣ የመንግስትን ፍላጎት ማስፈጸሚያ አጀንዳ የሆነ፣ መሬት ላለው እውነት ሳይሆን በልብ ላለው ክፋት ማስፈጸሚያ የሆነ “ሕገ አራዊት” ነው፡፡ ሕገመንግስቱ ዜግነትን ኋላ ጥሎ እና ብሔርን አግንኖ፣ የግለሰብ መብት እየተደፈጠጠ፣ የቡድን መብት ይከበራል የሚል ዓይነት የማያስማማ ተረክ ይዞ በመምጣቱ፤ ከጅምሩ ተቃውሞዎች በርክተውበት ነበር፡፡ አንቀጽ 39ኙን ጨምሮ አሚጋች እና በሴራ የተሸፈኑ የሕገመንግስቱ ድንጋጌዎች ለዘመናት ሲያታግሉም ኖረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕገመንግስት በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ላይ የይስሙላ ሕጎችን ደርድሮ በሌላ በኩል ሃገር እንደሃገር ጸንታ የምትኖርባቸውን መሰረታውያን በመግፋት አንድነትን አደጋ ውስጥ መጨመሩ ለብዙዎች የኢህአዴግ ሴራ ውጤት ነው፡፡ በተለይ ሕወሓት የራሱን የረጅም ጊዜ አላማ ለማሳካት ሴራ የጎነጎነበት ሕገመንግስት እነሆ ህዝብንም ሃገርንም አንድ አድርጎ የማቆየት ሃይል እንደሌለው ያስመሰከረበት ጊዜ ላይ ነን፡፡

## የሙያ እና የቡድን ጥያቄዎች

ከሃገር አቀፍ የክልል እና የብሔር እንዲሁም የቋንቋ ጥያቄዎች መለስ ስንል አሁንም ከፊታችን ሌላ ጥያቄ ተገትሮ እናገኛለን፡፡ የባለሙያዎች ጥያቄ፡፡

በቅርብ ጊዜ ውስጥ ብቻ በኢትዮጵያ ሁለት ግዙፍ የሚባሉ የሙያ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ቀዳሚው የሕክምና ባለሙያዎች ያነሱት ጥያቄ ሲሆን፤ ተከታዩ ደግሞ መምህራን ያነሷቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ጥያቄዎች በተለይም በሕክምና ባለሙያዎች የተነሳው ጥያቄ የሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን የውጭ መገናኛ ብዙሃንን ቀልብ የሳበ፣ የጠ/ሚ/ር ዐቢይን አስተዳደር አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ ያስገደደ፣ ነገር ግን ራሳቸው ጠ/ሚ/ር ዐቢይም ገብተውበት ቢሆን ሊያበርዱት ያልተቻላቸው ከባድ ጥያቄ ነበር ፡፡

## የሕክምና ባለሙያዎች ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ ከባድ የሚባሉ ክፍተቶች ያሉበት እና በችግሮች የተሞላ ዘርፍ መሆኑን ነው ባለሙያዎች የሚናገሩት፡፡ የኢትዮጵያ የሕክምና ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ገመቹስ ለማ እና ምክትላቸው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በኢሊሌ ሆቴል በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንዳብራሩት፤ በኢትዮጵያ የህክምና ታሪክ ውስጥ ቀዳሚ የሆነው የህክምና ማህበር ላለፉት 30 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ዓመታት የህክምና ዘርፍን እና የሃኪሞችን የመብት ጥያቄ አንስቶ መንግስት ጋር ሲመላለስ ኖሯል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ሃገሪቱ ከድህረ ደርግ በኋላ በተከተለችው የበሽታ መከላከል ፖሊሲ ውጤት ቢመዘገብም በዚያው መጠን ደግሞ የህክምናው ዘርፍ ተረስቶ እና ተዘንግቶ መኖሩ በህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት ጥራት፣ ተደራሽነት እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የማይቃና የሚመስል ጉብጠት አስከትሏል፡፡ ይህ የዘርፉን ችግር ውስብስብ ወደሆነ ደረጃ በማሸጋገሩ ሃኪም አክሞ የማያድን ፣ ህመምተኛ ታሞ የማይድን ሆኖ የሃገሪቱ ህክምና ስርዓት ቁልቁል ወርዷል፡፡

መንግስት ለዘርፉ የሚመድበው በጀት ከሚጠበቀው 15 በመቶ በታች 4 እና 5 በመቶ ብቻ መሆኑ፣ የህክምና ባለሙያዎችን በብዛት ለማምረት የተከፈቱ ትምህርት ተቋማት ጥራት ያለው ትምህርት አለመስጠታቸው፣ 100ሺህ የህክምና ባለሙያ በሚያስፈልጋት ሃገር ላይ ሆነን ተማሪዎቹ ዶክተር ሆነው ሲወጡ የሚገቡበት ህክምና ማዕከል ባለመገንባቱ ለስራ አጥነት መዳረጋቸው፣ የሃኪሞች የደምወዝ፣ የስራ ሰዓት እና የትርፍ ሰዐት ክፍያ አለመስተካከሉ ህክምናን የወረደ ሙያ እንዳደረገው፣ መንግስት ጀግና ነኝ የሚልበት ዘርፍ የላሸቀ ውጤት የሚዘገብበት መሆኑ፣ በጤና ባለሙያ እና በታካሚ መካከል ያለመተማመን መፈጠሩ ወዘተ ባለሙያዎቹ ሆ ብለው ተቃውሞ እንዲወጡ ያደረጋቸው ነገር ሆኗል፡፡

በዚህ ሳቢያ ሚያዝያ 26 ቀን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ 3ሺህ ከሆኑ ዶክተሮች እና የጤና ባለሙያዎች ጋር ባደረጉት ስብሰባ ላይ የተጠቀሟቸው ቃላት ሃኪሞቹን ስላስቆጣቸው እና ጥያቄያቸው የጥቅማ ጥቅም ብቻ ተደርጎ ስለተወሰደባቸው ለሰላማዊ ሰልፍ ብቻ ሳይሆን ለስራ መቆም አድማ ጥሪ ማድረግና ያንንም መተግበር ጀመሩ፡፡ ይሄኔ ከባድ የሚባል ችግር መምጣቱንና በተለይ የጤናው ዘርፍ ሴክተር ወደቆ የአሁኑ አስተዳደር የባሰ ማጥ ውስጥ ሊገባ መሆኑ ጥገናዊ ለውጥን እንዲያደርግ አስገድዶታል፡፡ እንዲያም ሆኖ የደመወዝ ጥያቄ በጥቂቱ፣ ከ450 ሺህ ብር እስከ 1ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር ይጠየቅበት የነበረው የትምህርት ወጪ መጋራት ውሳኔም እንዲሁ ቢሰረዝም በዚያው መጠን አሁንም በዘርፉ ላይ እና በህክምና ባለሙያዎች መብት አጠባበቅ ላይ ያሉት ክፍተቶች በቀላሉ የማይቀረፉ በመሆናቸው ጥያቄው ቀጥሏል፡፡

የሕክምና ባለሙያዎች በተለይ ኢንተርን የሚባሉት ለተግባራዊ ልምምድ ስራ ላይ

የሚገኙ የመጨረሻ ዓመት የህክምና ተማሪዎች፤ እንዲሁም ለልዩ ሙያ ወይም ስፔሻላይዜሽን ኮርስ ላይ ያሉ ሐኪሞች ስራ በማቆም ያነሷቸው ጥያቄዎች በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በታካሚው ላይ ከባድ ችግር አድርሷል።

በኢትዮጵያ ሕግ የሕክምና ሙያ የስራ መቆም አድማ የማይደረግበት ነው ቢባልም፣ ይህንን ሐኪሞቹ ቢያውቁም ችግሩን ለማሳየት ግን አማራጭ አድርገው የጥያቄያቸው ማጠናከሪያ አንድ መንገድ አድርገው ተጠቅመውበታል። ዛሬም ድረስ ያልቆመው የሕክምና ባለሙያዎቹ ጥያቄ አሁን ድረስ ጥያቄ ለበዛባት ሃገር ከባድ ችግር ሆኗል። ጉዳዩ ጠበቅ ብሎም የፖለቲካ ቅርጽ የያዘ እና አጀንዳ ያላቸው ፓርቲዎችና የፖለቲካ ቡድኖችም በዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ላይ ጫና ለማሳደር የሚጠቀሙበት አንድ መንገድ ከፍቶላቸዋል እየተባለ ነው።

## የመምህራኑ ጥያቄ

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የመምህራን ደርሻ የጎላ ነው። ከ1966ቱ አብዮት ጀምሮ እስከ መካከለኛው የኢህአዴግ ዘመን የመምህራን ተቃውሞ ድረስ የኖረ ብዙ ታሪክ ያለው ሙያ ነው መምህርነት። በዚህ የኢህአዴግ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶታል የተባለው ይኸው ሙያ ቢሆንም ዘርፉ ጥያቄ ከማንሳት ግን አላገደውም። የመምህራን ደመወዝ ማሻሻያ፣ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት እና መሰል ጉዳዮች ቢሻሻሉም መምህራን አሁንም ገቢያችን ከኑሯችን ጋር አላላውስ ብሎናልና ትውልድን የማፍራት አቅም የለንም እያሉ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው ጥያቄ ማቅረብ ጀምረዋል።

መምህራኑ ሰሞኑን ባደረጓቸው የተቃውሞ የአደባባይ ሰልፎች ላይ መንግስት ኃይል ተጠቅሟል ብለው ይከስሳሉ። "ባለፉት 26 አመታት ተደጋጋሚ ስህተቶችን በመሥራት ከስህተቱ ሳይማር ዛሬም በሥልጣን ላይ የሚገኘው ገዢው ፓርቲ ዛሬም ከአንድ መንግሥት ነኝ ባይ የማይጠበቅ ተግባር በመፈፀም ላይ ይገኛል። መምህራን ተደራጅተን በሠላማዊ መንገድ ጥያቄያችንን እንዳናቀርብ አንጋፋውን የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ከእውነተኞቹ ተወካዮቻችን ከእነዶክተር ታዬ ወልደሰማያት እና አሠፋ ማሩ ተቀብሎ በገንዘብ ሕሊናቸውን ለሸጡ የመምህሩ ጉዳት እና የትውልዱ ምክነት ለማይሰማቸው የተወሰኑ የኢህአዴግ አባላት በመስጠት መምህሩን ያለተወካይ አስቀርቷል" እያሉ ነው።

መምህራኑ በመግለጫቸው እንደሚሉት ከደምወዝ ጭማሪው በመንግሥት አጠራር ማስተካከያ ጋር በተያያዘ እኛ መምህራን ያለንን ጥያቄ በተወካዮቻችን አማካኝነት እንዳያቀርቡ "ኢህአዴግ ጠፍጥፎ የሰራው" የሚሉት የመምህራን ማህበር እንቅፋት ሆኖባቸዋል።

በዚህም የተነሣ መምህራን መብታችንን ለማስከበር በሕቡዕ መንቀሳቀሱ የተሻለ መሆኑን ተረድተን የራሳችንን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የምንገኝ ሲሆን የስራ ማቆም አድማው በሰፊው ተቀጣጥሎ ንጹሃን ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ከመራቃቸው በፊት መንግሥት ነኝ ባዩ ኢህአዴግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአፋጣኝ ሊመልስ ይገባል" ሲሉም ነው ጥያቄ ያቀረቡት። ከጥያቄዎቻቸው መካከልም " በሃገራችን ለተመሳሳይ የትምህርት ደረጃዎች የሚከፈለው ደምወዝ ልዩነት እጅግ የተጋነነ ልዩነት ከመሆኑ ባሻገር 20 አመት የሰራ መምህር ደመወዝ ከ6000 ብር የማያልፍ መሆኑና ጀማሪ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው አንድ የወረዳ ተራ ካድሬ መነሻ ደመወዝ ግን ከ6000 ብር በላይ መሆኑን ቀዳሚ ያደርጋሉ። በቅርቡ በአዲስ አበባ ለሚገኙ መምህራን ተከፋፈለ የተባለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች እጣ እጅግ ሲበዛ ኢፍትሃዊ የነበረና መንግስትን ይቃወማሉ ተብለው የሚታሰቡ መምህራን እጣው ውስጥ እንዳይሳተፉ በክፍለ ከተማ አመራሮች ተደርገዋል፤ በማለት መንግሥት በሚዲያ ይቅርታ በመጠየቅ ስማቸው ከእጣ ውጭ የሆኑ መምህራን የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያድርግም ብለዋል። "ተለጣፊው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በአስቸኳይ ፈርሶ፣ ሁሉንም መምህር ባሳተፈ መልኩ በገለልተኝነት የሚሰራ የመምህራን ማህበር በአስቸኳይ ይቋቋም ዘንድ መንግሥት ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻች" እንዲሁም "ከመምህራን የሥራ ማቆም አድማ ጋር በተያያዘ ለእስር የተዳረጉ መምህራን ባልደረቦቻችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በነፃ ይለቀቁ" በማለት ጠይቀዋል። ይህ ጥያቄ በ2009 የቀረበ ቢሆንም አሁንም በ2011 ዳግም በሰልፍ ቀርቦ እንዲሁ ከመንግስት ጋር መላተምን ፈጥሯል። "ያኔ የጠየቅነው አልተመለሰልንም" ያሉት መምህራን አሁንም ይህንኑ እና ሌሎችን ጥያቄዎች አንግበው ወጥተዋል። የጠ/ሚር ዐቢይ አስተዳደርም የመምህራን ደምወዝና ጥቅማ ጥቅም ማሻሻያ በትምህርት ሚኒስቴር እየተከለሰና እርማት እየተደረገበት ነው ብሏል። ያም ሆኖ መምህራኑ በተደጋጋሚ ጊዜ ጥያቄ ሲያቀርቡና ጥገናዊ ምላሽ ብቻ ሲሰጣቸው መኖራቸው ስላበሳጫቸው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸውን በገለፁ እለት በፖሊስ ታስረው ተንገላተዋል የሚሉ ሪፖርቶችም ወጥተዋል።

## የጥያቄ ዘመን?

ብዙዎች 27 ዓመታት ሙሉ ጥያቄ ያልቀረበበት ዘመን አልፎ አሁን ሃገር ሳትረጋጋ እንዴት በዚህ ዘመን ጥያቄ ይቀርባል? የሚል ሃሳብ ያነሳሉ። ሁለት ምክንያቶች ለዚህ ምላሽ ተደርገው ይቀርባሉ። አንዱ ሃገሪቱ አሁን ያለችበት የፖለቲካ ሁኔታ የታፈኑ ብሶቶች የገነፈሉበት እና መንግስትም ህዝብ እንዲናገር የፈቀደበት፣ በዚህም ብዙ ሃሳቦች መድረክ ላይ የወጡበት በመሆኑ ዘመኑን የጥያቄ ዘመን አድርጎት ነው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሆን ተብሎ በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር ላይ ጥላቻ ያላቸው ወገኖች የተዳፈኑ ጥያቄዎችን እየቆሰቆሱ ጫና ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት ውጤት ነው እያሉ ነው።

> ...በኢትዮጵያ ህግ የህከምና ሙያ የስራ መቆም አድማ የማይደረግበት ነው ቢባልም፣ ይህንን ሃኪሞቹ ቢያውቁም ችግሩን ለማሳየት ግን አማራጭ አደርገው የጥያቄያቸው ማጠናከሪያ አንድ መንገድ ኢድርገው ተጠቅመውበታል...

በርግጥ ኢትዮጵያ መልስ የምትሰጥበት ዘመን ላይ አትመስልም። በሁሉም ዘርፍ የሚጠየቁ ጥያቄዎቿን እንኳን በተዳከመ ኢኮኖሚ ላይ ያለው የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር ቀርቶ የቀደመው ዘራፊ የኢህአዴግ አስተደዳደርም ሊመልሰው የማይችለው ከባድ የኢኮኖሚ ፣ የመዋቅር መስተካከል፣ የሰው ኃይል ቅንነትና አመለካከት እንዲሁም የፖለቲካ ፍቃድ የሚፈልግ ነው። የቀደመው አስተዳደር በጠመንጃ አፍኖ በጸረ ሽብር እና ሕገመንግስት መናድ አንቀጾች ሽብቦ ዝም ያስባለው ህዝብ መንገድ ሲከፈትለት በአንድ ጊዜ ሁሉንም ጥያቄ ማንሳቱም በራሱ ለጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር ራስ ምታት መሆኑ አይቀሬ ነው።

ያም ሆኖ አሁን ያለው ህዝብ ሃገር ያለችበትን ሁኔታ የሚገነዘብ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ እና መዋቅራዊ ጉዳዮች ብዙም ውጥረት ውስጥ አይከቱም። የሚፈለገው ነገር የጠቅላይ ሚኒስትሩ ምላሽ የመስጠት እና ተስፋ የማበጀት ሁኔታ በምሬት እና በሽርደዳ ሳይሆን በቀጥተኛ ችግሩን ገላጭ በሆነ መልክ መሆኑ ነው የሚፈለገው። ከፍትፍቱ ፊቱ እንዲሉ።

በሌላ በኩል የፖለቲካ ጥያቄዎች የኢህአዴግ ሴራ ውጤቶች ናቸውና ሃገሪቱን ወዴት ይመሯታል? የሚለውን መገመት ይከብዳል። ማስተካከያ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ የሕግ ማሻሻያ ጭምር እየተካሄደ ወይም ህዝበ ውሳኔ ድረስ የሚያስደርስ ከሆነም ያ እየተተገበረ መስመር ማስያዝ ግድ ይሆናል። ከመስመሩ አፈንግጦ የሚጓዝ በህግ አግባብ እንዲታረም እየተደረገም ሃገር ከመበታተን ወይም አደጋ ውስጥ ከመግባት ስጋት ልትድንም ግድ ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አመራር እና አስተዳደር በዘርፈ ብዙ ጥያቄዎች መወጠሩ በአንድ በኩል የአመራር እና ችግር አፈታት ጥበቡን አይቶ ብቃቱን ለመመስከር፣ በሌላ በኩል ጥያቄዎቹ በራሳቸው ይዘው የሚመጡት ምላሽ የተሳሳተ ፖሊሲን እና አቅጣጫን ለማረም መንገድና ግብዓት በመሆን የሃገሪቱን ችግር ለመፍታት መነሻ ይሆናሉ። የህዝብ ጥያቄን በቀና ልብ መመልከት ለመፍትሄ ያቀርባል። በጥርጣሬ እና በጸረሰላም ሃይሎች ሽፋን መመልከት ደግሞ ከመፍትሄው ያርቃል። በዚህ ረገድ ተቀደመው ኢህአዴግ አፍኖ ያልዘለቀውን ድምጽ አሁን ማፈን፣ ከቀደመው ስህተት አለመማር እንዳይሆን መጠንቀቅ ተገቢ ነው። ለጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ምላሽ መስጠት ተገቢ ቢሆንም ሃገር አቅም እና ብቃት በሌላት ጊዜ ችግርን መስማት ችግርን የመፍታት አንድ መንገድ መሆኑም መዘንጋት የለበትም።

# ሰይጣናዊ ተልዕኮ ያነገቡት፤ የግብረ ሰዶማውያኑን ጉብኝት በፅኑ እንቃወማለን!

በአሜሪካ የሚኘውና "ቶቶ" በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የግብረዶማውያን አስጎብኚ ድርጅት፣ ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት የሚጓዝ መሆኑን በማህበራዊ ሚዲያዎች ማሳወቁን ተከትሎ፤ መላው ሕብረተሰብ ተቃውሞውን እየገለፀ ይገኛል፡፡ ሕዝባችን ባለፉት ዘመናት ይዞት በቆየው ባህል፣ እምነትና ታሪኩ እንዲህ ዓይነት አስነዋሪ ድርጊቶችን አምርሮ የሚጠላ ከመሆኑ አኳያ፣ የሕዝብ ስሜት እንዲህ መጋሉ ብዙም አያስገርምም ማለት ይቻላል፡፡

አስጎብኚ ድርጅቱና አባላቱ ይህችን ቅድስት ሀገር በምን መልክ እንደተረዷት መናገር ባይቻልም፣ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ዕውን እንደሆነ መግለጹን ቀጥለውበታል፡፡ በተለይም ሀሳባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት አለማግኘቱን ተከትሎ፣ በሰጡት መግለጫ "ምንም ዓይነት ተቃውሞ ቢገጥመን፣ ከኢትዮጵያ ጉብኝታችን አንቀርም" ብለዋል፡፡ ይሄ ዕብሪተኝነት የተቀላቀለበት አስተያየት፤ ከእምነትም፣ ከሰዋዊ እሳቤም ባፈነገጡ "ኃጢአን" ሰዎች የወጣ ነውና አባባሉ እምብዛም ባያስጨንቅም፣ ግብረ ሰዶማውያኑ ሌሎች አማራጮችን እንዳይጠቀሙ ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረጉ ግን ተገቢ መሆኑን ሳንገልፅ አናልፍም፡፡

በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት፤ ግብረሰዶም ተግባር ሲፈፀም የተገኘ፣ ወይም ለመፈፀም ሙከራ ያደረገ ሰው በሕግ እንደሚጠየቅና ከባድ ቅጣት እንደሚጣልበት ጭምር በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በርግጥ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ፤ በሀገራችን በተለይም ከ"መጤ ዘመናዊነቶች"፣ ከተለያየ የዓለም ክፍል በግብረሰናይ ድርጅት ስም በሚገቡ የውጭ ዜጎች አማካይነት፤ ግብረሰዶማዊነት ስር ሰዶ፣ የአባላቱ ቁጥር ጨምሯል ማለት ይቻላል፡፡ "ዘመቻ" በሚመስል መልኩ ከጥቂት ዓመታት በፊት በርካታ የጎዳና ህፃናትና ወጣቶች ተደጋጋሚ የግብረሰዶም ጥቃት እንደተፈፀመባቸውም የሚዘነጋ አይደለም፡፡

በመሀል ከተማይቱ የተለያዩ (አንዳንዶቹ መናፈሻና የቤ/ክርስቲያን የጀርባ ቦታዎችና የመቃብር ስፍራዎች ሲሆኑ) የግብረሰዶማውያን መዝናኛና መቀጣጠሪያ ናቸው ተብለው የሚታሙ ቦታዎች በዝተዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ግብረሰዶማውያን ቁጥራቸው ጨምሯል እየተባለ በሚተችበት፣ በዚህ ወቅት ነው የግብረሰዶማውያኑ አስጎብኚ ድርጅት አባላቱን ይዞ እንደሚመጣ ያሳወቀው፡፡ የጉዞው ሀሳብ በሕዝብም፣ በቤተ ክርስቲያናትም ሆነ በተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ከወዲሁ ተቀባይነት እንዳላገኘ ቢታወቅም፤ በሰይጣናዊ ተግባር የተሞሉት አባላት ይፋዊ ጉብኝታቸው ዕውን እንደማይሆን ሲያውቁ፣ ከተባለው ጊዜ በመቅደም ወይም በመዘግየት፣ በተናጠል ወደዚህች ሀገር ሊገቡ የሚችሉበት አጋጣሚ እንዳይከሰት፤ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ማንነት መሰረት በማድረግ፣ ያልተቋረጠ ቅድመ ጥንቃቄና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በርግጥ ይህ ከባድ ቢሆንም፣ ሀገራችን የምታጣውን ክብር ግምት ውስጥ በማስገባት፣ እግረ መንገድም የሚበላሸውን ትውልድና ባህል መሰረት በማድረግ፤ ግብረሰዶማውያኑ የጉዞአችን መዳረሻ ነው እስካሉት ላሊበላ ድረስ ተገቢው ክትትልና ጥበቃ መደረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰይጣናዊ ድርጅቶች፤ ሁሌም በየሀገሩ በሚገኙ አባሎቻቸው አማካይነት የመስፋፋትን ስራ የሚያከናውኑ እንደመሆናቸው መጠን፣ ሀገር ውስጥ በዚህን መሰል አጸያፊ ተግባር የተሰማሩ ሰዎች፣ (በተለይም በግብረሰዶማዊነት ከዚህ ቀደም ተጠርጥረው የተያዙ) ላይ አስፈላጊውን ምርመራ ማድረግ፤ የግብረሰናይ ድርጅቱን የህቡዕ ሀገራዊ መስመር ማቋረጥ፣ ብሎም ዕቅዱንም ማክሸፉ ላይ በጥልቀትም፣ በፍጥነትም መስራት ይኖርበታል፡፡ በመጨረሻም መንግስታችን ይህን የግብረ ሰዶማውያን ጉዞ በተመለከተ የማያወላዳ የአቋም መግለጫ በማውጣት፣ የሕዝባችንን እምነትና እሳቤ ለዓለም እንዲያሳውቅልን፤ በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
ፍቅርተ ተሾመ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
አሸናፊ ዘደቡብ


**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ
ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



# የዘውግ ፖለቲካ ምንነት

## ፕ/ር መሳይ ከበደ (ከአሜሪካ በተለይ ለግዮን መጽሔት)

የዶክተር ዐቢይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ መመረጥ; የለውጥ ተስፋና ጅምር እንዳመጣ ብዙ ኢትዮጵያውያን ያምናሉ። በተመሳሳይ ብዛትም ለውጡን ሊያደናቅፍ፣ አልፎም ሊያቆምና ወደ ከፋ ሁኔታ ሊወስድ የሚችል ከባድ እንቅፋት እንዳለ ይገነዘባሉ። እንቅፋቱ በአገሪቷ የሰፈነው የዘውግ ፖለቲካና አደረጃጀት መሆኑንም ይቀበላሉ። በመሆኑም በሥራ ያሉት ዘውጋዊ ደንቦችንና አሰራሮችን ማቆም ወይም ማሻሻል፤ ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን የለውጡን መቀጠልና መስፋት የሚወስን፣ አስፈላጊና አጣዳፊ እርምጃ ነው። ይህ ጽሁፍ፤ የሚፈለገው የማቆም ወይም የማሻሻል እርምጃ ስኬታማ የመሆን እድሉን ለማመዛዘን፣ በቅድሚያ የዘውግ ፓለቲካ ባሕርይና ፍላጎትን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል የሚል መርህ በመከተል የቀረበ ነው።

### ሶስት መላምቶች

የተወሰኑ ተመራማሪዎች የዘውግ ፖለቲካ መሰረታዊ ፍላጎት፤ የራስን እድል በራስ የመወሰንን መብት መቀናጀትና መተግበር ነው ይላሉ:: በእነሱ አመለካከት ዘውግ የደም፣ የዘር፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል የመሳሰሉ የማይለወጡ ወይም የሚወረሱ ትስስሮች ላይ ለተመሰረቱ ማህበራዊ መለያዎች ቅድሚያ የሚሰጥ፣ የማንነት ስሜታዊ የኅሊና ቅርጽ ነው:: ዘውጋዊ ትስስሮች ተፈጥሮአዊና ስሜታዊ ግፊት ስላሏቸው ከመደባዊ ክፍፍሎች በላቀ መንገድ መሰረታዊና ተቀዳሚ ናቸው:: እንዲህ የመሰለ ስሜታዊ የኅሊና ቅርጽ፤ የተወደዱትን መለያዎች ለመጠበቅና ለማሳደግ የሚያስችለውን ፖለቲካዊ ሉአላዊነት እጅግ ይመኛል:: በመሆኑም እንደ ተመራማሪዎቹ አመለካከት፣ የዘውግ ግጭቶችን ማቆም የሚቻለው ህዝቦች በሚመርጡት መንግስት ሥር፣ እስከመገንጠልም ድረስ ቢሆን፣ እንዲተዳደሩ በመቀበል ብቻ ነው:: በማንነት ፖለቲካ የተቀሰቀሱ ሕዝቦችን በግድ ባለው መንግስት ሥር ለማቆየት መሞከር ዘውጋዊ ግጭቶችን ያባብሳል፤ ከዚህም አልፎ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ይወስዳል::

ይህን ትንታኔ የማይቀበሉ ተመራማሪዎች ደግሞ፤ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ላይ ተመርኩዞ ፖለቲካዊ ድንበሮችን እንደገና መቅርጽ፤ ብዙውን ጊዜ ዴሞክራሲን አያስገኝም፣ ግጭቶችንም በሰላም አያቆምም ይላሉ:: ለዚህ የኢትዮጵያ ምሳሌ በቂ ማስረጃ ነው:: የኤርትራ መገንጠል ለኤርትራውያን ዴሞክራሲንም፣ ሰላምንም አላስገኘም:: በሕወሓት የተቀረጸው ዘውጋዊ ፌዴራሊዝም ዴሞክራሲንም ሆነ ሰላምን በማምጣት ረገድ የተለየ ውጤት አላስገኘም:: ሃቁ ከተፈለገ፣ እንደ ዘውግ ውስንና ግትር እምነት ላይ የተመሰረተ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለሚጠይቀው ልምጥምጥነት ቦታ የለውም:: ለምን የዘውግ ፖለቲካ እነዚህን ጠባዮች ያሳያል? ብለን ስንጠይቅ ነው እውን ባሕርይውን የምናገኘው::

ዘውጋዊ ማንነት የመለየትና የማጻረር ጠባይ አለው:: ይህ ጠባይ ለፖለቲካ ትግል ካልሆነ ለምን ይበጃል? በመሆኑም ዘውግ ለመንግስት ሥልጣንና ለማህበራዊ በላይነት የሚፎካከሩ ልሂቃኖች የሚቀምሙት የትግል መሳሪያ ነው:: ዘውግ ተፈጥሮአዊ ከመሆን ይልቅ ማህበራዊ አለመመጣጠኖችና በደሎች ከሚፈጥሯቸው ቅሬታዎች የሚመነጭ የትግል ስልት ነው:: አሰራሩም ግልጽ ነው:: የበላይ የሆነው ዘውግ ባሉት የመልክ፣ የቋንቋ፣ የባህል ወዘተ መለያዎች በመጠቀም ሌላውን ያገላል፤ የበታች የሆነው ዘውግ በበኩሉ ያሉትን መለያዎች በማስመርና በእነሱ ዙሪያ በመደራጀት አንድነቱ ይጠናከራል:: የበታችነቱን ለማስቀረት ይታገላል:: ስለሆነም የመጀመሪያው መላምት እንዳለው፣ ዘውግ ከተፈጥሮ የሚመነጭ ሥነ ሕይወታዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ግፊት አይደለም:: የተዛቡ ማህበራዊ ግንኙነቶች ውጤት በመሆኑ ►

በአመዛኙ የተፈበረከ ነው፡፡

በተለይም፣ የዘውግ ፖለቲካ የተገለሉ ማህበርሰቦች ልሂቃኖች ፤ለሥልጣን ለመፎካከር "በማንነታችን የልዩ ጭቆና ኢላማ ሆነናል" በማለት መሰል መለያ ያለውን ሕዝብ ለማሰባሰብና ለማንቀሳቀስ የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው፡፡ ዘውግ ከፖለቲካ ትግል ጋር ያለውን ግንኙነት ማስመር፣ የዘውጋዊ ግጭቶች መንሳኤ የባህል ወይ የዘር አለመጣጣም እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ የፖለቲካ ፉክክር መሆኑን መቀበል ደግሞ ወደ መፍትሄ ይወስደናል፡፡ ችግር የሚመጣው ከመገለል በመሆኑ ያልተማከለና ሥልጣን የሚያጋራ መንግስት የሚመሰርት ፖለቲካዊ ስምምነት ላይ ቢደረስ ዘውጋዊ ግጭት ሰላማዊ መፍትሄ ያገኛል፡፡

ዘውጋዊ ማንነት የልሂቃኖች መጠቀሚያ ነው የሚለው ድምዳሜ ዋና ድክመት አለው፤ የማንነቱን ከፍተኛ ስሜታዊ ኃይል ያሳንሳል፣ በዚህም የተነሳ ወደ ኃይላዊ ግጭት የመውሰድ ዝንባሌውን አያብራራም፡፡ ትንታኔው የማንነትን ፖለቲካ ከምክንያታዊ ስሌት ጋር ስለሚያዋህድ ለምን ሰፊው ህዝብ የልሂቃኑን ስሌት በከፍተኛ ስሜት ይከተላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የለውም፡፡ የማንነት ፖለቲካ ሰፊ ድጋፍ ለማግኘት የሚችለው የልሂቃን ጥቅም በተወሰነ ደረጃ የህዝብን የልብ ትርታ ሲነካ ነው፡፡ ይህን ድክመት ለማረም ነው ዘውጋዊ ንግግር፣ የአዲስ ማንነት ፈጠራ ነው የሚለው ሶስተኛ መላምት ብቅ ያለው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ የተገለሉ ልሂቃኖች እጅግ የሚያስጎመጅ ባሕሪይ ያለው ማህበረሰብ በሃሳብ በመቅረጽ እንወክላን የሚሉትን ሕዝብ ለማነሳሳት ይጥራሉ ይላል፡፡

> ...ዘውግ ከመደብ አንድነት ይልቅ ወገናዊ አጋርነትን ስለሚያሰምር ከሕዝቡ ጋር ዘውጋዊ አንድነት ያለው የልሂቃን አገዛዝ ብቻ ሕጋዊና ተስማሚ ያደርጋል። ከዚህ ውጪ የሆነ መንግሥት የባእድ ሥርአት በመሆኑ፣ በመሰረቱ አድላዊና ጨቋኝ ከመሆን ሊያመልጥ አይችልም ይላል...

ማህበራዊ ግኑኝቶችን ይጠይቃል፡፡

ዘውግ የተወሰነ ታሪክ ውጤት እንጂ ተፈጥሮአዊ አይደለም ማለት፣ የፖለቲካ ይዘቱን አጉልቶ የሚያሳየን ዘውግ መሳሪያ ነው ወደሚለው አመለካከት ይወስደናል፡፡ ዘውጋዊ ማንነት መለያ ብቻ ሳይሆን አንድን ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ የሚያገልልና የሚያቃርን መሆኑ ፖለቲካዊ ግቡን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም በሕዝቦች መካከል ምንም ተፈጥሮአዊ ቅራኔ ስለሌለ ዘውጋዊ ማንነት በአንድ አድሎአዊ ፖለቲካዊ አገዛዝ ሥር ካሉ ማህበራዊ ግኑኙነቶች የሚመነጭ ተቃውሞ ወይም የበላይነት መግለጫ ነው፡፡ የሕዝቦች እጥ ተመሳሳይ በመሆኑ ሊቃወም ወይም የበላይ ልሁን እያለ የፖለቲካ ትግል ውስጥ የሚገባው ያው የልሂቃኖች የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ የመገንጠልን ፍላጎት ብንወስድ እንኳን ብዙውን ጊዜ የምናገኘው እንደ ቋንቋ በመሰለ ዘውጋዊ መለያ ዙሪያ የሚሰባሰቡ ልሂቃኖች፤ ሌላ ተፎካካሪ እንዳይኖር የሚያደርግላቸውን የተከለለ ግዛት የመቅረጽ እቅድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዘውጋዊ ፌዴራሊዝም አንዱ ግብ ኦሮሚያን ለኦሮሞ ልሂቃኖች ብቻ፣ ትግራይን ለትግሬ ልሂቃኖች ብቻ ወዘተ መከለል ነው፡፡ እንዲሁም ለምን የዘውግ ፖለቲካ የኦሮሞና የትግራይ ልሂቃኖች ዘንድ እጅግ ይከራል? በለን ብንጠይቅ የበላይነት ፍላጎት ሁለቱምጋ እንደ ዓላማ በመወሰዱ ነው የሚል መልስ ይጠብቀናል፡፡ ዘውጋዊ አመለካከትን ለአንድ ባሕልና ማንነት ታማኝነት ባሻገር ፖለቲካዊ ግብ አለው ካልን፣ ከልሂቃኖች የፖለቲካ ፉክክር ልንለየው አንችልም፡፡

መመሳሰል ወይም የተወሰኑ መለያዎችን መጋራት ያቀራርባል፤ የዝምድና ስሜት ላይ የተመሰርተ፣ የመተማመንና የመተሳሰብ ስሜት ያፈልቃል፡፡ ይህ ደግሞ ዘውጋዊ ርእዮተ ዓለምን የሚያራምዱ ልሂቃኖች እንደ ወገን ወይም ዘመድ እንዲታዩ ስለሚያደርግ፤ ከሕዝቡ ጋር ስሜታዊ ትስስር ይፈጥራል፡፡ በወገኔ ነጻ አውጪነት ከአስከፊ ሁኔታ እላቀቃለሁ የሚል ምናባዊ (imaginary) ተስፋ ስለሚቀሰቅስ ነው ይህ የተፈበረከ ማንነት ኃይል አግኝቶ ሕዝብን የሚያንቀሳቅሰው፡፡

ምናባዊ የተባለበት ምክንያት በዘውግ አንድነት ላይ ስለተመሰርተ፣ አንድ ህብረተሰብ እኩልነትና ፍትህን ሲያነግስ ታይቶ ስለማይታወቅ ነው፡፡ ለዚህም የቅርብ ማስረጃ የኢትዮጵያ ዘውጋዊ ክልሎች የእኩልነት መፈንጫ ከመሆን እጅግ የራቁ መሆናቸውን መመልከት ይበቃል፡፡ በመሆኑም ዘውግ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን የሰው ፈጠራ ችሎታ የሚወልደው ታሪካዊ፣ ውስብስብና ተለዋዋጭ የማንቀሳቀሺያ እምነት ነው፡፡ እንዲሁም ዘውግ የተነቃቃ፣ ቀደም ብሎ የነበረ ማንነት ሳይሆን አዲስ የተፈጠረ ማንነት ነው፡፡

## የሶስቱ መላምቶች አስተጻምሮ

ዘውግ ተፈጥሮአዊ መሰረት ያለው ዐቢይ መለያ ነው የሚለው ንድፈሐሳብ በትክክል የሚያስተምረን ሙሉ በሙሉ ምክንያታዊ ያልሆነና ኃይለኛ ስሜቶችን የሚቀሰቅስ ግፊት እንደሆነ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ነው የሚለው እምነት የንድፈ ሃሳቡ ደካማ ጎኑ ቢሆንም፣ ኃይለኛ ስሜቶችን እንደሚያስነሳ ማስመሩ ለዘውጋዊ ግጭቶች ተመጣጣኝ መፍትሄ እንድንፈልግ ያደርገናል፡፡ የዘውግ ፖለቲካን መናቅ ወይም ፍላጎቱን በትክክል አለመረዳት፣ በበርካታ አገሮች ታሪክ እንደታየው፣ ብዙ የሚያስከፈል ስህተት ውስጥ ይከታል፡፡ "የዘውግ ፌደራሊዝም ይከልከል" እያሉ የሚጠይቁ ፖለቲካዊ ፓርቲዎችና አክቲቪስቶች የሚዘነጉት ይህ የዘውግን ስሜታዊ ኃይል ነው፡፡ ለምሳሌ የመገንጠል ፍላጎት እንደ ኢኮኖሚ በመሰለ ምክንያታዊ ጥቅም ጋር ቢጋጭም፤ በስሜት ኃይል ብቻ እውን ሊሆን ይችላል፡፡ ኃይል አለው ማለት ግን ተፈጥሮአዊ ነው ማለት አይደለም፡፡ ዘውግ ፖለቲካዊ ይዘት አለው ካልን ተፈጥሮአዊ ወይም መሰረታዊ ከማድረግ ጋር አብሮ አይሄድም፤ ምክንያቱም ፖለቲካዊ ለመሆን የተወሰነ ከታሪክ የመነጨ የተዛባ

ይህ ሁሉ ትክክል ቢሆንም ከላይ እንደተጠቀሰው ዘውግ መሳሪያ ነው የሚለው ንድፈ ሃሳብ እነዚህ የተቆመላቸው ዘውጋዊ መለያዎች ለምን ለፖለቲካ ግብ ሕዝብን ሳይቀር አንቀሳቃሽ መሆን ቻሉ? ለሚለው ጥያቄ መልስ አይሰጥም፡፡ እንዴት ዘውግ ሕዝቦችን የሚለይ ብቻ ሳይሆን በመብትና በማህበራዊ ደረጃና ሥልጣን ረገድ የሚያጻርርና የሚያበላልጥ ሆነ?፣ ከቀድሞ የተወረሰው ባህል የማጋጨትና የማበላለጥ ፍች አልነበረውም፡፡ በእርግጥ ማንነትን ይገልጽ ነበር፣ ነገር ግን የፖለቲካ ውድድር መሳሪያ አልነበርም፡፡ መሳሪያ ሊሆን የሚችለው በአዲስ መልክ ሲቀረጽ ብቻ ስለሆነ ነው ሶስተኛው መላምት ዘውጋዊ እሳቤ ፈጠራን ያካትታል ያለው፡፡

ሊካድ የማይቻለው ባህላዊ ማንነት፣ ስሜታዊ አሳቢነት በሚያመነጭ በአዲስ መልክ ከተቀረጸ ጥቅምን ለማራመድ እጅግ ገቢራዊ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡ የድሮውን ዝም ብሎ መድገም ጠቀሜታ የለውም፡፡ ፈጠራ ሲታከልበት ግን አሁን ላሉት ችግሮችና ፍላጎቶች ተስማሚ የሆነውን ማንነት ይቀምራል፡፡ ለሥልጣን የሚታገሉ ልሂቃኖች ተደማጭነት አግኝተው፣ ፖለቲካዊ ክልሎችን ለመቅረጽ የሚችሉት የድሮውን እንደነበረ በማንሳት አይደለም፡፡ የድሮውን ከማሸብረቅ በለይ ለመጪው ብሩህ ተስፋ የሚሰጥ አመለካከት ሲፈጥሩ ነው፡፡ የደስታ፣የእኩልነት፣ የብልጽግና ዋስትና ሲኖረው ባህላዊ ማንነት ለፖለቲካ ዓላማ የሚያነሳሳ ይሆናል፡፡ ከላይ ተገልጿል፣ ለዚህ ተስፋ መሰረቱ ዘውግ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ወዘተ ላይ በመንተራስ የሚነድፈው ወገናዊነትና የጋሪዎሽነት ስሜት ነው፡፡ ስሜቱ የማርክሳዊ፣ ሌሊናዊ ሶሺያሊዝም ከፈጠረው የሰፊው ሠራተኛ ወንድማማችነትና መደጋገፍ ስሜት የተወረሰ ነው፡፡ ልዩነቱ የማርክሳዊ ሌሊናዊ ሶሺያሊዝም በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ሳይለይ ሁሉን የኢትዮጵያ፣ከዚያም አልፎ የዓለም ሠራተኞችን ሲያቅፍ፣ የዘውግ ወገናዊነት ግን ከመደብ አንድነት ሳይሆን ከሚለዩ ባህላዊ ማንነቶች የሚመነጭ መሆኑ ነው፡፡

ዘውግ የሚያበስረው ወገናዊ ግንኙቶች ከማርክሳዊ ሌሊናዊ ሶሺያሊዝም የተወረሰ መሆኑ የድሮውን በአዲስ መልክ የመቅረጽ ፈጠራ ውጤት መሆኑን ያሳያል፡፡ ዘውግ ከመደብ አንድነት ይልቅ ወገናዊ አጋርነትን ስለሚያሰምር ከሕዝቡ ጋር ዘውጋዊ አንድነት ያለው የልሂቃን አገዛዝ

ቀሪውን በገጽ 22 ይመልከቱ

# እንደበት



“የባለስልጣናት ንብረት በመመዝገብ ለውጥ ማግኘት ቢቻልም፣ ግልፅ፣ ቁጥጥር ያለበትና ጠንካራ የሆነ መንግስታዊ መዋቅርና አሰራር በመዘርጋት ሙስናን በእጅጉ መቀነስ ይቻላል:: የመሰረተ ልማት ተቋማት፣ የጉምሩክና ገቢዎች መስሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም፣ የመሬት አስተዳደርን በማጠናከር ችግሩን መቀነስ ይቻላል። በሁሉም መስሪያ ቤቶች ያለውን የአስተዳደር ሥርዓት በማዘመንና ግልፅ በማድረግ፣ የኦዲት ስርዓቱ እንዲጠነክር በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። በአጠቃላይ፣ የፖሊስ ክትትልን በማጠናከር ሙሰኞች የማይተማመኑበትን ድባብ መፍጠር ይቻላል፤ ሰጪም ተቀባይም እንያዛለን ብለው ከፈሩ ወደ ሙስና ተግባር ውስጥ አይገቡም። በተለይ የባለስልጣናትን እንቅስቃሴ በዓይነ ቁራኛ መከታተሉ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣም አምናለሁ”

*አቶ ቃሲም ቁፋ /የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር/*
*ኢትዮጲስ ጋዜጣ ግንቦት 25 ቀን 2011 ዓ.ም*



“ግንቦት ሀያ በተግባር ምንድን ነው? ስትል የክህደት ቀን ነው። ግንቦት ሀያ አብረው የሚኖሩ ዜጎች በመካከላቸው ጥላቻ መስፈን የጀመረበት፣ ዜጎች አብረው እያሉ እንዲለያዩ የተደረገበት፣ የአንድ ወገን የበላይነት እንዲሰፍን በሥርዓት ደረጃ የተዘረጋበት ዕለት ነው። አፓርታይድን በኢትዮጵያ በተግባር ያየንበት የመጀመሪያ ቀን ነው። ይሄንን አስፈሪ የታሪክ ገፅታ በተለያየ መንገድ መዘከር ይቻል ይሆናል። አንደኛ የዚህን አስፈሪ የታሪክ ገፅታ እያስታወስን ማለትም ልክ እንደ ጀርመኑ ናዚ በሌላው ላይ እንዳደረሰው አሰቃቂ ታሪክ በመዘከር፣ እንደ ቀይ ሽብር እልቂት ዘመን ያለፉት 27 ዓመታት ተመልሰው እንዳይመጡ እያስተማርን፣ ክፍተቱን እያሳየን ከዚያ ችግር የምወጣበትን መንገድ እያፈላለግን መሆን አለበት”

*አክቲቪስት ስዩም ተሾመ*
*ቦሌ ታይምስ ጋዜጣ ግንቦት 24 ቀን 2011 ዓ.ም*



“እኛ የመጀመሪያውን ተነሳሽነት ወስደን ደረጃውን የጠበቀ ማረሚያ ቤት መስራታችን፣ የሀገሪቱን የማረሚያ ቤቶች ሁኔታ ለመቀየር የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል። በሰብዓዊ መብት አጠባበቅና እስረኞች አያያዝ ላይም ስልጠናዎች ስንሰጥ ቆይተናል። እኛ በዋናነት ትኩረታችን ማረሚያ ቤቶች ላይ ነበር። በእርግጥም በሰራናቸው የማሰልጠን ስራዎች በማረሚያ ቤቶች የሰብዓዊ መብት አያያዝን ማሻሻል እንደቻልን አምናለሁ:: እንደሚታወቀው አብዛኛው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይፈፀም የነበረው ማረሚያ ቤት ሳይሆን በፖሊስ ጣቢያዎች ነበር። ማዕከላዊን መጥቀስ እንችላለን። እኛ በፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ብዙም አልሰራንም”

*ፓስተር ዳንኤል ገ/ስላሴ*
*አዲስ አድማስ ጋዜጣ ግንቦት 24 ቀን 2011 ዓ.ም*



“የአፍጥር ፕሮግራሙ ከዚህ በፊት ካየናቸው የመንግስት ባህሪያት የተለየ ነው። በሀገር ደረጃ ይህ ሲሆን የተለመደ አይደለም። ህዝበ ሙስሊሙ የእኔም ሀገር ነው የሚል ስሜት እንዲያድርበት፣ ለሀገሪቷም ሆነ ለእራሱ የተሻለ ማንነት አስተዋፅኦ እንዲያደርግ የሚገፋፋው ተግባር ነው። በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በባለቤትነትና በያገባኛል መንፈስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያዳበረ የሚሄድ ተሳትፎ እንዲደረግ የሚያስችል ከፍተኛ የመነቃቃት ስሜትንም ፈጥሯል”

*ሀጅ ከማል ሀሩን /የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የቦርድ ዋና ፀሐፊ/ አዲስ ልሳን ጋዜጣ ግንቦት 27 ቀን 2011 ዓ.ም*



“ከባድ የሆነው ዘረኝነቱ የተስፋፋው የፖለቲካ ችግር ወደኳሱ ስለመጣ ነው የዳኝነት ስህተትኮ የትኛውም አለም አለ.... አሁን ረብሻውን ያባባሰው የዳኝነት ስህተት ሳይሆን ዘረኝነቱ ነው የእኔ ዘር እንዴት ይሸነፋል ማለት መጀመሩ ነው አደጋው.... ይሄ አስተሳሰብ ነው መቅረት ያለበት የዘረኝነት ችግሩ የፖለቲካ ጣጣው መጀመሪያ መቅረት ያለበት አመራሩ ጋር ነው:: የአመራሩ ችግር ነው ወደ ደጋፊው የመጣው ኳሱ ችግር አለበት ብዬ አላምንም”

*ዘርአይ ሙሉ /የሲዳማ ቡና አሰልጣኝ/*
*ሀትሪክ ጋዜጣ ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም*

## ለጠቅላላ እውቀት

= ሳተርን የተባለችው ፕላኔት አካልዋ በእጅጉ የሳሳ ከመሆኑ የተነሳ በግዙፍ የውኃ አካል ላይ ብታርፍ ትንሳፈፋለች እንጂ አትሰምጥም።

= በናይል ወንዝ ውስጥ የሚገኙ ካትፊሽ ተብለው የሚጠሩ የዓሣ ዝርያዎች የሚዋኙት ከላይ ወደ ታች ቁልቁልና ከታች ወደ ላይ ሽቅብ ነው።

= በ2 አህጉር ውስጥ የምትገኝ ብቸኛዋ ርዕሰ መዲና የቱርኳ ኢስታምቡል ስትሆን ግማሽ ክፍሏ አውሮፓ ግማሽ ክፍሏ ደግሞ እስያ ውስጥ ይገኛል።

= ዓሣዎች የአይን ቆብ ስለሌላቸው ሲያንቀላፉም አይናቸው ክፍት ነው።

= በረሃ የማይገኝበት ብቸኛ አህጉር አውሮፓ ነው።

= ትልቁ ስጋ በል ዓሣ “ዘ ግሬት ዋይት ሻርክ” ይባላል።

## አባባል

- ጉብዝና በትምህርታችን ሳይሆን በህይወታችን ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ነው።
- አምላክ ሆይ ልቀይራቸው የማልችላቸውን ነገሮች እንድቀበል ትዕግስትን፣ መቀየር የምችላቸውን ደግሞ እንድቀይር ድፍረቱን ስጠኝ። የሁለቱ ልዩነት እንዲገባኝ ደግሞ ጥበብን።
- ሁላችንም እውነተኛ ጥበብን የምንላበሰው ስለ ህይወት፣ ስለ ራሳችንና በዙሪያችን ስላለው ነገር ያለን እውቀት እጅግ በጣም አናሳ እንደሆነ ስንረዳ ብቻ ነው።
- ትልቁ ነገር ያለንበት ቦታ ወይም ደረጃ ሳይሆን እየተጓዝን ያለንበት አቅጣጫ ነው።
- መልሶቹን በሙሉ ማወቅ አያስፈልግህም፤ ሁሉንም ለመጠየቅ የሚያስችል አቅም ያለው ሰው የለምና።
- አንድ ሻማ ሌላውን በመለኮስ የሚጎዳው ወይም የሚያጣው ነገር አይኖርም።
- ሰላም ከፈለክ የምትኖርበትን አለም ሳይሆን እራስህን ቀይር። የመሬትን ወለል በሙሉ በጨርቅ ለመሸፈን ከመሞከር ይልቅ፣ ነጠላ ጫማ ማድረጉ ይቀላልና።
- ትርጉም የሚሰጠው የምታውቀው ነገር ሳይሆን በምታውቀው ነገር የምትሰራው ስራ ነው።

## እቴጌ መነን በሬዲዮ

በዓለም ለሚገኙ ሴቶች ሁሉ ድምፃችንን ለማሰማት ዛሬ ማታ ምክንያት ስላገኘን እጅግ ደስ ብሎናል። በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የአጥቂነት ሥራ ሊደረግበት በሚዘጋጅበት ጊዜ ሰላምንና ነፃነትን ለማፅናናት የቆመው የአለም ሴቶች ማህበር ስለገለጠልን የጋለ ወዳጅነት አሳብ ጥልቅ ምስጋናችንን ስናቀርብላቸው ደስ ይለናል:: አሁን ለምናደርገው ቃል የሚያዳምጠው ሁሉ ትርጉሙ በቶሎ እንዲገባቸውና በመጠባበቅም ጊዜ እንዳይወስድባቸው አስበን እጅግ የተወደደች ልጃችን ፀሐይ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንድታነበው አድርገናል።

***ጳጉሜ 6 ቀን 1927 ዝክረ ነገር***



ፍቅርተ ተሾመ

# የመምህርነት ሙያን ወደ ቀደመ ክብሩ እንዴት እንመልሰው?

መምህርነት ሙያ ነው። ሙያነቱም በህሊና ላይ የተመሰረተ፣ ኃላፊነቱ የላቀ፤ ትውልድን የሚሰራ፣ ለሃገር ብቁ ዜጋን ሲያስረክብ ኃላፊነት የተጣለበት ሙያ ነው። አንድ መምህር በተማሪዎቹ ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ አንዳንዴ ወላጆቹ ከሚፈጥሩት የላቀ ነው። ማሳያ፤ ልጆች ወላጆቻቸውን እና መምህራኖቻቸውን በእውቀት ደረጃ ለንፅፅር የሚያቀርቡባቸው አጋጣሚዎች በእድሜ ከፍ ሲሉና ማመዛዘናቸው ሲልቅ ለማመጣጠን ካልቻሉ በቀር፤ መምህራን ለእነርሱ የእውቀትና የማስተዋል መነፅራቸው ናቸው። ጉዳዩ ጥናት እንደሚያስፈልገው ግልፅ ነው፤ ሆኖም ግን ህፃናት ልጆች ከወላጆች ጋር በቤት ውስጥ ለድርጊቶቻቸው የሚያወጡትን አቃቂር ማስተዋል በቂ ነው። ስህተቶችን ሁሉ "ሚስ" "ሚስተር" "ቲቸር" እንዲህ ብሏል፣ ስለዚህ አይደረግም! ይላሉ።ወላጆችም ቢሆኑ ለሚስ ነው የምናገረው፣ ለመምህርሽ ነው የምነግርልሽ እያሉ ልጆችን እንዲታዘዙ የሚያደርጉበት አጋጣሚ ብዙ ነው።

## የሙያ ነፃነት እና ኃላፊነት

መምህርነት ሙያው ነፃነትን የሚፈልግ ነው። ነፃነት እንደየአውዱ እንደሚለያየው ለመምህርነት የሚያስፈልጉት ነፃነቶች ከሌሎች ሙያዎች ይለያል። ብዙ ጊዜ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራን ከሚያነሷቸው ችግሮች ውስጥ የአስተዳደር እክል አንዱ ነው። አንድም የፖለቲከኛ ሹመኞች፣ ወዲህ የሙያ ክህሎታቸው እምብዛም የሆኑ አካላት ለአስተዳደር ይታጫሉ፣ ይሾማሉ። ይህ ሁኔታ መምህሩን ግዞተኛ ያደርገዋል። ለአንድ ሰዓት ቆሞ ማስተማር ከስምንት ሰዓት የጉልበት ስራ ጋር እንደሚስተካከል ይዘነጉና አላስፈላጊ ጫናዎችን መምህራን ላይ ይጭናሉ፤ አንድ ምክንያት ከሙያው ለመራቅ። መምህራን በግላቸው እንደሌላው ዜጋ ሁሉ የኑሮ ውድነት፣ የቤተሰብ ኃላፊነት እና ሌሎችም ጫናዎች አሉባቸው። ከሚያፈሱት አቅም እና ካለባቸው ድካም አንፃር የሚሰጣቸው ዋጋ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ እንዲያውም ለንፅፅር ካቀረብን መምህርነት የሙያዎች ሁሉ ቁንጮ ነው። ቢሆንም ግን የክፍያ እና የተለያዩ ሊከበሩ የሚገባቸው ጥቅማጥቅሞች ትኩረት ከማይሰጣቸው ሙያተኞች ዋነኞቹ ናቸው።

## የዩኒቨርሲቲ መምህራን ምን ይበሉ

በነገራችን ላይ የደሞዝ እና የመኖሪያ እንዲሁም የሙያ ክብር እንደውም በዩኒቨርሲቲ መምህራን ከዚህ በፊት አለመነሳቱ ግር ይላል። ምክንያቱም በአንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች ለመምህራን የሚከፈለው ደምወዝ ከአንድ ዩኒቨርሲቲ መምህር ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ አስቂኝ ነው። ዩኒቨርሲቲዎቻችን ለመምህራን የሚሰጡት ክብር በጣም በብዙ መልኩ ጥያቄን የሚያስነሳ መሆኑ በጉልህ የሚታይ ነው። የመምህራን ደምወዝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከ5000 ጀምሮ እስከ ፕሮፌሰሮች በ20000 ይደርሳል። ይህ እርከኑ ነው። አንድ መምህር በዩኒቨርሲቲ ሲቀጠር ደሞዙ 5000 ከሆነ በእውነት ይህ ሙያ የቀደሙ ክብሩ ወዴት አለ? ያስብላል። መምህራን እራሳቸውን በተለያየ የጥናት ስራዎች ይደጉማሉ፤ ለዚህም ሲባል ይመስላል ከከፍተኛ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ጋር በንፅፅር ያላቸው ነፃነት የተጠበቀ ሆኖ የምናገኘው።

## መምህራን በቀድሞ ጊዜ

በቀደሙት ጊዜያት የመምህርነት ሙያ ዋጋውን በመገንዘብ በእድገት በህብረት ወቅት በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ወደ መምህርነት ሙያ እንዲገቡ ይደረጋል፤ አሁን በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደሚደረገው ማለት ነው። ይሄ መምህርነትን ከሚያስከብሩ፣ ዋጋውንም ከሚያሳዩ ሁኔታዎች አንዱ ነው። አንድን ትውልድ ማጥፋትም ሆነ ማብቃት የሚችልን ይህን ሙያ የነበረ ክብሩን መመለስ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይም አይደለም። መምህርነት በቀደሙ ጊዜያት እንዴት እንደነበረ ሲታሰብ ዘላቂነት ቢኖረው ኖሮ የሚሰራውንና የሚገነባውን ትውልድ ማሰብ አጓጊ ነው። ሆኖም አልዘለቀም።

## መምህራን አሁን

አሁን ላይ መምህርነት አንዱ ክፍት የስራ መስክ ከሚታይባቸው መስኮች እንደ አንዱ ከመቆጠር ባለፈ የክህሎቱ፣ የተሰጥኦ፣ የብቃት፣ የስነ ምግባር እና ሌሎች ሊሟሉ እና ሊታዩ የሚገባቸው መለኪያዎች ተሸቀንጥረዋል። አሁን የተገኘውን መምህር ከመቅጠር ባለፈ አማራጭ እየጠፋ መጥቷል። ለብዙ አዲስ ተመራቂ ሙያተኞችም የስራ መፈለጊያ መሆኑ የአደባባይ እውነት ነው። ይህን ሙያ በፍቅር እና በኃላፊነት የሚያገለግሉትን በዚህ ውስጥ ለመፈረጅ ባይቻልም፤ አሁን ላይ ግን የሙያ ዘርፉ ክብሩ እና ዋጋው፣ እንዲሁም ኃላፊነቱ ከተዘነጋ ሰነባብቷል። አሁን መምህር ተብሎ መጠራት የሚያኮራ መሆኑ ቀርቶ የሚያሳፍር ሆኗል። መምህርነቱን በኩራት የሚናገር ጥቂት ነው። መምህር መሆን የስኬት እጦት ማሳያ ሆኖ መታየት መጀመሩ ፤ ሙያው ያለውን ክብር እና ገፅታ ቀይሮታል። ስለዚህ መምህርነት አሁን ላይ ተመራጭ የስራ መስክ አይደለም፤ መሸጋገሪያ እንጂ። የግል ትምህርት ቤቶች ያሉባቸውን የመምህራን እጥረት ተግዳሮት በተለያየ መንገድ ለመሸፈን ይሞክራሉ ፤በአማላይ የጥቅማ ጥቅም ቃሎች እና በብር ለመሸፈን ቢሞክሩም መንግስትም በበኩሉ የተለያዩ ቃል በተገቡ፣ እንዲሁም በተግባርም በሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች መምህራንን ለማ ማለል ይሞክራል። መንገዱ ለሙያው ፍቅር ያላቸውን መምህራን የማስቀረት አቅሙ አናሳ በመሆኑ እና ማታለያ ሆኖ ስለሚሰማቸው ሙያውን የሚወዱት ቢሆንም እንኳን ሳይወዱ በግድ እንዲሸሹ እና በሌላ መስክ እንዲሰማሩ፤ መለኪያዎቹን የማያሟሉ ምናልባት ለሌላ መስክ ብቁ ሆነው በመስካቸው ስራ ያጡ በመምህርነት እንዲገቡበት ይሆናል።

ታዲያ እነዚህ ሁሉ ድለላዎች እውነት ተፈላጊውን መምህር ለማግኘት ነው ወይስ ባለው የተጨማለቀ አካሄድ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ ለመቆየት ብቻ ነው? የሚለው በሁሉም የሙያ መስኮች ላይ እየታየ ያለውን ድንዛዜን ያሳያል። ችግሮችን ከስር መሰረታቸው ከመገንዘብ ይልቅ ላይ ላዩን፣ ጥቃቅኑን በመቀጨንብ ጊዚያዊ ነገሮችን መጠየቅ ለሀገርም ለራስም በግለሰብ ደረጃ ማለት ነው ዘላቂ መፍትሄን እንደማይሰጥ ግልፅ ነው።

## አሁን መምህራን ጥያቄያቸው ምንድነው?

በተለያዩ ሚዲያዎች እንደተዘገበው በሺዎች የሚቆጠሩ መምህራን የተለያዩ ጥያቄዎችን አንግበው ሰልፍ ወጥተዋል። ግላዊ ከሆኑ የጥቅማ ጥቅም ጥያቄዎች እስከ ትምህርት ጥራት ለመጠየቅ በአደባባይ ተገኝተውም ነበር። ይህንን እና መሰል ጥያቄዎች ሊጠይቁ እንደሚገባ ዲሞክራሲውም ይሁን በሃገር ላይ ያላቸው ሚና የሚፈቅድላቸው ነው። ግን ቁም ነገሩ ያለ ወንፊት እየተቀበልን ያለነው የሊበራሊዝም /የግለሰብ መብት/ ጉዳይ ማሳያ ሆነዋል። ሃገሪቷ የገባችበት ምስቅልቅል መዳኛዋ በዚህ ወቅት የህዝብ እና የመንግስት የተግባቦት ችግር ሆኖ ሳለ፤ በዚህ እና በዚያ እየፈነዱ ያሉትን የፍላጎት እና የችግር ጥሪዎች ማስተናገድ የሚችል የባለ 0 ካዝና መንግስትን መተንፈሻ ማሳጣት መፍትሄ ሳይሆን፣ ለሃገሪቷ መመሳቀል የራስን ድርሻ መወጣት፤ ጠጠር መጣል ይሆናል። ጥያቄው ባልከፋ፣ መልሱን በአግባቡ መጠበቅም ያሻል። ለዚህ ነው የሙያ ማህበራት አስፈላጊ የሚሆኑት፤ ጥያቄዎችን ስራዎች ሳይስተጓጎሉ፣ የችግር ገበናችን ለአደባባይ ሳይወጣ በሙያው ላይ ያሉ ጥያቄዎችን አልፎ ተርፎም ሙያዊ አስተዋፅኦዎችን፣ ተወካይ ሆኖ ከማንኛውም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነትና ተፅዕኖ በመፍጠር ለውጥን በቀላሉ ማምጣት ማስቻል የሚኖርበት።

መምህራን ብቁ ባለመሆናቸው ብቁ ዜጋ ማምረት እንዳይቻል ዋነኛው ተግዳሮት ነው። በተጨማሪም የተማረ የሰው ሃይል መኖሩ እንደ ኢትዮጵያ አይነት በርካታ የህዝብ ቁጥር እና የገጠር ነዋሪ ባለበት ሃገር ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት። ለምሳሌ ያክል ግብፅን ማየት ይቻላል ግብፅ ከቱሪዝም ቀጥሎ ከፍተኛ ገቢ ከሚያስገኙላት ነገሮች አንዱ የተማረ የሰው ሃይል አቅርቦቷ ነው። ግብፅ ከአፍሪካ ከፍተኛ ማንበብ እና መፃፍ የሚችሉ ዜጎች ያሉባት ሃገር ስትሆን ዜጎቿ ጥሩ የንባብ እና የእውቀት ቃርሚያ ልምድ እንዳላቸው ይነገራል። ከዚህ ባለፈም ሙያተኞችን በብቃት በማፍራትም በዜጎቿ ገቢ ታስገባለች። በዚህ ላይ መምህራን ብቁ ባለመሆናቸው ብቁ የሆኑ ዜጎችን በማፍራት ትውልድ ከማሰናከል ባለፈ የሃገር ተስፋ መቅጨት ይሆናል፤ ምክንያቱም ዘመኑ በሉዓላዊነት ሂደት ውስጥ ሃገራት በመረጃና የእውቀት ክምችት ፉክክር ቀን ከሌት የምትደክምበት በመሆኑ፤ ተገዳዳሪ ለመሆን እሱም ቀርቶ እየሆነ ያለውን ለማወቅ እንኳን ብቃቱ የሚገኘው በትምህርት ነውና።



አሸናፊ ዘ-ደቡብ

# ቀመረ ከዋክብት - ሐሳበ ጠቢባን ወጠባባት

“የደም ቧንቧ ኦፕራሲዮን ሲደረግላቸው ለግንዛቤ በሚያስቸግር አኳኋን ደም የሚያፈታባቸው ሕሙማን ያጋጥማሉ፡፡ ምክንያቱን ልረዳ የቻልኩት በቅርቡ ነው” ሲሉ ዶክተር ፒተር ሽላይሸር የሰጡት ቃል ይጠቀሳል፡፡

የቀዶ ሕክምና ተግባር ሲከናወን በብዛት ደም እየፈታ የሚያስቸግርበት ምክንያት ምን ይሆን? ተጠባቢው ፒተር ሽላይሸር “በቅርብ የተረዱትስ ምክንያት” ስለ ምንድን ነው? ዝርዝር ጉዳዩን በኋላ እመለስበታለሁ፡፡

በአያሌ የባሕር ማዶ መጽሔቶችና ጋዜጦች ላይ ስለ ሐሳበ ከዋክብት (አስትሮሎጂ) ተጽፎ እናገኛለን፡፡ “መጻፍ” ሲባልም የሐሳበ ከዋክብትን (የቀመረ -ከዋክብትን) ምንነት “መግለጽ” ማለት አይደለም፡፡ የሰውን ዕለተ - ልደት ተመርኩዘው ተጠባቢዎቹ ቀማርያነ ከዋክብት (አስትሮሎጂስቶች) ያ ግለሰብ በዚያን ወቅት (በአንድ የሆነ ሳምንት ወይም ወር) ሊያገኝና ሊያጣ የሚችለውን ይነግራሉ፡፡ ኮከብን ከዕለተ ልደት አዛምዶ፣ ዕድል ፈንታን መተንበይ የቱን ያህል በተጨባጭ ሊያረጋግጥ እንደሚበቃ በእጅጉ የሚያከራክር መሆኑ ባያጠራጥርም “ፍኖተ ሐሳበ ከዋክብት” እየተባለ በውጭ ሀገር መጽሔቶች፤ በተለይም በምዕራቡ አህጉር/በአእማድ ሠፍሮ፣ በሰንጠረዥ ተሞሽሮ እናያለን፡፡

ለምሳሌ በጎርጎሪዮሳዊው ቀመር ከሐምሌ 23 እስከ ነሐሴ 23 ባሉት ዕለታት መሐከል የተወለደ ሰው በ”አንበሳ” ይመሰላል፡፡ በየካቲት 20 እና በመጋቢት 20 ባለው ጊዜ ከእናቱ ማኅፀን የወጣው ደግሞ “ዓሣ” ይባላል፡፡ የቀመረ ከዋክብት ጠቢባንና ጠባባትም ከዚህ ተነሥተው፤ ቀምረውና ደምረው፣ ከወቅት አገናዝበው ይተነብያሉ፡፡ ትንቢቱ ያዘ ወይም አልያዘ የሚጠይቅ ግን ብዙም የለም፡፡ የዚህ ትንበያ ሳይንሳዊነት በብርቱ ያጠራጠራቸው አንድ የመጽሔት አንባቢ የጻፉትም ለጥቅስ የሚበቃ ነው፡፡ ይኸውም “ሥራ አይቀናህም በተባልኩ ጊዜ ቀንቶኝ ይዘሃል ተብሎ ሲነገረኝ ተበላሽቶብኝ አግኝቼዋለሁ” ያለው ነው፡፡ “ይኸ አስትሮሎጂ እንደ እንቆቅልሽ ለፌዝ ከሚውል በቀር፤ ለቁም ነገር የሚያስቡት አይደለም” ያሉትም ሊጠቀስ ይገባዋል፡፡

ይሁንና በየሳምንቱ በሚታተሙት ጋዜጦችና መጽሔቶች ፣በየዕለቱ በሚወጡትም ጭምር የሐሳበ-ከዋክብት ሠንጠረዥ መታየቱ አልቀረም፡፡ ምናልባት ዕንቆቅልሽም ቢሆን ጥቂት ፈገግ ማድረጉ አይቀርምና ኅትመቱ ለዚህ ብቻ ይመስላል “ለቀልድ፣ ለጨዋታ፣ ለሳቅ .... ብቻ” የሚለው፡፡

በዚህች በኢትዮጵያችንም ቀማርያን የሉም ለማለት አይቻልም፡፡ እንደ ወዲያኛው ዓለም ሕዝብ “አስትሮሎጂስቶች” ባይባሉም ጠንቋዮች ከጥንት ጀምሮ የሰውን ዕጣ ፈንታ ሲተነብዩ መኖራቸውን እናውቃለን፡፡ የትንቢታቸው አማንያን ዛሬ ምን ያህል እንደሆኑ አኃዛዊ ማረጋገጫ መስጠት ያዳግታል እንጂ፤ አሁንም ቢሆን “ስም”፣ የእናት ስም ፣ የአባት ስም፣ መዓልት፣ አውራኅ፣ ዓመተ ዓለም ፣ ዓመተ ምሕረት፣ ወንጌላዊ.......›› ብለው፤ “አጽፈ ወርኅ ሐራ ዘመን” የሚያስቀምሩ፣ የዕድል ፈንታ መዘርዝር የሚቆጥሩ፣ የሚያስቆጥሩ እንዳሉ አንክድም፡፡ እንደቀመሩ “አሰድ፣ ሚዛን፣ ሐመል፣ ገውዝ፣ ቀውስ፣ ወዘተ” እያሉ ይሰይማሉ፡፡

ጋብቻ ሲፈልጉ፣ ለክርክር ሲነሡ፣ መንገድ ሲያስቡ መጀመሪያ ጠንቋይ መጠየቅ ያለባቸው ኋላቀሮች ዛሬም አልፎ አልፎ በከተማ ይስተዋላሉ፡፡ በገጠር እንዲያውም “ጥንት እንደነበር...” ለማለት ሳያስደፍር አይቀርም፡፡ ባሕር ማዶኞች በጥበብ በመራቀቃቸው፣ በዕውቀት በመበልጸጋቸው በመጽሔትና በጋዜጣ ሠፍሮ የሚያገኙትን ንድፈ ሐሳበ ከዋክብት (ሆሮስኮፕ) እንደ “ቀልድ” ከማየትና ለፈገግታ፣ ለሳቅና ለጨዋታ ከመጠቀም በቀር ልዩ ትርጓሜ አይሰጡም፡፡ ብዙኃኑ አንባብያን በሐሳባዊ ምኞት ታሥረው፣ ሕይወታቸውን በባዶ ተስፋ እየመሩ መኖርን አይመርጡምና፡፡ በሀገራችን ግን የባህል ዕድገት ጉዞው ገና ረዥም ጉዳይ ስለሚቀረው የገድ እምነት፣ የጠንቋዮች ትንቢት ሙሉ በሙሉ የሚያጠፉበትን ጊዜ በናፍቆት እንጠብቃለን፡፡ እንደነዚያ “የፌዝ አንባብያን” (እንደ ፈረንጆች) ለሳቅ፣ ለጨዋታ ብቻ እያየን “እንዲህ ነበር” የምንልበትን ሰዓት ለማየት ብዙዎቻችን እንሻለን፡፡ ሆኖም በዛሬም ጊዜ ወደ ኋላ እየተመለስን፣ የቀድሞውን እየከለስን የምንገኝበት ወቅት ያለመጥፋቱ ጥቂት የሚያስገርም ነው፡፡

ለዚህ ጽሑፍ መግቢያ ያደረግሁት “የደም ቧንቧ ኦፕራሲዮን” ጉዳዩ ከአስትሮሎጂው ንድፈ ሐሳብ ወይም ከቀማርያኑ ሐሳበ ኅሊና ጋር ሙሉ በሙሉ የተዛመደ ነው ባይባልም ጥቂት ይቀራረባል፡፡

ጀርመናዊው ዶክተር ሽላይሸር ቀዶ ሕክምና ሲደረግላቸው ደም ስለሚያፈታባቸው ሕሙማን የጻፉት ሊቃውንትን ለትኩስ ፍተሻ የሚያሳናዳ መሆኑ በአንድ ወቅት ተነግሮ ነበር፡፡

በዶክተር ሽላይሸር ፍተሻ ሰነድ መሠረት “የደም ቧንቧ ኦፔራሲዮን ሲካሄድ ፣ ደም የሚያፈታው በተቀዶ ታካሚው በሽተኛ ሥነ ሕይወታዊ ጉስቁልና ሳቢያ ነው” ለማለት አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ይላሉ ዶክተሩ “እኛ በዚህ ክፍለ ዘመን የምንገኝ የሕክምና ጠቢባን-ጠባባት ሳንገነዘብ የኖርነውና በቅርቡ ልንረዳ የቻልነው አንድ ዓቢይ ነጥብ አለ፡፡ የደም ቧንቧ ኦፕራሲዮንም ሆነ ሌላ የቀዶ ሕክምና ተግባር በሚከናወንበት ሰዓት፤ ደም የሚያፈታባቸው ታካሚዎች ሲያጋጥሙን የክስተቱን መንስኤ በውል አናውቅም ነበር፡፡ ከራሳቸው ከሕሙማን ሥነ አካላዊ ጉድለት አንፃር ብቻ እየተመለከትን መፍትሔ ሳናገኝለት ቆይተናል፡፡”

የዶክተሩ ጥናታዊ ሰነድ እንደጠቆመው በሙሉ ጨረቃ የሚደረግ ቀዶ ሕክምና ደም ማፍታት ዐቢይ ምክንያት ነው፡፡ ምንም እንኳ ተቀዶ ታካሚዎች ደም የሚያፈታባቸው “በዚህ ምክንያት ብቻ ነው” ብለው ለመመስከር እንደሚቸገሩ ባይሸሽጉም፤ ለደም ማፍታት አደጋ አጋላጭ የሆነውና አደጋውንም ከፍ ሊያደርገው የሚችለው ሙሉ ጨረቃ መሆኑን በማስረጃ አስደግፈው አቅርበዋል፡፡ ምሁሩ በአስረጅነት ያቀረቡትን፣ በየጊዜው በሙሉ ጨረቃ የተካሄደውን የቀዶ ሕክምና ተግባር ሲሆን “ደም ያፈታባቸውን ታካሚዎች ስቆጥር፣ ዕለቱንና ሰዓቱን ስመዘግብ፣ በመቆየቴ የሙሉ ጨረቃን ተጽእኖ ለማረጋገጥ በቅቻለሁ” ሲሉ አስምረውበታል፡፡

“በጨረቃ ስሕበት የሚከሰተውን ማዕበለ-ባሕር እናውቃለን፣ እናጸድቃለን፡፡ በጨረቃ ስሕበት የሚደርስ ማዕበለ- አካል መኖሩን ግን አናውቅም፤ ወይም እያወቅን እንንቃለን፡፡” በማለት ጥናታዊውን ሰነድ አደባባይ ያወጡት ዶክተር ምርምራቸው ሊቀር የሚችል ከሆነ፤ በሙሉ ጨረቃ በሚካሄድ ከባድ የቀዶ ሕክምና ተግባር ላይ ሊቃውንት ማዕቀባቸውን እንዲያደነድኑ በአደራ ጭምር ነው የተማጸኑት፡፡ እስከ አሁን ድረስ ግን የማዕቀቡም ሆነ የይሁንታው ውሳኔ አደባባይ ወጥቶ በተግባር ሲውል አልታየም፡፡

የዶክተር ሽላይሸር የፍተሻ ወረቀት ጥልቅ ምርምር የሚያሻው መሆኑን ሊቃውንት አልደበቁም፡፡ ይሁንና አዲስ የምርምር ምዕራፍ ሊከፍት መብቃቱን የተጠራጠሩ የሉም፡፡ ደምና ጨረቃ የተቆራኙበትን ሳይንሳዊ ሐረግ በቅድሚያ መተንተን ፣ ማስተንተን አለባቸውና፡፡



# “ሃይማኖትና ብሔርን መሰረት ያደረጉ፣ ባንኮችን ማበረታት ትልቅ ስሕተት ነው”

## አቶ ክቡር ገና

**አ**ቶ ክቡር ገና በ1990ዎቹ መጀመሪያ የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት ፕሬዝዳንት በመሆን ሰርተዋል። በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ቢዝነስ ጉዳዮች ዙሪያ በሚሰጧቸው በሳል አስተያየቶችም በህዝብ ዘንድ በስፋት ይታወቃሉ። ላለፉት አስራ አራት ዓመታት ኢኒሼቲብ አፍሪካ በተሰኘ ድርጅት በትምህርት ዘርፍ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል። በቅርቡ አገር ውስጥ ሃይማኖታዊና ብሄር ተኮር ባንኮች በምስረታ ላይ መሆናቸውን አስመልክቶ የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ አነጋግሯቸው የሰጡትን ምላሽ እንዲህ ባለመልኩ አቅርቦታል።

**ግዮን፡- ለውይይታችን መንደርደሪያ እንዲሆን አሁን እየሰሩበት ያለውን ድርጅት ለአንባቢያን ቢገልፁልን?**

አቶ ክቡር፡- እኔ በአሁኑ ወቅት ኹለት ድርጅት ውስጥ ነው የምሰራው። አንደኛው ላለፉት አስራ አራት አመታት በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች በመሳተፍ፤ የትምህርት ውጤቶች ሊሻሻሉ የሚችሉበት ጥናቶች በማጥናት፤ ስራዎችን በመስራት፣ ወጣቶችን በመርዳት፣ መምህራንን በተለያየ የማሰልጠኛ ፕሮግራም እንዲሳተፉ በማድረግ፣ እየሰራንበት ያለው ድርጅት ኢንሼቲብ አፍሪካ ይባላል። በተለይም በሴት ተማሪዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡ ፡ ለምሳሌ በቅርቡ የሴት ተማሪዎች ውጤትን በተመለከተ፣ ትምህርቱ አንደኛና ሁለተኛ ክፍል ሲጀመር ቁጥራቸው ከወንዱ ቁጥር የማይተናነስ፣ እንደውም የሚበልጥበት ሁኔታ እያለ፤ ነገር ግን ክፍሎቹ እየጨመሩ በመጡ ቁጥር የሚወድቁትን ሴቶች እንዴት ነው ወደ ትምህርት የምንመልሳቸው? ለምንድንስ ነው? የሚወድቁት? በሚሉት ጉዳዮች፤ እንዲሁም የሚደርስባቸውን ጥቃቶች፣ የአቅምና የኢኮኖሚ ጉዳይ፣ አንዳንዴ ካሪኩለሙ ወይም መምህሩም ሴቶችን ለመርዳት፣ የበለጠ በትምህርታቸው የተሻለ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ዕውቀት ማነስም አንደኛው ችግር ስለሆነ፤ እነዚህን በማስወገድ ረገድ እየሰራን እንገኛለን።

ሌላኛው ድርጅት የፓን አፍሪካ ቼምበር ኦፍ ኮሜዞን ኢንዱስትሪ ይባላል። የአፍሪካ ንግድ ም/ቤቶች በተቻለ መጠን፣ በተለይ አሁን በተፈጠረው ነፃ ቀጠና ላይ የንግድ አባሎቻቸው በምን መልኩ ተጠናክረው እዚህ ውድድር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ? የሚለው ላይ የሚሰራ ድርጅት ነው፡ ፡ ከእሱ ጋር ሌሎች ፕሮግራሞች አሉ፤ ለምሳሌ በተቻለ መጠን የንግዱ ህብረተሰብ፣ ንግድ ላይ ያለ ተቋም ንግዱን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ያካሂዳል። ጉብኝት ሊሆን ይችላል፣ የአቅም ግንባታ ሊሆን ይችላል፣ እንዲህ ዓይነት ስራዎችን የሚያከናውን ተቋም ነው። እንግዲህ እነዚህ ኹለት ድርጅቶች ላይ ነው እየሰራሁ ያለሁት።

**ግዮን፡- በቅርቡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ባካሄዱት የአብሮነትና የኢፍጣር ፕሮግራም ላይ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ እስላማዊ ባንኮች እንዲከፈቱ መንግስት አስፈላጊውን ትብብር እንደሚያደርጉ ተናግረዋል። ሁኔታው በዚህ ወቅት ብዙ እያነጋገረ ከመሆኑ አኳያ፣ እርስዎ እንዴት ያዩታል?**

አቶ ክቡር፡- መነጋገሪያ ከሆነ እንግዲህ በጥሩ መልኩ መነጋገሪያ የሚሆን ርዕስ ይመስለኛል፡ ፡ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ሕዝቦቿ በብዛት ▶

ለማለት በሚያስችል መልኩ፣ በሁለት ዋና ዋና እምነቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። አንደኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን፣ ሁለተኛ የእስልምና እምነት። የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ በተለይ ከሃይማኖታቸው ጋር በተያያዘ የተለየ የባንክ አሰራር እንዳላቸው ይታወቃል።

ስለዚህ በመሰረቱ የውጭ ባንክ ይመጣል፣ አይመጣም የሚለው ጥያቄ እንደገባኝ ገና የተወሰነ ባይሆንም፤ አቅጣጫ ያሳዩ ይመስለኛል። ሀገሪቷ ለባንኮች ክፍት እንደምትሆንና የውጭ ባንኮች ሀገር ውስጥ ካሉ ባንኮች ጋር ተወዳድረው ስራ መስራት እንደሚችሉ፣ ከእነዚህ ውስጥም አንዳንድ ባንኮች የሙስሊም ባንኮች እንደሆኑ ነው እንግዲህ የሚነገረው።

በዛ መልኩ ካየነው፤ የሙስሊም ሳይሆን፣ የክርስቲያን ሳይሆን፣ ወይም ደግሞ ሃይማኖት የሌለው ባንክ ሳይሆን በአጠቃላይ የውጭ ባንኮች ኢትዮጵያ ውስጥ መምጣት የማያመጣው ነገር ወይም ደግሞ እንዴት አድርገው ነው መምጣት አለባቸው? የሚለው ላይ ማተኮሩ የተሻለ ይመስለኛል። ምክንያቱም ሀገሪቷ ከውጭ ሊገቡ የሚፈልጉት ባንኮች መረጣ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባት ነው የሚታየኝ። መረጣ ስንል፤ የአገሪቷ ልማት ላይ ትኩረት የሚሰጡ እንጂ፣ ከአገሪቷ ላይ ያለችውን ቅሪት ወደ አገራቸው በሚወስዱት ላይ ማተኮር ያለባት አይመስለኝም።

በዚህ መንፈስ የሚመጡ ባንኮች ካሉ የተሻለ ካፒታል ሊያመጡ ይችላሉ ብዬ ነው የምገምተው። ምንም እንኳን ይሄ ብዙ ጊዜ ግልፅም ባይሆን፣ በርግጥ አንዳንድ ጊዜ እንደዛም ላይሆን ይችላል፤ ግን ዞሮ ዞሮ ካፒ ታል ይዘው ይመጣሉ፣ የአገሪቷ ልማት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ ብለን ከወዲሁ እንገምት።

**ግዮን፡- ከአንድ ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ባንክ ይመሰረታል ተብሎ ነበር። ያን ጊዜ እንደውም እርስዎ ሰፋ ያለ አስተያየት ሰጥተው ነበር፡ ፡ እስኪ ይሄንን ጉዳይ ዳግም ወደ ኋላ መለስ ብለን እንመልከተው?**

አቶ ክቡር፡- የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምታቋቁመው ባንክን በወቅቱም ቢሆን አልደገፍኩትም። አሁንም አልደግፍም። ዛሬ ልዩነቱ ምንድን ነው? አንድ የሃይማኖት ድርጅት፣ ወይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፤ እንደ ቤተ ክርስቲያን ባንክ ማቋቋምና የእስልምና ተከታዮች የሆኑ ባንኮች ማቋቋም ደግሞ የተለያየ ነገር ነው።

እንደ ቤተ ክርስቲያን የሚቋቋመው ባንክ በእኔ አስተያየት የደከሙትን ለመርዳት፣ አቅማቸው ደክሞ የባንክ አካውንት መክፈት ያልቻሉ ወገኖች የባንክ አካውንት እንዲከፍቱና ሐብት ማጠራቀም እንዲችሉ ማድረግ ፣ እንደዚሁም ደግሞ ሌሎች ባንኮች ሊያበድሯቸው የማይፈልጉትን ቤተክርስቲያኗ ቤትም መስሪያ ይሁን፣ ሐብትን ለመፍጠር የሚደረጉ ንግዶች ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ካሉ እነሱን ለመርዳት ከሆነ የሚመሰረተው ብዙም አያከራክርም። ከዛ ውጭ እንዳሉት ባንኮች በየዓመቱ ለባንኩ ባለድርሻዎች ሰላሳ፣ አርባ በመቶ ትርፍ መስጠት ማለት ለእኔ ብዙም አይገባኝም። የአንድ ቤተ ክርስቲያን ስራም ይሄ ይሆናል ብዬ አልገምትም።

ከዚህ ሀሳብ በመነሳት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ባንክ አትክፈት ሳይሆን፣ የምትከፍተው ባንክ አቅም የሌላቸውን ለመደገፍ እስከሆነ ድረስ መበረታታት አለበት የሚል አቋም ነው ያለኝ።

**ግዮን፡- የሃይማኖት ተቋማት በቀጥታ የባንክ ስራ ውስጥ መግባታቸው ተገቢ ነው? በውጭ አገርስ እንደዚህ ዓይነት ልምዶች አሉ?**

አቶ ክቡር፡- ለምሳሌ ካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን ትልልቅ ባንኮች አሏቸው ከሚባሉ የሃይማኖት ድርጅቶች አንዷ ናት። አንዳንዴ የተለያዩ የማይሆኑ ስራዎች ውስጥ በመግባት ችግር ውስጥ የገባችበት ወቅት አለ፣ በባንኮቿ ትክክለኛ ያልሆነ አሰራር ምክንያት። እንዲህ ዓይነቱ የሃይማኖት ባንክ አዲስ ነገር አይደለም፡ ፡ ሌሎቹን አገራት ብንወስድ የሃይማኖት ተቋማት የከፈቷቸው ባንኮች አሉ። ግን ዋናው ነገር ሌሎቹ ስለከፈቱ እኛም እዚህ እንክፈት ማለት የለብንም።

እዚህ ሀገር መሆን ያለበት በእኔ አስተያየት በገለፅኩት መንገድ ሲሆን የተሻለ ነው ብዬ አምናለሁ። በነገራችን ላይ ቤተ ክርስቲያን ባንኩን የምትከፍተው ከምዕመናን በሰበሰበችው ገንዘብ እስከሆነ ድረስ፣ ለምዕመኗ በቂ ምላሽ መስጠት ይኖርባታል። ምዕመኗ ማለት አቅም ያለው ወይም ሼር ለመግዛት የቻለ ብቻ ሳይሆን፣ ጠቅላላ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ፣ ከዛም አልፎ የሌላ እምነት ተከታዮች ቢሆኑም በሯን መክፈት አለባት፤ ደካሞች እስከሆኑ ድረስ። የውጪዎቹ ስላደረጉ ብቻ እኛም ያንን ማድረግ አለብን የሚል አስተሳሰብ ግን መኖር የለበትም።

**ግዮን፡- የሃይማኖት ባንኮች ከተመሰረቱ ማህበረሰቡ "ይሄ የእኔ ዕምነት ነው፣ አይደለም" የሚል የመከፋፈልን ችግርን አይፈጥሩም?**

አቶ ክቡር፡- በመሰረቱ የሃይማኖት ባንክ የሚከፈተው ለእዚህም ነው። ተከታዮቻቸውን በሃይማኖትም፣ ይሁን በብሔር የሚመስላቸውን ለመርዳት፣ ለመጥቀም፣ ለማሳደግ ተብሎ ነው እነዚህ ባንኮች የሚከፈቱት። የሀገሪቷ የፖለቲካ መሰረቶች እየተናዱ ባሉበት፣ አንድነቷ እየተሸረሸረ ባለበት፣ብሔርተኝነት በተስፋፋበት በአሁኑ ወቅት፤ ሃይማኖትና ብሄርን መሰረት ያደረጉ እንደዚህ ዓይነት ባንኮችን ማበረታታቱ በጣም ትልቅ ስህተት ነው ።አያስፈልግምም።

በተወሰነ መልኩ እንደገለጽሁት እንዲህ ዓይነት ባንኮች የሚቋቋሙት የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ክልላቸው ላይ ልማት ለማምጣት፣ በማሰብ ነው። እንደሱ እስከሆነ ድረስ ደግሞ መንግስት ማበረታታት ያለበት፣ ክልላዊ ባንክ በዛው ክልል እንዲቋቋም በማድረግ ነው። ይሄኛው አሰራር ሃይማኖት ሳይል፣ ብሄር ሳይል ለክልሉ ልማት ብቻ ይሰራል። በአብዛኛው በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ብሄሮች አንድ ዓይነት ቢሆኑም፣ ነገር ግን ባንኩ በብሄር ሳይሆን የሚቋቋመው ክልሉን ለማሳደጊያ እስከሆነ ድረስ የበለጠ ተጠቃሚ፣ የበለጠ ደጋፊም ሊያገኝ ይችላል የሚል ዕምነት አለኝ።

በአሁኑ ወቅት አንዱን ከአንዱ ሊለያዩ የሚችሉ ድርጅቶችን መክፈት ወይም ማበረታታት፤ በእኔ አስተያየት ትክክል አይመስለኝም። አሁን ምን እየተደረገ ነው? ካልን በባንክ ሰበብ ፖለቲካ ያለ ፖለቲከኞች እየተሰራ ያለ ይመስለኛል፣ እሱን ማስቀረት መቻል አለብን። ይህ ካልሆነ ግን ከችግርና ከመከፋፈል ወጥተን ወደ አንድነት መምጣቱ ያዳግተናል።

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ባንኮች በብዛት ተቋቁመዋል። ይሄ ራሱ የመከፋፈል ስሜትን አያመጣም? በሰለጠነው ዓለምስ እንዲህ ዓይነት አሰራር ይኖር ይሆን? በባንክ አሰራር የሚቀድሙን አሉና ከእነሱ በመነሳት እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

አቶ ክቡር፡- እንግዲህ ባንክ ከንግድ ጋር የተያያዘ ነው። ነጋዴ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ከሚያምነው ጋር ይጣመራል። ይሄ ያለ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ነገር በውጭ ሀገርም እናያለን፤ ለምሳሌ እንግሊዝ ሀገር ውስጥ የጃማይካ ነዋሪዎች ባንክ አለ፣ የህንዶች፣ የፓኪስታኖች ባንክ አለ። እነዚህ በእዛ ሀገር ውስጥ አናሳ ብሄሮች ናቸው፡ ፡ በአናሳነታቸው ከዋናዎቹ ባንኮች ሊያገኙ የሚችሉትን ጥቅም ያነሰ ሊሆን ይችላል፡ ፡ በቋንቋ ወይም በአመለካከት ሲታዩ የሀገሩ ሰዎች ባለመሆናቸው፣ ባንኩ በተለየ መልኩ የሚሰራበት፣ የሚከላከላቸው አገልግሎቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ያንን ለመጋፈጥ ሲሉ ነው እንደዚህ ዓይነት ባንኮች መመስረት የሚያስፈልጉት።

"እዛ መሄድ ካልቻልን፣ እርስ በርሳችን ተሰባስበን፣ ባንካችንን ከፍተን፣ ገንዘባችን አስቀምጠን፣ ብድርም ካስፈለገ ብድር ወስደን የራሳችንን ባንክ እናቋቁማለን" የሚለው ነገር የሰለጠነው ዓለም ውስጥም አለ። አሜሪካን ብንመለከት የጥቁሮች ባንክ አለ፣ የህንዶች ባንክን የመሳሰሉ የተለያዩ ባንኮች በስራ ላይ አሉ፤ ይሄ አዲስ ነገር አይደለም፡ ፡ በተለይ ፖለቲካው ነፃ ነው የሚባልበት ቦታ ላይ እንደዚህ ዓይነቶቹን ባንኮች መከልከል አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። አታድርጉ ማለት አይቻልም ለማለት ሳይሆን፣ አሁን ባለው አስተሳሰብና አሁን ባለው አካሄድ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ለመከልከል ያስቸግራል።

ምክንያቱም ቅድም እንዳልኩት አመጣጣችን በኢትዮጵያ፣ እነዚህ ሁለት ትልልቅ የሃይማኖት ተከታዮች ያሉበት ሀገር ነው። አንደኛውን ከልክለህ አንደኛውን አትፈቅድለትም። ወይም ደግሞ ሁለቱንም የምትከለክልበት አቅጣጫ ሊኖር ይገባል። ይሄ ራሱ ደግሞ አስቸጋሪ ነው። ዋናው መደረግ ያለበት፣ አለማበረታታትና ሌሎች ባንኮች ሊያረጉ ያልቻሉትን እንዲያደርጉ መገፋፋቱ ነው ውጤታማ የሚያደርገው። ዛሬ ያሉት ወይም ነገ የሚከፈቱት ባንኮች፤ ለምሳሌ ሌሎች ያልደረሱበት ቦታ እንዲደርሱ፣ ሌሎች የሚከለክሏቸው የብድር ዓይነቶች ካሉ፣ እነሱ ያንን ለመፍቀድ የሚያስችል አቅም እንዲያገኙ መንግስት መርዳት አለበት ብዬ ነው የማምነው።

**ግዮን፡- እነኚህ በሃይማኖት ወይም በብሔር መሰረት ላይ የሚቋቋሙና የተቋቋሙ ባንኮች፣ ጥቅማቸው ነው የሚያደላው ጉዳታቸው?**

አቶ ክቡር፡- እርሱን በሁለት ዓይነት ነገር ልትለካው ትችላለህ። በፖለቲካ ስታየው መከፋፈልና መለያየቱን ሊያሰምርበትና ሊያጎላው ይችላል። በጥቅም ካየነው ግን

እንዲህ ዓይነቱ መሰባሰብ የተሻለ ጥቅም ሊያስገኝ ይችል ይሆናል፡፡ ግን እሱም ቢሆን ችግር አያጣውም፡፡ ለምሳሌ ሶማሌ ክልል ውስጥ የተከፈተ ባንክ፣ በሩን ለሌሎችም ቢከፍት ነው የበለጠ ጥቅም የሚያገኘው እንጂ ለሶማሌ ተወላጅ ብቻ ብሎ ከሰራ፣ አቅሙ ወይም የትርፉ ውስንነት ወዲያው ግልፅ ሆኖ ይታያል፡፡

በዚህ መንገድ ካየነው የፖለቲካው ችግር የበለጠ ያመዝናል፡፡ መለያየቱ የበለጠ ጎልቶ ይታያል፡፡ ለማለት የፈለግሁት ሀገርን ለማሰባሰብ ይጠቅማል? ወይስ ሀገርን ለመበታተን ይጠቅማል? የሚለውን በተመለከተ ነው፡፡ ይቻላል፣ አይቻልም፣ ህጉ ይፈቅዳል፣ አይፈቅድም? የሚለውን ካየን፤ ይሄ ግልፅ ነው፣ እንዲህ ዓይነቱን ባንክ ማቋቋም እንደሚቻል ሕጉ ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን ትኩረት ማድረግ ያለብን፣ ሀገርን ከመበታተንና ከመሰባሰብ አኳያ ነው፡፡ በእሱ ደረጃ ስናየው በእኔ እሳቤ እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ሀገርን የበለጠ ያራርቃል፣ ልዩነትን ያሰፋል እንጂ አያቀራርብም የሚል ነው፡፡

**ግዮን፡- ለ27 ዓመታት በብሔር ተከፋለን ብንቆይም፣ አሁን ላይ መንግስት ህዝብን ወደ አንድነት ለማምጣት እየሰራ ባለበት ወቅት እንዲህ ዓይነቶች ባንኮች እውን መሆናቸው ስልጣን ላይ ላለው አካል ለራሱ ዕንቅፋት አይሆንበትም?**

አቶ ክቡር፡- ዕንቅፋት ይሆንበታል፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል የሀገሪቷ፣ የህዝቧ ስብስብና አንድነት ላይ እየሰራ ነው ብለን እንገምታለን፤ ከዛ አኳያ ስንወስደው ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ እንግዲህ ከህጋዊነት ስናየው ነው፣ ዲሞክራሲ ከሚለው እሳቤ አይደለም፡፡ ስለዚህ እነዚህን ነገሮች መንግስት እንዴት ነው የሚያጣጥማቸው? የሚለው ነው ዋናው ነጥብ፡፡

መንግስት ወይም የመንግስት ኃላፊዎች እንዲህ ዓይነት ሀሳብ ሲመጣ፣ እንዲህ ዓይነት ዕቅድ ሲቀርብ በተቻላቸው ላለመቀበል መጣር ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሄ የሚሆነው በማስገደድ አይደለም፣ በማሳመን መደረግ መቻል አለበት፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ባንኮች ሊያድጉና ሊጠነክሩ የሚችሉት፣ ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያ ስታድግ እንጂ፤ ኢትዮጵያ በብሔር ስትለያይና ስትከፋፈል አይደለም፡፡ ስለዚህ መንግስት ይሄንን ማሳመን መቻል አለበት፡፡

በምን እንተካው ከተባለ? ወይም በክልሌ ባንክ ያስፈልገኛል የሚል ጥያቄ ካለ፣ ከላይ እንደገለፅሁት፤ ክልሉ የራሱን ባንክ በፈለገው ቁጥር መጠን ማቋቋም የሚያስችለውን አቅም በመስጠት ከችግሩ መውጣት ይቻላል፡፡ ክልሉን ለማሳደግ ከተፈለገ፣ ሕዝቡን ከመበታተንና ከመለያየት ባሻገር ማለት ነው፡፡ በዚህ መልክ ካየነው ብቻ ነው ውጤታማ መሆን የምንችለው፡፡

**ግዮን፡- የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውስ ጥቅሙ ምንድን ነው? እዚህ ሀገር የተቋቋሙትን ባንኮችን አያዳክማቸውም?**

አቶ ክቡር፡- የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ ማየት ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ የውጭ ባንኮች ሲከፈቱ፣ ሀገር ውስጥ የነበሩ ባንኮች በሙሉ በውጪዎቹ ተውጠዋል ወይም የተሸፈኑበት ሁኔታ አለ ብሎ ሙሉ በሙሉ ለመናገር ያስቸግራል፡፡ በርግጥ ተወዳዳሪነታቸው አንዳንዴ ችግር ውስጥ ሊከታቸው የሚችልበት ቦታና ሁኔታ አለ፡፡ ግን የውጭ ባንኮች እንደዚህ ዓይነት ቦታ የሚመጡት አንደኛ የሚያገኙት ትርፍ ሲኖር ነው፡፡

አሁን ባለንበት ሁኔታ ኢትዮጵያ በሯን ለውጭ ባንክ ከፈተች ብንል፣ ሮጦ የሚገባ ባንክ አለ የሚል ዕምነት የለኝም፡፡ የውጭ ምንዛሬ ችግር አለ፣ የኢኮኖሚዋ መዳከም አለ፤ የወደፊት አቅጣጫዋን እንኳን ለማየት አስቸጋሪ የሆነበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ኢኮኖሚዋ ለረዥም ጊዜ እየተንገዳገደ የምትሄድበት ሂደት እየተስተዋለ ስለሆነ፣ ብዙዎቹ የባንክ ድርጅቶች ትኩረት የምትስብበት ሁኔታ ላይ አይደለችም ሀገራችን፡፡

ግን ደግሞ የውጭ ባንኮች ቢመጡ ለሁሉም በር መክፈት ያለብን አይመስለኝም፡፡ መምጣት ያለበት፣ መፈቀድ ያለበት እኛ ሀገር ውስጥ ለሀገሪቷ ልማት የሚሰሩ፣ ያንን ማረጋገጥ የሚችሉ፣ ያለንን ሃብት ይዘው የሚጠፉ ሳይሆኑ፣ አብረውን የሚያድጉ ባንኮች መሆን መቻላቸው በደንብ መረጋገጥ አለበት፡፡ ይሄን ደግሞ ሌሎች ሀገራት ያደረጉበት ሁኔታ ስላለ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ከዛ ውጭ ገና ለገና የውጪ ባንክ ስለሆነ ብቻ ዝም ብለን፣ በራችንን ከፍተን አስገብተን ማንም እንደፈለገ የሚፈነጭበት መሆን የለበትም፡፡

**ግዮን፡- የሙስሊም ባንኮች ሲከፈቱ ለማህበረሰቡ ያለ ወለድ ነው አገልግሎት የሚሰጡት፣ ባንክ ደግሞ አትራፊ ነው፣ በሰራ መጠን ወለድ የማይቀበል ባንክ ከሆነ የት ድረስ ይጓዛል? እንዲህ ዓይነቱ አሰራር በሌላ መልኩ ማህበረሰቡንም ተፅዕኖ ውስጥ ይከተዋል የሚባልም ነገር አለ፡፡**

አቶ ክቡር፡- ወለድ የለውም ለማለት ያስቸግራል፤ በርግጥ ወለድ የሚለውን ስም ላይጠቀሙበት ይችላሉ፣ ግን ለሚሰጡት አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ይኖራል፡፡ ሌሎች ሌሎች አገልግሎቶች እየሰጡ የሚያተርፉበትም

መንግስት ወይም የመንግስት ኃላፊዎች እንዲህ ዓይነት ሀሳብ ሲመጣ፣ እንዲህ ዓይነት ዕቅድ ሲቀርብ በተቻላቸው ላለመቀበል መጣር ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሄ የሚሆነው በማስገደድ አይደለም፣ በማሳመን መደረግ መቻል አለበት፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ባንኮች ሊያድጉና ሊጠነክሩ የሚችሉት፣ ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያ ስታድግ እንጂ፤ ኢትዮጵያ በብሔር ስትለያይና ስትከፋፈል አይደለም፡፡ ስለዚህ መንግስት ይሄንን ማሳመን መቻል አለበት፡፡

ሁኔታ አለ፡፡ እንዳልከው የባንክ አገልግሎትን ያለ ትርፍ መስራት ያስቸግራል፡፡

በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ውስጡን ጠለቅ ብዬ ባላውቀውም አካሳሱ ያልሆነ ትርፍ፣ ያልሆነ ወለድ፣ ማስከፈል የለብንም የሚል መርህን መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ሃይማኖቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች የተደነገገ ደንብ እንደ መሆኑ መጠን፣ ወደ ዘመናዊው ዓለም ስንመጣ በተለይ ባለፉት ዓመታት ውስጥ የምናየው፣ የእኛ ባለ ወለድ ባንኮቻችን ለእኔ ከመጠን በላይ ተገልጋዩ ላይ ወለድ የሚጭኑ ናቸው፡፡ ልማት እስከተፈለገ ድረስ ይሄ መስተካከል መቻል አለበት የሚል አቋም ነው ያለኝ፡፡ ምክንያቱም ነፃ ገበያ በሚል መርሆ፣ የተወሰኑ ሼር ሆልደር የምንላቸው (በቁጥር ጥቂት የሆኑ)፣ ቢደመሩ ሰላሳና አርባ ሺህ የማይሞሉ ሰዎች፣ በባንክ የሚሽከረከረውን ትርፍ ጠቅላላ እነሱ ወስደው፣ ሌላው በሚሊየን የሚቆጠረው ህዝብ ንብረቱን የሚያስረክብበትና የሚያጣበት ሁኔታን መፍጠር ትክክል ነው ብዬ አላምንም፡፡

በዚህ ዙሪያ ከእስልምና ባንኮች ብዙ እንማር ይሆናል፡፡ “ወለድ አናስከፍልም” ሲሉ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ በንግድ ላይ የሚተዳደር ሰው ብድር ወስዶ፣ ወለድ አትክፍልም ቢባል የማይደግፍ የለም፡፡ ባንኮች ደግሞ ይሄን ማድረግ ከቻሉ፣ አገልግሎታቸው ለህዝብ ትልቅ ውጤት የሚያመጡና ትልቅ ዕርዳታ የሚሰጡ ተቋማት ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸው የአገሪቷን ውጭ ምንዛሬ እጥረት በመቅረፉ በኩልስ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል?**

አቶ ክቡር፡- እንደማንኛውም ንግድ ከውጭ ብዙ ገንዘብ ይዘው የሚመጡበት ምክንያት የለም፡፡ ለምሳሌ ኢንቨስት አድርጎ ( በባንኩ አባባል፣ በነጋዴዎቹ በኩል ማለት ነው) ከእነሱ የሚያገኘውን ትርፍ ወደ ዶላር ለውጦ፣ ሀገሩ ይዞ መሄድ ነው የሚፈልገው፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ ላይ እሱን ማድረግ አይችልም፡፡ ወደፊት ማድረግ ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲመጣ፤ ሊያደርግ የሚችለው ሀገሪቷ እየከበረች፣ በእጇ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እያደገ ሲመጣ፣ ከዛ ውስጥ ወደ ሀገሩ ይዞት ሊሄድ የሚችል ዓይነት ደረጃ ላይ ስንደርስ፣ የእዛ ዓይነት አሰራር ይፈቀዳል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

በመሰረቱ ባንኩ ራሱ ወደ እኛ ዓይነት ሀገር ለመግባት የደብሊው ቲዩ አባል ነን ወይስ አይደለንም? የሚለው ራሱ፣ ትልልቅ ባንኮች እንዲመጡ ወይም ደግሞ በሚፈልጉት ደረጃ እንዳይሰሩ ፈተና ይሆናል ብለን መገመት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ደብሊው ቲዩ በመንግስትና በእነዚህ ባንኮች መካከል እንኳን ችግር ቢመጣ እንዴት እንደሚዳኝ፣ የት እንደሚዳኙ በግልጽ የሚያስቀምጥ ድርጅት ነው፡፡

የተባለው ችግር ቢመጣ፣ እነሱ የኢትዮጵያ ባንኮች ወይም ደግሞ የኢትዮጵያ የንግድ ተሳታፊዎች በአንድ ዓይነት ዓለም አቀፍ ህግ እንዲዳኙ የሚፈልጉ ስለሆኑ፤ አሁንም ኢትዮጵያ ወደ እዛ ሲስተም መግባቷ ለዚህ ነው የሚጠቅመው ለማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ከቅርብ ዓመታት በፊት ባንኮችና**



**► ኢንሹራንስ ውስጥ ሼር ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ድርሻቸው እየተመለሰ፣ ከባለድርሻነት እንዲወጡ ሲደረግ ነበር። በቅርቡ ደግሞ እንደ አዲስ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ባለድርሻዎች እንዲቀጥሉ የተደረገበት አሰራር አለ። አንድ ወጥ አቋም አለመያዙና መገለባበጡ ከኢኮኖሚው አኳያ እንዴት ይታያል? በዚህ ላይ ሰፊ ጥናት መደረግ የለበትም?**

አቶ ክቡር፡- እንደ መንግስቱ አስተሳሰብ ነው፣ በወቅቱ ያ ነገር የተደረገው። ለዚህኛው መንግስት ዲያስፖራው መጥቶ ኢንቨስት ማድረጉ አስፈላጊነው፣ ለሀገሪቱ ዕድገት ይጠቅ ማል ብሎ አስቧል። የቀድሞው መንግስት ደግሞ የዲያስፖራው መምጣት ብዙም አይጠቅምም የሚል እሳቤ ነው የነበረው። የሚቀጥለውና ከዚህ በኋላ የሚመጣው መንግስት ደግሞ ምን እንደሚል አይታወቅም። እነዚህ የፖለቲካ ሂደቶች ናቸው።

በመሰረቱ ጥያቄው ትክክል ነው? ትክክል አይደለም? የሚለው፣ ህግ ተላልፈዋል? አልተላለፉም? የሚለው ነው። የኢትዮጵያ ህግ በወቅቱ “የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆኑ የባንክ ሼር መግዛት አይችሉም” የሚል ህግ ነበረ። ከዛ በኋላ በተለያየ ምክንያት አንዳንዱ በወቅቱ ኢትዮጵያዊ ነበር፣ ከዛ ዜግነቱን የለወጠ አለ፤ አንዳንዱ ደግሞ ይመስለኛል በውርስ ያገኘው አለ። እነዛን የተለያዩ ምክንያቶች ህጉ እንዴት ያየዋል? ከሚለው በመነሳት ይመስለኛል ውሳኔው የተላለፈው። አንዳንዱ ውሳኔ በርግጥ ሊገባ የማይችል ነው። “በገዛችሁበት ዋጋ ውሰዱ” የተባሉ አሉ። እሱ ትክክለኛቱ ፈፅሞ አይታየኝም። እነዛ ሰዎች በወቅቱ አክሲዮንን ሲገዙ፣ ያኔ በነበረው ዋጋ ስለሆነ ሲመለስላቸው ደግሞ በሚመለስበት ወቅት ባለው ዋጋ ነው መመለስ የነበረበት።

ዞሮ ዞሮ ዲያስፖራው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ እንዲሳተፍ ከተፈለገ፣ እሱ ባለበት ሀገር ከሚያገኘው የተሻለ ጥቅም ሲያገኝ ነው መጥቶ እዚህ የሚንቀሳቀሰው። በተለይ አሁን እንደበፊቱ ተንደርድሮ አይመጣም፤ ካሳለፈው ነገር የተነሳ ዕምነቱ እስኪገነባ ድረስ፣ ወይም እምነቱን ሊያጠናክርለት የሚችል ዋስትና እስከሚሰጠው ድረስ እንደበፊቱ በብዛት ላይመጣ ይችላል።

**ግዮን፡- መንግስት በተቀያየረ ቁጥር የሀገሪቱ የቢዝነስ ኢኮኖሚ ወደላይና ወደታች መውጣትና መውረዱ ይታወቃል፤ የባንኮች ህግ በየጊዜው ከመቀየር ይልቅ ለምንድን ነው ወጥ አሰራር በግልፅ ሊቀመጥ ያልቻለው?**

አቶ ክቡር፡- ፖለቲከኞቹ የራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው ሲመጡ፣ በወቅቱ ከነበረው መንግስት የተለየ ፕሮግራም ይዘው ለመምጣት ነው የሚፈልጉት። ምክንያቱም ያ አልሰራም ብለው ስለሚያምኑ፣ የራሳቸውን ፕሮግራም ያወጣሉ። እንደ አጋጣሚ አሸንፈው ከመጡ፣ ህዘቡ ፈልጎታል ማለት ነው፤ የእነሱን ፕሮግራም። ቀደም ብለን ያነሳነው የዲያስፖራ ችግር ትክክለኛ ዴሞክራሲ ቢሆን ኖሮ የተመረጠው፣ በዛ አጀንዳ ሆኖ ከተመረጠ የህግ የመለዋወጥ ባህሪይ ፖለቲካው አዲስ አቅጣጫ ማሳየት እንዳለበት የሚያመላክተን። በተለይም በምርጫ ጊዜ።

ወይም ደግሞ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ከመጡ በኋላ ያላየነውና ግልፅ ሆኖ የማይወጣው፤ እንደ ፖለቲከኛ ይሄ መንግስት ይሄን ሀገር፣ ይሄን ኢኮኖሚ ወዴት ነው የሚወስዱት? የሚለው ነጥብ ለረዥምም ጊዜ አነጋጋሪ ነበር። በርግጥ አሁንም፣ ምናልባት ገና ወደ ፊትም አነጋጋሪ የሚሆን ይመስለኛል ምላሽ እስካልተሰጠበት ድረስ። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ነገር በግልፅ መቀመጥ ያለበት ይመስለኛል።

**ግዮን፡- ከለውጡ በኋላ በሀገሪቱ ያሉትን ሂደቶች እርስዎ እንዴት ተመለከቷቸው?**

አቶ ክቡር፡- የኢትዮጵያ ለውጥ አዲስ ሳይሆን፣ ወደ ኋላ ወደ ከ19 60 ዎቹ መነሳትና ማየት አለብን። ምክንያቱም ከዛን ጊዜ የተጀመረ ለውጥ ነው እስካሁን ድረስ በየጊዜው አንዳንዴ የተስተካከለ እየመሰለ፣ መልሶ የሚያገረሽበት። የተማሪዎች ንቅናቄ በወቅቱ ያነሳው ጥያቄ፤ “ሀብቱ ያለው ንጉሱና የተወሰኑ መኳንንት ጋር ነው ፣ ሕዝብ የሀብት ባለቤት አልነበረም” የሚል ዓይነት ነበር። በርግጥ ሌሎችም ጥያቄዎች እንዳሉ ሆነው። የብሔር ብሔረሰብ ጥያቄም ተነስቶ ነበር፤ በጊዜው በሀብት ክፍፍል ላይ፣ የመሬት ክፍፍል ላይ ያተኮረው ኃይል አሸንፎ የተወሰነ ጊዜ ተጉዟል።

ከዛ ደግሞ “የብሔር ብሔረሰብ ችግር ገና አልተፈታም” የሚለው ከደርግ በኋላ የመጣው ኃይል፣ ለ27 ዓመት ስልጣን ላይ ተቀመጠ። እነዛን ችግሮች በተለይ የብሄር ብሔረሰብ ችግሮችን ለመፍታት፣ የሚደረጉ ወይም ደግሞ መደረግ አለባቸው የተባሉ መፍትሄዎች በክልል፣ በቋንቋ የተዋቀሩ ክልሎችን ማደራጀት፣ የራሳቸው አስተዳደር እንዲኖራቸውና “እስከመገንጠል ድረስ ይጓዙ” በሚል የተሄደበት አሰራር አሁን ላይ፣ “መገንጠልማ የለብንም” ፣ “አንድነት ያስፈልገናል” የሚል መርህ መጥቷል።

በምን መልኩ ነው አንድ ላይ አንድ ላይ መሆን ያለብን? የሚለው ገና በደንብ የተጠና አይመስለኝም። ግን “መበታተን የለብንም፣ መፍረስ የለብንም፣ አንድ ላይ መሆን ይገባናል” የሚለው ኃይል እንግዲህ እየተንቀሳቀሰ ነው ያለው። ስለዚህ ሂደቱ ገና አላበቃለትም ማለት ነው። የስልሳዎቹ አብዮት እስካሁን ድረስ እየተቀጣጠለ ሄዷል። እዚህ ሂደት ውስጥ ማየት ያለብን፤ ተስፋ አለው ወይስ ተስፋ የለውም ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ? የሚለውን ነው።

**ግዮን፡- ታዲያ እርስዎ እዚህ ላይ እምነትዎ ምንድን ነው?በዚህች ሀገር በቀጣይ ትልቅ ተስፋ አለ?**

አቶ ክቡር፡- እኔ እነዚህ ጥያቄዎች በብሔርና በብሔረሰብ ችግር የሚፈቱ አይደሉም የሚል ዕምነት ነው ያለኝ። ምክንያቱም ብሔር ብሔ ረሰብ አሁን ያለንን የሥራ አጥነቱን ጉዳይ አይቀርፈውም። አሁን ያለንን ከኢኮኖሚ ጋር የተያያዙ፣ ሀብት የማፍራት፣ ድህነት የመ ነስን ጉዳዮችን አይመልስም። ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በዓለም ላይ ብዙዎቹን ነገሮች እየ ለወጠ እንዳለ በሚታይበት ጊዜ፣ የትምህርት አሰጣጣችንና ከትምህርት የሚገኘው ውጤት፣ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ ሊጠቅሟት የሚችሉ፣ በጎ ውጤቶችን ሊያመጣ የሚቻልበት ሁኔታ ያለ አ ይመስለኝም። እሱ ነው የበለጠ የሚያስፈራኝ።

በአንድ ወቅት ባርነት በጊዜው እንደ ትክክለኛ ነገር የሚታይበት ሁኔታ ነበር፤ እሱ ተገልብጦ ባርነት የተወገደበት ጊዜ አለ፣ ከዛ ደግሞ የንጉሶች ወይም የተወሰኑ ሰዎች ብዙዎቹን ሀገሮች ይዞ የመሄድ ስልጣን፣ ከእግዚአብሄር ለአንድ ሰው እንደተሰጠ ዓይነት የሚታይበት ወቅት ነበር፤ ግን እሱ ሁሉ ተደርምሶ ሌላ አይነት አካሄድ መጥቷል። ይሄ የአለማችን ታሪክ ነው፤ አሁን ያለንበት ሁኔታ ለሁሉም ድምፅ መስጠት የሚቻልበት፣ ሁሉም የሀገሪቱን፣ የራሱም ዕድል ወሳኝ ሊሆን የሚችልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፤ በዲሞክራሲያዊ መንገድ። ስለዚህ አሁን ካለንበትና ችግር የምንወጣ ይመስለኛል። ወዴት አቅጣጫ ነው የምንሄደው? የሚለው ግልፅ ባይሆንልኝም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለም ብዬ ነው የምገምተው።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**



# በእንቁላሉ በቀጣሽኝ

ብሩክ አስቻለው

ይህን አባባል ለተለያዩ ገጠመኞቻችን እንጠቀመዋለን፡፡ የተባለበት ታሪክም በአብዛኛው ህብረተሰባችን ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ አንድ ልጇን ይዛ በድህነት የምትኖር እናት፣ ከዕለታት በአንድ ቀን ልጇ እንቁላል ሰርቆ ይዞ ይመጣል፡፡ ይህች ቀን የሕይወቱን አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ የቀየረች ቀን ናት ማለት እንችላለን፡፡ እናትም "ጎሽ የኔ ልጅ" ብላ እንቁላሉን ጠብሰው በሉ፤ በዚህ የጀገነው ልጇ፣ በቀጣይ ዶሮ ሰርቆ መጣ፡፡ አሁንም አልተቃወመችውም፡፡ ዶሮዋን ሰርተው በሉ፡፡ በግ ይዞ ሲመጣ፤ አሁንም አልተቃዋመችውም፤ በጉንም አበጃጁት፡፡ በሌላዋ የቀን ክፉ ከበረት ገብቶ በሬ ሰርቆ ሊወጣ ሲል ተያዘ፡፡ ወደ ህግም ቀረበና፤ በዘመኑ ቅጣት መሰረት በስቅላት እንዲሞት ተፈርዶበት ፍርዱ ወደሚፈፀምበት አደባባይ ተወስዶ ሊሰቀል ሲል፤ የልጇን የሞት ፍርድ ሰምታ ለምታለቅሰው እናት "የአሁኑ ለቅሶሽ አይጠቅመኝም፣ ያኔ በእንቁላለሉ በቀጣሽኝ ነበር" አላት- ይላል ተረቱ፡፡

ማንኛውም ነገር ከጅምሩ ገና ሲያቆጠቁጥ፣ እንከን ሆነው የመጡትን ነገሮች ሁሉ ማስወገድ ከባድ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ አንድ ዛፍ ያልተስተካከለ አስተዳደግ ካሳየ፣ ገና በለገናቱ ያን የተዛባ ክፍል ወደሚፈለገው ቁመና ማቃናት በጣም ቀላል ነው፡፡ ይህን የለጋነት ጊዜውን ሳንጠቀምበት አልፎ፣ ስር ሰዶ በማደግ ግንድ ከሆነ በኋላ ግን ማስተካከያ ሊደረግበት አይችልም፡፡ ጎባጣውን ለማቅናት ማሰብ ቂልነት ነው፡፡ ህፃን ልጅ ወላጆቹ ሲያሳድጉት በሚበጀው አካሄድ ከገሩት፣ የወጣትነቱን፣ የጉልምስናውን ብሎም የእርጅና ዘመኑን ስንቅ ሰነቁለት ማለት ነው፡፡ በግል ጤንነታችን እንኳ በጊዜው የታከምነው የጤና መታወክ እና ችላ ብለን ጊዜ የሰጠነው ህመም የመኖር እና ያለመኖርን ውጤት የሚያስከትል ሰፊ ልዩነት ነው ያለው፡፡ ብዙ ማለት እንችላለን፤ ግና "ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም"ና ወደ ነጥቤ ልግባ፡፡

የአንድ አገር መንግስት ከአምባገነንነት የፀዳ ከሆነ፣ ግቡ ለህዝቦቹ የተሻለ ነገርን ለማምጣት መትጋት ነው፡፡ በዚህ ጉዞው የሚመራቸው ህዝቦች ሁሉም ምቹ ይሆኑለታል ማለት አይደለም፡፡ በበሳል አመራር እና በሆደ ሰፊነት የአብዛኛውን ይሁንታ ያገኛል በተለይ ድሃ አገርን መምራት የችግሩ ዐይነት ብዙ ስለሆነ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ አላስፈላጊ አካሄዶች ሁሉ በጊዜው ማረምን፣ ለውይይት ማቅረብ፣ወርዶ መቃኘት፣ማህበረሰቡ ምክንያታዊ መሆንን እንዲለምድ ያደርጋል፡፡ ቅሬታ የመቀበል ባህል እንዲያዳብር ያደርገዋል፡፡ ይህን በጊዜው ያለማረም ድክመት ያለበት አመራር ዋጋ የሚያስከፍል ማህበረሰባዊ ቀውስ ይገጥመዋል፤ ልክ "በአንቁላሉ በቀጣሽኝ" እንዳለው፡፡

**...የአንድ አገር መንግስት ከአምባገነንነት የፀዳ ከሆነ፣ ግቡ ለህዝቦቹ የተሻለ ነገርን ለማምጣት መትጋት ነው፡፡ በዚህ ጉዞው የሚመራቸው ህዝቦች ሁሉም ምቹ ይሆኑለታል ማለት አይደለም...**

ከቀናት በፊት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኢንጅነር ታከለ ኡማ "በአዲስ አበባ የሚገኙ ባለሀብቶች፣ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት፣ ደላሎችና የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ጭምር የተሳተፉበት ህገ ወጥ የቤት ግንባታ እና የመሬት ወረራ ላይ፤ (በቁጥር 30 ሺ ተብሏል) የከተማ አስተዳደሩ የሚወስደው እርምጃ ግንባታውን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን፣ በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ ስራም ይሰራል የሚል መንፈስ ያለው መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ህገወጥነትን ማውገዝም፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴ መስመር ማስያዝና ህግ ማስከበር ለከተማ አስተዳደሩ የስራው ክፍል ነውና ብቻውን ችግር የለበትም- ይበረታታልም፡፡ ነገር ግን ለዚህ ሂደት ሲባል በአንዳንድ አካባቢዎች እንደምናየው የዜጎችን እንደ ሰው የመኖር መብት የጣሰ፣ ያለ ቅድመ ውይይትና ምትክ እርምጃ እወስዳለሁ፤ ማለት ግን በራሱ ህገወጥነት ይመስለኛል፡፡

ምክንያቱም እነዚህ ህገ ወጥ የተባሉ አካላት፤ እዚህ ቦታ ላይ እንደ "እንግዳ ደራሽ" ድንገት አልተከሰቱም፡፡ በሂደት ነው የተሰባሰቡት፡፤ እንቅስቃሴው ከጅምሩ ቢገታ፣ ማንም ሳይጎዳ ህግ ይከበር ነበር፡፡ የዚሁ ስርዓት ተዋናዮች በተሳተፉበት አሰራር ነው ቤት ገንብተው፣ ቤተኞቻቸውን ይዘው አገር አማን ብለው ኑሮዋቸውን እያስቀጠሉ የቆዩት፡፡ ለህገ ወጥነታቸው ጭንብል እያለበሱ፣ ህጋዊ የሆኑ ያህል እንዲሰማቸው ያደረጓቸው፤ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላትም ናቸው፡፡ እነዚህ ገንቢዎች የቦታው መብት አለኝ ከሚል ይግዙት፣ አልያም ራሳቸው ሄደው ይስፈሩበት፤ ከመንግስት ዓይን እና ጆሮ ውጭ ግን አልነበሩም፡፡ ይልቁንም እነዚህ የአካባቢው የመንግስት ሰዎች፣ ህገወጥነታቸውን መጠቀሚያ በማድረግ፤ በእያንዳንዱ የአፈፃፀም እንቅስቃሴያቸው ህጋዊ ይሆንላችኋል እየተባሉ ብዙ ገንዘባቸውን ተበዝብዘዋል፡፡

ውሃና መብራት ሲያስገቡ፣ ግብር እንዲከፍሉ ሲደረግ፣ ለልማት አስተዋፅኦ ሲያደርጉ፣ እንደ ህጋዊ ተቆጥረዋል ማለት ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆንም መንግስት አለ፤ ያኔውኑ ብዙ ሳይከስሩ፣ በእንጭጩ መቅጨትና አገርንም፣ ዜጎችንም መታደግ ይቻል ነበር፡፡ ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል እንደሚባለው፤ የባለቤትነት ስሜታቸው እንዲጎለብት ተደርገዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ችግር እንደሆነ እንኳ ዕውቀቱ የሌላቸውም አሉ፡፡ ታዲያ ዜጎችን ከእንዲህ አይነት ምስቅልቅል ውስጥ የከተቱ አሁንም በመዋቅሩ ውስጥ ተሰግስገው ሳይነኩ አህያውን ፈርቶ ዳውላውን መሆኑ አስተዛዛቢ ነው፡፡

እነዚህ "ህገወጥ ናችሁ" የተባሉ ሰዎች አብዛኛዎቹ ቤት አለን ብለው ኑሮ መስርተዋል፤ ወልደዋል፡፡ እነዚህ ልጆች ደግሞ የነገ አገር ተረካቢ ናቸው፤ እንደ ዜጋ ምን ዓይነት ስነ ልቦና እየገነባንላቸው ነው? ይህን ቤተሰባዊ አንድነት በፈለገ ጊዜ "ተነስ" ማለትስ ፍትሃዊ ነው? በኑሮ ውድነት እና በተለያዩ ስጋቶች ተወጥሮ ላለ ወገን፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆን ህግ የማስከበር ስራ ነው የሰራነው ለማለትስ ሞራሉ አለ?

በዚህ ህገ ወጥነት የተፈረጁት ዓይነታቸው ብዙ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ አልጠግብ ባይ አግበስባሾች አቅማቸው በፈቀደው ልክ የተለያዩ ግለሰቦችን ስም እየተጠቀሙ የገነቡት ከሆነ፣ አገራችን ኢትዮጵያ እነዚህን የምታስተናግድበት ትከሻ ስለሌላት፤ እየተጣራ እርምጃ (ህጋዊ እርምጃ) ይወሰድ፡፡ ነገር ግን ይህን ሳይረዱ፣ በተለያየ የህይወት መስመር ገብተው፣ በአረብ አገር ተንከራተው፣ ወዘተ ያለ ጥሪታቸውን ቤት ይሻለናል ብለው በዛ ላይ ያራገፉት ዜጎች፤ እንደ ሰው ሰብዓዊ መብታቸው ሳይደፈጠጥ መፍትሔ ሊበጅላቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ሁሉ ግምት ውስጥ ሳይገቡ፣ ሳይለዩ፣ ሳይጤኑ "ውጡ" ማለት ያለመሳሪያ መግደል ነው፡፡ የት ይውደቁ? መጠለያ ይዘጋጅላቸው፤ ያወያያቸው፤ መፍትሔው በጋራ ይፈለግ፡፡ ሐገር የነሱም ናትና፡፡

ይህን ሁሉ ስል መንግስት ህግ የማስከበር ስራውን የሚቃወም መንፈስ ፈፅሞ የለኝም፡፡ በእንቁላሉ ያልቀጣ አካሄድ ይዞ ስለቆየ የሚያስከበርበት መንገድ ግን ይስተካከል፡፡ ህግ ለሰው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለህግ አልተፈጠረም፡፡ ከተወያየን፣ ከተሳሰብን፣ ከተግባባን የማንንደው ተራራ የለም ብዬ አምናለሁ፡፡ አበቃሁ፡፡

**ቸር እንሰብት**



ጥላሁን መሸሻ

# ኢትዮጵያ ዛሬ አርበኛ ትውልድ ትፈልጋለች !

አንዳንድ ሰዎች ቢማሩም ባይማሩም የተፈጥሮ ሂደትና ዕድገት ብዙ አይገባቸውም፡፡ ሁሉንም ነገር በእነሱ በራሳቸው ዕድሜና የአስተሳሰብ ርቀት ይለካሉ፡፡ የሚገርመው ነገር የሰው ልጅ እንደ አንድ ግለስብ በምድር ላይ የሚኖረው ሕይወት እጅግ አነስተኛና በማህበረሰብም ሆነ በዓለም ታሪክ ላይ እዚህ ግባ የሚባል ተፅዕኖ የለውም፡፡ በግልም እንደ አንድ ሰው ሊሰራው የሚችል ትልቅ ታሪክ የለውም፡፡ ምክንያቱም ታሪክ እንደግንብ በግለስብ ወይም በትንሽ ሰዎች የሚሰራ አይደለም፤ በምኞትና በፍላጎትም የሚፈጠር ታሪክ የለም፡፡ ታሪክ የራሱ ሂደት አለው፣ የራሱ አቅጣጫ አለው፣ የራሱም የሆነ ጊዜና ቦታ አለው፡፡ ታሪክና ሀገር የሚፈጠረው ከማንም ግለሰብና ግለሰቦች ፍላጎትና ምኞት ወይም ድርጊት ውጭ ነው፡፡

ሀገር በቀናት ወይም በወራት ሲባልም በጥቂት ዓመታት የምትፈጠር መሬት አይደለችም፡፡ ታሪክም እንደዚሁ እንደሀገር በተመሳሳይ ሁኔታ አፈጣጠሯም ሆነ አሰራሯ ሩቅ ነው፡፡ ሀገር የአንድ ትውልድ ፍጡር አይደለችም፡፡ ታሪክም እንደዚሁ የዚህ ወይም የዛ ትውልድ ታሪክ ተብላ ልትፈረጅ አትችልም፡፡ ምክንያቱም የትኛውም ትውልድ ቀዳሚ ወይም ከርሱ በኋላ የሚመጣ መነሻና አወዳዳሪ ወይም ደግሞ ተከታይ፣ ባለፈው ሕይወት ላይ የቆመና ያለፈውን ለራሱ ማንነት መስታዎት አድርጎ የሚያይበት አንድ ትንሽ የታሪክ አካል ነው፡፡ ማንኛውም ትውልድ ታሪክ የሚኖረው ከእርሱ በቀደመው ላይ ቆሞና ወደሚቀጥለው ትውልድ የድርሻውን አዋጥቶ ነው፡፡ በነዚህ ትውልዶች መካከልና እንዲሁም በእያንዳንዱም ትውልድ ዘመን እርስበርስም ሆነ አንዱ ከሌላው ጋር ሚያጋጭና የሚያፎካክሩ ጉዳዮች አሉ፡፡ ታዲያ ታሪክ የነዚህ ሁሉ ኩነቶች ውጤት ናት፡፡ እነዚ ሁሉ ኩነቶች ደግሞ የሚከወኑት በምድር ላይ፣ በጊዜና በቦታ ነው፡፡

ሰዎች ሁሉ ቲያትረኞች ናቸው፣ ዓለም ደግሞ የትወናው መድረክ ናት ብሎ ታላቁ ደራሲ ሼክስፒር እንደተናገረው ሀገር የነዚህ ሁሉ የታሪክ ሂደቶችና ትወናዎች ውጤት ናት፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችንም የዚህ ዓይነቱ ዘመንና ኩነቶች በአንድ የተወሰነ የምድር አካል ላይ ሲንከባለል፣ ሲሸጋገርና ሲቀባበል የኖረ ታሪክ የፈጠራት ምድርና ሕዝብ ናት፡፡ አፄ ቴዎድሮስን የፈጠራቸው ቅድመ እሳቸው የነበረው ዘመነ መሳፍንት እና ከዘመነ መሳፍንትም በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ ነው፡፡ አለበለዚያ አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ስለማድረግ ባላሰቡም ነበር፡፡ የእሳቸውንም ድካምና ጥረት ተከትሎ የነገሱ ነገስታትና ስለሀገራቸው፣ ለንጉሠ ነገሥታቱና ለሀገሪቱ ታማኝ ሆነው ሲዘምቱና ሲያዘምቱ የኖሩትም መኳንንቱና መሳፍንቱ ሁሉ የየራሳቸውን ትውልድ አሻራ በሀገራቸው ታሪክ ላይ አትመው አልፈዋል፡፡ አፄ ዮሐንስ መተማ ድንበር ሄደው የወደቁት ሀገራቸውንና ታሪክ የጣለባቸውን የትውልድ አደራ ለመወጣት፣ ለመጠበቅና ለመከላከል ነበር፡፡ ዓላማቸው ማንንም ለመውጋት ወይም ማንንም ለማምበርከክ አልነበርም፡፡ አፄ ምንይልክም እንዲሁ ታሪክ፣ ሀገርና ትውልድ የጣለባቸውን ከቅድመ እሳቸው ተርፎና ተላልፎ የመጣውን የሀገርና የትውልድ ዕዳ ለመወጣት ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ሲባዝኑ ሕይወታችው አለፈ፡፡ ይኸ ሁሉ ዘመን ያመጣባቸው የትውልዳቸው ዕዳ እንጂ ሰውየው ሀገር ለመግዛት፣ ሕዝብን ለማስገበር ፕላን አውጥተውና ዕቅድ ነድፈው የተፈጠሩ አልነበሩም፡፡ ይህ ታሪክ ነው፣ ከማንም ቁጥጥርና ምኞት ውጭ የሆነ ታሪክ፡፡ ሀገርም እንዲህ ናት፤ መነሻዋና መድረሻዋ እዚህ ነው ተብሎ የማይወሰን፣ ነገር ግን ትውልዶች በረዥሙ የታሪክ ገመድ ተቆራኝተው የሚፈራረቁባትና መጨረሻ እንደሌለው ጂረት የሚፈሱባት ወንዝ ነች፡፡

በዘመነ ቅኝ ግዛት የኛ አያቶች ግማሾቹ በዱር፣ በገደሉ "እምቢ ለሀገሬ፣ ለነፃነቴ እስከወዲያኛው ያልፋል ሕይወቴ" ብለው በኢጣሊያ ወራሪ ሀይል ላይ ክንዳቸውን ሲያነሱ፤ ግማሾቹ ደግሞ የቅኝ ገዢዎች ጉርሻና የባንዳ ሹመት የሞቃቸው ባለማዕረግ ነበሩ፡፡ ሁለቱም ታሪክ ሰርተዋል፡፡ አንዱ ለራሱ፣ ለትውልዱና ለሀገሩ ታማኝ ሆኖ የሚያኮራ ታሪክ ሰርቶ ሲያልፍ፣ ሌላው ደግሞ ለሆዱና ለከሀዲ ሕሊናው አሽከር በመሆን የሚያሳፍር ታሪክ ጥሎ አልፏል፡፡ ይህ ለሀገር ተቆርቋሪ የሆነው የትውልድ አካል በአንድ በኩል ስለሀገርና ወገን ደንታ የሌለውና የታሪክ ተልዕኮው ስለራሱና ለሆዱ ብቻ የሆነው ሆድአምላኩ በሌላ በኩል ሆነው ሲታገሉባት ረጅም ታሪክ ያሳለፈች ሀገራችን፣ ዛሬ ግን ከዚህ አሳፋሪ አዙሪት ልትወጣ ይገባታል፡፡ ኑ ትምህርት እንማር፣ ካለፈው ታሪካችን ትምህርት እንውሰድ፣ ታሪክ ለመማሪያ ነውና ካለፈው ተግዳሮት ወደፊት የሚያራምደንን ዕውቀት እንቅሰም፣ አዕምሮአችንን ያደነዘዘውን፣ ልቦናችንን ያሳወረውን፣ ጆሮአችንን ያደነቆረውን አስማተ ድንቁርና እንለይና ወደፊት የሚያራምደንን መንገድ እንከተል፡፡ ሀገርና ታሪክ ለኛ ካስረከቡ ቀደምቶቻችን ታሪክ እንማርና ምን ነበር ችግራችን? ምን ነበር ስህተታችን? ምንስ ነበር ያላሰተዋልነውና መጥፎውን ታሪካችንን መለወጥ ያቃተን? ብለን እንጠይቅ፤ በችግራችን ላይ ሳይንሳዊ ጥናት አድርገን ከዚያ ችግር የምንወጣበትን መንገድ ፈልገን እናግኝ፡፡

## ለመሆኑ የቀደሙት ትውልዶች ምን ጥሩ ነገር አስተማሩን?

አፄ ምኒልክ ከዓመታት ግብር የማብላትና የደግነት እንቅልፍ ነቅተው፣ ሀገራቸውን ለማዘመን የተወሰነ ጥረት ካደረጉ በኋላ በማይድን ደዌ ተይዘው በአሳዛኝ ሁኔታ የአልጋ ቁራኛ ሆኑ፡፡ ሀገራቸው ከዓለም ወደ ኋላ የቀረችበትን ስልጣኔ እንድታገኝ በቁጭት ተነስተው ብዙውን ነገር አስጀመሩ፡፡ ትምህርት ቤት ከፈቱ፣ መኪና አስመጡ፣ ሆስፒታል አሰሩ፣ የባቡር መንገድ፣ የስልክ ግንኙነት ወዘተ ሆኖም የ የሀገራችን ሾተላይ የሆነው አዙሪት ጠልፎ ጣላቸው፡፡ ይህን ሁኔታ በሀዘን የተመለከቱት ምሁር ገ/ሕወት ባይከዳኝ እንዲህ ሲሉ የታሪክ ምስክርነታቸውን ሰጠተዋል፡፡ "ምስኪን ኢትዮጵያ ሆይ፣ የዕድልሽ ቀን መቼ ይነጋ ይሆን፣? አጤ ምኒልክ ይህን ያህል ጊዜ በጤና ኖረው በብርታት ሊጥሩልሽ ሲነሡ በበሺታ ተያዙ፡፡" የታሪካቸው አስቀጣይ ተብሎ በወንበራቸው የተተካው የልጅ ልጃቸው እያሱ ሚካኤል ደግሞ የዚህ ዓለም እብደት፣ ግለኝነትና ራስ ወዳድነት ቢጠናወተው ብልህና አስተዋይ ነው ተብሎ በሚገመተው የዕድሜ እኩያው፣ (የዚያን ጊዜ ተፈሪ መኮንን የኋላ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ) እንዲተካ ተደረገ፡፡ በዘመኑ አስተዋይና ተራማጅ ናቸው ተብለው፣ አልጋ ወራሽና የመንግሥቱ ሙሉ እንደራሴ የሆኑት እኚህ ሰው፤ በርግጥም በወቅቱ አስተዋይም ተራማጅም ነበሩ፡፡ ለዚህም ነበር በስተኋላ ጠባቸው ከርሮ ሲያስሩት፣ ሲፈቱት ኖረው በስተመጨረሻ ያስገደሉት ደጃዝማች ታከለ ወ/ኃዋርያት እንኳን ሳይቀር እሳቸው በልጅ እያሱ እግር እንዲተኩ አምርሮ የታገለው፡፡ አርበኛውና ለለውጥ ሲታገል ሕይወቱን የከፈለው ደጃዝማች ታከለ፤ እርሱ ቢሞት ትግሉ አብሮት አልሞተም፡፡ የትግሉን ችቦ በቀሪው ትውልድ ጭንቅላት ውስጥ አቀጣጥሎት ሞተ እንጂ፡፡

አዎ፤ ዐፄ ኃ/ሥላሴ ወደስልጣን ሲመጡ ተራማጅ ነበሩ፡፡ የትውልዱም ድጋፍ አልተለያቸውም ነበር፡፡ ነገር ግን የስልጣን ሰይጣን የሚመጣው እያደር፣ እየዋለ ነው፣ ወንበሩ ሲሞቅ "አዳል ሞቲ" ይሆንና ከፈረሴ▶

ላይ አልወረድም ብሎ ቡራከረዩ ይላል፡፡ የስልጣን ሱስ እንዲህ እንደዋዛ በቡና በእጣን የሚሶረፍ በሺታ አይደለም፡፡ ለዚህ ነው የስልጣን ዘመን ገደብና የዴሞክራሲ ስርዓት አስፈላጊ የሚሆነው፡፡ ዐፄ ኃ/ሥላሴ በእያሱ ዘመን ተራማጅና የለውጥ ሐዋርያ ነበሩ፡፡ ስልጣን ላይ ለብዙ ዘመን በመቆየታቸው የተነሳ የስልጣን ዛር ሰፍሮባቸው ከሰማንያ ዓመታቸው በኂላ እንኳን ከዙፋኔ ላይ ቅበሩኝ ብለው መጨረሻቸው በቅሌት ተደመደመ፡፡ አያችሁ! ዐፄ ኃ/ሥላሴ ከእያሱ ሕይወት አልተማሩም፡፡ ከራሳቸውና ከሀገራቸው ታሪክ የወሰዱት ምንም ትምህርት የለም፡፡ ይልቁን የመረጡት መንገድ ስህተትን በስህተት መደረት፣ የበቀለውን ሳር ይዞ ወደዳር ከመውጣት ይልቅ ስሩ ተቆርጦ በባህሩ ላይ የሚንሳፈፈውን ሳር ይዞ መስመጥን ሆነ፡፡ እነሆም በራሳቸው የስልጣን ባህር ውስጥ ሰምጠው ቀሩ፡፡ ቀድሞውን አለማወቅ፣ ወይ ደግሞ አለመስማትና አለመደማመጥ የሚያመጣው ጣጣ ይህን ነው፡፡

ከዐፄ ኃ/ሥላሴስ ማ ተማረ? መንግስቱ ኃ/ማርያም ድንገት በተፈጠረ የታሪክ አጋጣሚ ስልጣን ላይ ወጣ፡፡ የሕዝብን ጥያቄ በጦር ኃይል ረምርሞ፣ በባዕድ አማካሪዎች (በሶቪት ሕብረት አማካሪነት) ስልጣን ላይ ከተቆናጠጠ በኂላ ሀገሪቱ ለሃምሳ ዓመታት፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት እያስተማረች ያፈራቻቸውን ምሁራን፣ የተማሩ የጦር አዋቂ ጀነራሎችዋን (strategists) ምጥጥ አድርጎ በልቶ ባዶዋን አስቀራት፡፡ “ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትልስው ፈጃት፣ እንዳትተወው ልጇ ሆነባት” ዓይነት ሆኖ ይኸው እስከዛሬ ኢትዮጵያ ከለቅሶ፣ ከረሀብና ከድህነት አልወጣችም፡፡ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም መንገድ ለኢትዮጵያ የመፍትሄ አቅጣጫ እንደማይሆን ቀድሞውኑ በጧቱ ይታወቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ሲጀመር የምናስበው በጭንቅላታችን ሳይሆን በጡንቻችን በመሆኑ መንግሥቱ ኃ/ማርያም የሀገሩን ልጆች አባቶቻቸው ግብር ከፍለው በገዙት መሳሪያ የተማሩ ልጆቻቸውን ጨፍጭፎ ከጨረሰ በኂላ፣ በቀጠረው አዕምሮ ተሰናድቶ ሲደሰኩረው የኖረውን “የሰፊው ሕዝብ” የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ጎዳና ርግፍ አድርጎ ትቶ የማን አህሎኝና የማን አለብኝ ወንበር ላይ ሲንፈላሰስ ተረኛው ባለጡንቻ ድንገት ደርሶበት በወጥመድ እንደተያዘ “ግመሬ ዝንጀሮ” ዓይኑን እያቁለጨለጨ ለዚህ ዓይነት ወራዳ ስደት ተዳረገ፡፡

“ያዉም እንደመስሰዋለን፣ ደሙን እንደዚህ እናፈሰዋለን” እያለ በአደባባይ ሲፎክርበት በነበረው ጠላቱ አሜሪካ የፊጥኝ ተቀፍድዶ ዚምባቦይ ገባ፡፡ የውርደት ውርደት ማለት ይኸ ነው፡፡ ከጅምሩ ከሀገሩ ልጆች ጦር ባይማዘዝ ኑሮ፣ የሀገሩን ልጆች ምክርና የሕዝቡን ጥያቄ ቢያከብር ኑሮ፣ ራሱን በታሪክ ፊት ባላጠለሼ፣ ሀገሩንም ለዚያ ዐይነት ውድቀት ባልዳረጋትም ነበር፡፡ ጉልበተኝነት ቋሚ ወዳጅ የላትም፣ አንድ ወቅት ላይ የወደቀ ሌላ ጊዜ መገልበጡ አይቀሬ ነው፡፡ የሚገርመው ነገር ግን ከዚህስ ታሪክ ማ ተማረ? በቃ በዚች ሀገር ላይ ከታሪክ መማር የሚችል ትውልድ አልፈጠር አለ ማለት ነው፡፡ በመሰረቱ እንድ ለውጥ በሌላ ለውጥ ካልታገዘ የሚጠብቀውን ውጤት ከመቀበል አያመልጥም ፡፡ ትልቁ ችግራችን ይህን አለማወቃችን፣ ብናውቅም ደግሞ

> **ስዩመ እግዚአብሔር የሆነን መንግሥት “ለሕዝብ አልሰራህምና ስልጣን ለሕዝብ መልስ፣ መሬት የሚያርሰው ሕዝብ ንብረት ነውና ለአራሹ ሕዝብ ይገባል” ብሎ የተቃውሞ ጥያቄ ማንሳት በዚያ ዘመን ከከባዶች ሁሉ የከበደ የድፍረት ድፍረት ነበር**

አለመቀበላችን፣ ለለውጥም አለመቆማችን ነው፡፡ አዲስና የሚያምር ነገር ሁሉ ያረጃል፣ ያልቃል፣ ይደክማልም፡፡ ሰውም እንዲሁ ነው፡፡ ትናንት ተራማጅ የነበረ ዛሬ ይደክማል፣ ትናንት ሮጦ የማይጠግብ የሚመስለው ጀግና ዛሬ ይዝላል፣ ወደፊትም መራመድ ያቅተዋል፡፡ የዚያን ጊዜ ታዲያ የሚመራትን መርከብ ጀግናው ካፒቴን በተለመደው ፍጥነትና በተጠበቀው አቅጣጫ ማስኬድ ባለመቻሉ በወቅቱ ካልተቀየረ ወይም እርሱ ራሱ የለውጥ ሰው ካልሆነ መርከቧን ያዘገያታል፣ ጉዞዋንም አሰልችና አድካሚ ያደርግባታል፣ ለማዕበልም ይዳርጋታል፡፡


## የአሁኑ ትውልድስ ከቀደሙቱ ያገኘው ትምህርት አለ?

የኛ ትውልድ ማለትም የ1950/60ዎቹ ትውልድ ጀግና ትውልደ ነበር፡፡ ያን የደለበ የመሳፍንት ስርዓት የደፈረ ትውልድ ነው፡፡ በዚያ ዘመን በተደጋጋሚ የተነሱበትን የስልጣን ተቀናቃኞቹን እያንበረከከ የኖረ፣ በፍቃደ እግዚአብሔር የተሰየመ፣ ስዩመ እግዚአብሔር የሆነን መንግሥት “ለሕዝብ አልሰራህምና ስልጣን ለሕዝብ መልስ፣ መሬት የሚያርሰው ሕዝብ ንብረት ነውና ለአራሹ ሕዝብ ይገባል” ብሎ የተቃውሞ ጥያቄ ማንሳት በዚያ ዘመን ከከባዶች ሁሉ የከበደ የድፍረት ድፍረት ነበር፡፡ በዚያ ዘመን ዋናው የሀብት ምንጭ መሬት የነበረ ሲሆን፣ የባለቤትነት መብት ማስረገጫው ደግሞ የቤተመንግሥት አባል መሆን ወይም ለቤተመንግሥት የቀረቡ መሆን፣ የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት መሆን፣ የዘማች ልጅ፣ አርበኛ ወይም የአርበኛ ልጅ መሆን፣ ከአርበኞች መዛመድ ወዘተ የመሬት ባለቤት ለመሆን ቅርብ ያደርግ ነበር፡፡ ቤተመንግስት አካባቢም አገልግሎና ደጂ ተጠንቶም መሬት ማግኘት ይቻል ነበር፡፡ በዚያን ዘመን የሀብት ምንጭ በስልጣን ላይ ካሉት መወለድ፣ ሥልጣን መያዝ፣ ደጅ ጥናትና አገልጋይነት ነበሩ፡፡ በተለይም ወደ ንጉሡ ቀረብ ያለ ሰው የፈለገውን ያህል መሬት በፈለገው አካባቢ ማግኘት ይችል ነበር፡፡ ቀደምት ይዞታው የማም ይሁን የማ (ብቻ የገበሬ ይዞታ ይሁን እንጂ) ደጅ ጠኝው ከንጉሡ ልብ የገባ ከሆነ የጠየቀውን መሬት ያገኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም መሬት ሁሉ የንጉሡ ነበራ!

ያ ትውልድ ይህን በዘርና በጥቅም እንደሸቦ የተጋመደ ወገንተኛ ስርዓት ነበር በቆራጥነት የተጋፈጠው፡፡ ስለገበሬው፣ ስለአርሶ አደሩ፣ ስለጭቁኑ አምራች ላብአደር ነፃነት ሲል ነበር ደብተሩን ይዞ አደባባይ በመውጣት ከዚያ ሥርዓት ጋር ፊትለፊት የተጋፈጠው፡፡ ስለሰብዐዊ ሀዘኔታ አይደለም፣ ስለአክቲቪስትነትም አልነበረም፡፡ ያን ጊዜ የሕዝብ ድህነት እየተባባሰ መሄድ፣ የሀገር ኂላቀርነት፣ ውድቀትና አሳዛኝ ድህነት በአንድ በኩል፣ የአገዛዙ ስለሕዝብና ስለሀገር ደንታቢስ መሆን፣ “የአስረሽ ምቺው” ሕይወት በሌላ በኩል ነበር ትውልዱን ለትግል ያነሳሳው፡፡ ድህነት፣ ርሀብ፣ ስደትና ውርደት፣ የሰዎች ውርደት፣ የሕዝብና የሀገር ውርደት እያደገና እየተስፋፋ የመጣበት ዘመን በመሆኑ ይህ ሁኔታ ትውልዱን በቁጭትና በቆራጥነት ለትግል እንዲነሳና ስለክብሩም እንዲሟገት አድርጎታል፡፡ ይህ አንዱና ትልቁ ቁምነገራችን ነው፡፡ የሰው ልጅ ሲበደል አይቶ ዝም ማለት፣ ስለራስ እንጂ ስለሌላው ደንታቢስ መሆን፣ እኔ ልኑር እንጂ ስለሌላው ምን አገባኝ? ማለት ለሰው ልጆች ሁሉ የማይገባ ባህሪይ ነው፡፡ በሬ እንኳን ጓደኛው በሬ ታርዶ ፈርሱ ሲሸተው ያጓጉራል፡፡ ከብቶች ሲመሽ ሰብሳቢ ካጡ ወይ ወደበረታቸው ይገባሉ፤ ወይ ደግሞ በአንድ ላይ ከትመው ይተኛሉ፡፡ በዚህን ሰዓት አውሬም አይደፍራቸውም፡፡ ይህን የሚያደርጉት አውቀውትና አምነውበት ነው፡፡ ምክንያቱም ሲመሽ ከተበታተኑ አውሬ እንደሚያጠቃቸው ያውቃሉ፡፡ እኛ ግን ሰዎች እንደሰውነታችን አንዳንድ ጊዜ በተለይም ሲመቸንና ሲደላን የሌሎች ሰዎች ችግር አይታየንም፣ የሰው ርሃብ ርሃብ አይመስለንም፣ የሰው ልጅ ተርቦና ተጠምቶ፣ ጎስቁሎና ተራቁቶ ስናይ ልቦናችን አይሳሳም፣ ቀልባችን አይደነግጥም፡፡ ሕይወት እንደሆነች አንዴ ወደላይ ወጭ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ታች ወራጅ ናት፡፡ ብዙዎቻችን ግን በተለይ ምቾት ላይ ካለን ይህ አይሰማንም፣ ወደኛም የሚመጣ አይመስለንም፡፡ አንዲት ፈረንሳዊት እመቤት ሰዎች ተርበው ዳቦ፣ ዳቦ እያሉ ሲጮሁ ሰምታ “ለምን ኬክ አይበሉም” ያለችው አይነት ማለት ነው፡፡

የዛን ዘመን ትልድ ታዲያ ይህን ነበር አይቶ መታገስ ያልቻለው፣ የዚህን ሕዝብ መገፋት እያየ አንጀቱ የተላወሰበትና ስለዚች አገርና ስለዚህ ሕዝብ መሞት ጽድቅ ነው፣ ይህን ዓይነቱንም ግፍ ከማየት ሞት ግልግል ነው ብሎ ነበር ጠመንጃን በደብተር ግብግብ የገጠመው፡፡ ለዚህ ነበር ጀግናው ገርማሜ ንዋይ “እኛ ባይሳካልንም መንገድ ያሳየነው ሕዝባችን መነሳቱና ትግሉን ጫፍ ማድረሱ አይቀርም” ብሎ በቤተ መንግሥት መሣሪያ የመዘዘው፡፡ ለዚህ ነበር ጀግናው ታከለ ወ/ኃዋርያት ሲታሰር ሲፈታ ኑሮ መጨረሻ ላይ ተታኩሶ ሕይወቱን የሰዋው፡፡ እርሱ ሲሞት የዝም ብሎ ሞት አልነበረም የሞተው፤ የነፃነት ጥሪ አድርጎ፣ ትግሉን ለትውልድ አስተላልፎ፣ ለትውልዱም አደራ ትቶ ነበር እንጂ፡፡ የዚያ ዘመን ትውልድ ለዚህ ወይም ለዚያ ዘር ወይም ነገድ፣ ጎሳ ወይም ብሔር አልታገለም፣ ስለ ሕዝብ በደል፣ ስለሰዎች ልጆች “ሰብዐዊ ውርደትና ጭቆና ለምን” ብሎ ነበር የተነሳው፡፡
***(የመጨረሻው ክፍል በቀጣዩ ሳምንት)***

# ኢትዮጵያ የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ምን ግዜም አያስፈልጋትም !



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

በአለማችን በርካታ አገሮች ሌላ አማራጭ ስለአጡ የኑክሌር ሐይል ማመንጫ ገንብተዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ አገሮች ሌላ አማራጭ፣ በሆነ መንገድ ቢያገኙ፤ ይህንን የኑክሌር ሐይል ማመንጫ ለመዝጋት ጊዜም አያባክኑም፡፡ ለምሳሌ አሁን በነዳጅ የበለፀጉ የአረብ አገሮች፣ በአመዛኙ ሐይል የሚያመነጩት ከተፈጥሮ ጋዝ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን እጃቸው ላይ ከፍተኛ የሚባል የገንዘብ ሐብት ስላላቸው፣ የነዳጅ ወይም የተፈጥሮ ሀብታቸው መጠኑ እየቀነሰ በመሄዱ፤ ፊታቸውን ወደ ኑክሌር ኃይል ማመንጫ በማዞር ላይ ናቸው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን የተትረፈረፈ ኃይል ከውሃ፣ ከንፋስ፣ ከከርሰ ምድር እንፋሎት ማመንጨት እየቻልን፤ የኑክሌር ኃይል ለመ ገንባት ማሰባችን በእጅጉ የሚያሳፍር ነው፡፡

ዛሬ በጠ/ሚ/ር ዐቢይ የሚመራው መንግስት ምናልባት ተሳክቶለት የኑክሌር ሐይል ማመንጫ መገንባት ቢችል፤ የሚቀጥለው የግንዛቤ ችግር ያለበት መሪ ደግሞ፤ “ለምን የኑክሌር ቦንብ አንገነባም” ሊል ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ አገሪቷ እንደ ኢራን ልትወጣው ወደማትችለው አዘቅት ውስጥ ይከታታል፡፡ ከፍተኛ መገለል፣ ማዕቀብ ወዘተ ሰላባ ልትሆን ትችላለች፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ከንፋስ ብቻ 1.3 (አንድ ነጥብ ሶስት) ሚሊዮን ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም እያለን፣ ከውሃ 45.000 (አርባ አምስት ሺ) ሜጋ ዋት ማመንጨት እየቻልን ስለ ኑክሌር ማሰቡ በራሱ የዕብደት ያህል የሚያስገርም ነው፡፡

እንኳን መገንባቱ ለጥናቱ የሚባክነው የሕዝብ ሐብት እንደተለመደው የተወሰኑ ግለሰቦች ኪስ ከማደለብ በስተቀር፤ ለኢትዮጵያ ሕዝቦችና ለአገሪቱ የሚፈይደው ምንም ነገር የለም፡፡ አለማችን ሁለት ዋና ዋና የኑክሌር ኃይል ማመንጫዎች አደጋን አስተናግዳለች፡፡ የመጀመሪያው በቀድሞው ሶቭየት ሕብረት ቻርዋቤል ሲሆን ሁለተኛው፤ ደግሞ በጃፓን ፉኩሽማ የሚባለው የኑክሌር ሐይል ማመንጫ ያደረሰው አደጋ ነው፡፡

ጃፓን ውስጥ በደረሰው የኑክሌር አደጋ ምክንያት ከፍተኛ የሚባል የውቅያኖስ አካል በኑክሌር ዝቃጭ በመበከሉ፣ የውቅያኖስ አሳዎች ሁሉ መበላት የማይችሉበት ደረጃ ደርሰው ነበር፡፡ ከላይ በተጠቀሱት የኑክሌር አደጋዎች ምክንያት እስከ አሁንም በርካታ ሕፃናት ከተለያዩ ችግሮች ጋር እየተወለዱ ነው፡፡

እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ችግር እየተፈጠረ ያለው ለሳይንስ ከፍተኛ ትኩረት በሚሰጡና በሰለጠኑ ሕዝቦች አገር ነው፡፡ እኛ ምንም ሳይቸግረን እጅግ ሌሎች በቀላሉ ልናስወግዳቸው የምንችላቸው ችግሮች እያሉብን፣ ዘለን ያለአቅማችን ችግር ለመበደር መሞከር በእውነቱ በጣም የሚያሳፍር ነው፡፡ ያለንን 70 ሚሊዮን የሚታረስ መሬት አርሰን፣ ስንዴ ማምረት ያልቻልን ሕዝቦች የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ለመገንባት ማሰባችን የአለም መሣቂያ ከመሆን አያድነንም፡፡

ይልቁንስ ያሉንን የኃይል ማመንጫዎች በአግባቡ ቶሎ ቶሎ ገንብተን ለጎረቤቶቻችን በመሸጥ፤ እነዚህ ጎረቤት አገሮች ፊታቸውን ወደ ኑክሌር ኃይል ማመንጫ እንዳያዞሩ ማድረግ ነው ያለብን፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ጎረቤት አገሮች በቀላሉ በቂ የኃይል ማመንጫ መገንባት ስለማይችሉ ፊታቸውን ወደ ኑክሌር ካዞሩና አደጋ ከደረሰ፤ አደጋው እኛ ጋ መምጣቱ አይቀርምና ነው፡፡

በተለይ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከሁሉም የጎረቤት አገሮች ጋ ጤነኛ ግንኙነት ላይ ያለች በመሆኑ፤ ይህንን ጤነኛ ግንኙነት ቶሎ ቶሎ በኢኮኖሚ ግንኙነት በማስተሳሰር፣ እንዲጠናከር ማድረጉ በእጅጉ የተቀደሰ ሐሳብ ነው፡፡

የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ለአደጋ ሊጋለጥ የሚችልበት በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ለምሣሌ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ የኃይል ማመንጫ ውስጥ ያሉ ሰራተኞች በሚሰሩት ስህተት፣ በሽብር ጥቃት እና በሌሎችም ምክንያቶች በቀላሉ ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል፡፡ በመሆኑም እንደ ኢትዮጵያ ላለ አገር በምንም መልኩ የማይመከር ሐሳብ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት ያመረትነውን የኤሌትሪክ ኃይል ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚው ጋር ማድረስ እንዳልተቻለ በተለያየ ጊዜያት በሚወጡ ዘገባዎች ለማየት ችያለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ዋናው ምክንያት ኢኮኖሚያችን ደካማ በመሆኑ፣ ያመረትነው ኤሌትሪክ የሚፈልገውን መሰረተ ልማት ማለት እንደ ሰብእስቴሽን (substation) ማስተላለፊያ መስመር የመሣሠሉ ግንባታዎች በበቂ ሁኔታ በመገንባት፤ ብክነትን አስቀርተን ሐብት መፍጠር ያልቻልንበት ሁኔታ እያለ ሊጨበጥ የሚችል ነገር ማሰቡ በራሱ የሚገርም ነው፡፡

**...ጃፓን ውስጥ በደረሰው የኑክሌር አደጋ ምክንያት ከፍተኛ የሚባል የውቅያኖስ አካል በኑክሌር ዝቃጭ በመበከሉ፣ የውቅያኖስ አሳዎች ሁሉ መበላት የማይችሉበት ደረጃ ደርሰው ነበር፡፡ ከላይ በተጠቀሱት የኑክሌር አደጋዎች ምክንያት እስከ አሁንም በርካታ ሕፃናት ከተለያዩ ችግሮች ጋር እየተወለዱ ነው...**

በአሁኑ ጊዜ ስለ ኑክሌር ቴክኖሎጂ የሚያስቡ አገሮች፣ በሌሎች ሳይንሶች በቂ የሚባል እድገት ካስመዘገቡ በኋላ ነው ወደ ኒኩሌር ሳይንስ ፊታቸውን ያዞሩት፡፡ እነዚህ አገሮች በብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች፣ በፔትሮ ኬሚካል ኢንዱስትሪ፣ በማሽን ግንባታ ኢንዱስትሪ ወዘተ አቅማቸውን ካጎለበቱ በኋላ ነው ወደ ኑክሌር ሳይንስ ፊታቸው ያዞሩት፡፡ እኛ ተፈጥሮ ያበቀለውን ቡና አምርተን ወደ ውጭ በመላክ የተሻለ ሥራ መስራት ባልቻልንት ሁኔታ፤ ዘለን ስለ ኑክሌር ማሰቡ በራሱ የጤና አይመስለኝም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት እንኳን ስለ ኑክሌር ሳይንስ ልናወራ ይቅርና በዚህ ዙሪያ ምንም ዓይነት የጥናት ኮሚቴ፣ ወይም ይህንን ተግባር የሚያጠና ተቋም ማቋቋም በምንም መልኩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ገንዘብም መባከን የለበትም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የከርሰ ምድር እንፋሎት ኃይል ማመንጫ እስከ አሁን ባለው ጥናት ማመንጨት የሚቻለው የኃይል መጠን አሁን እያመረትን ካለው ኤሌትሪክ በእጥፍ የሚበልጥ ሆኖ ሳለ፣ ከውሃ ሃይል ከ45ሺ ሜጋ ዋት በላይ ማምረት ከተቻለ እንደ አፋርና ሶማሌ ክልል ደግሞ ከፍተኛ የፀሐይ ኃይል ማምረት እየተቻለ፣ ከላይ እንደተጠቀሰው ከነፋስ 1.3 ሚሊዮን ሜጋ ዋት ማምረት እየተቻለ፣ (በነገራችን ላይ 1.3 ሜጋ ዋት አሁን በመላው ዓለም ከተለያዩ ምንጮች የሚመረተው የኤለትሪክ ኃይል ጋር ይቀራረባል) ስለ ኑክሌር ኃይል ማመንጫ ማውራት መጀመራችን አስቂኝም አሳፋሪም ነው፡፡

የአንድ አገር መሪ በአቋራጭ መንገድ በማሰብ ብቻ ነው አገርን የሚለውጥ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻለው፡፡ እውነቱንና በዓለም ላይ ያለውን እጅግ የተሻለውን ሳይንስ የሚያውቁ ኢትዮጵያዊ ምሁራን፤ አገራችን ከበቂ በላይ አለ፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ የተናገሩትን ሁሉ የሚያዳንቁና የሚያጨበጭቡ አድርባዮችን በዙሪያቸው ሰብስበው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከኋላ ቀርነትና ድህነት አወጣለሁ ብሎ ማሰብ በፍፁም የሚሳካ አይሆንም፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያለን አገር የሚመራ መሪ፣ እያንዳንዱ ቀን ባለፈ ቁጥር አንድ አመት እንዳለፈ መቁጠር መቻል አለበት፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢኮኖሚውም፣ በፖለቲካውም ገና ሁሉንም ነገር ከመንግስት ነው የሚጠብቀው፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በመሬት አስተዳደር፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ ገና ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆን ሥልጣን አልተሰጠውም፡፡ በዚህ ዙሪያ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች በእጅጉ ቀድመውን ሄደዋል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው አመራር በዚህ ዙሪያ ቢሰራ የተሻለ ነው የሚል አስተሳሰብ አለኝ፡፡

# የዘውግ ፖለቲካ . . .

ከገጽ 10 የዞረ

ብቻ ሕጋዊና ተስማሚ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነ መንግሥት የባእድ ሥርአት በመሆኑ፣ በመሰረቱ አድላዊና ጨቋኝ ከመሆን ሊያመልጥ አይችልም ይላል፡፡ ለዚህ አመለካከት የበደልና የጭቆና ዋና ምክንያት ህዝቦች የራሳቸው ዘወግ አባል ያልሆኑ ገዢዎች ሥር ሲወድቁ ነው፡፡ የተወረሰው የቀድሞ ባህል ስለ በደልና ጭቆና ይህን ስለማይል ዘውጋዊ ማንነት የተቀመመ መሆኑን በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ የሕዝቦች የባእድ ሥርአት ቀንበር ስር መውደቅ ሊሆን የሚችለው ሁሉ እንዳይሆን ስላደረገ፣ ብሩህ ተስፋ ማለት በመገንጠልም ሆነ በሌላ መንገድ ዘውጋዊ መንግስት ማቋቋም ነው፡፡ ይህ ሲሆን ብቻ ነው የተወረሰው ባህል መለያዎች እምቅ ችሎታ እውን ሊሆኑ የሚችሉት፡፡

አንዳንድ ምሳሌዎችን እናንሳ፡፡ የኤርትራን ነጻነት ትግል ያጀበው ተስፋ “ከኢትዮጵያ ጨቋኝና ሕገ ወጥ አገዛዝ መላቀቅ፣ ኤርትራን የአፍሪካ ታይዋን ያደርጋታል” ይል ነበር፡፡ እንዲሁም የኦሮሞ ምሁራን “የኦሮሞ ገዳ ሥርአት ዴሞክራሲያው ይዘት ያለውን የማዘመን ችሎታ እውን ሊያደርግ ያልቻለው በአማራ ቅኝ አገዛዝ ሥር በመውደቁ ነው” ይላሉ፡፡ በትግራይ ምሁራን ዘንድ ተመሳሳይ አቀራረብ እናገኛለን፤ “ትግራይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ምንጭና መሰረት ብትሆንም፣ የአማራ ገዢ መደብ ተፎካካሪ ተነስቶ የበላይነቱን እንዳያጣ ትግራይን በማግለል በሁሉም መስክ እንድትቀጭጭ አድርጓታል” ይላሉ፡፡

## የተገኙ ውጤቶች

ዘውግ ተፈጥሮአዊ መሰረት ያለው የማንነት ተቀዳሚ መግለጫ ነው የሚለው ንድፈ ሐሳብ፤ ዘውጋዊ ግጭቶችን ለማቆም የሚሰጠን የአንድ መንገድ መፍትሄ ብቻ ነው፡፡ እሱም የማይስማሙ ዘውጋዊ ማህበረሰቦችን በመለያየት አዳዲስ አገሮችን መፍጠር ነው፡፡ ይህ የባልካኒዜሽን መፍትሄ ልዩነትን መከለል ለዴሞክራሲና እድገት ዋስትና እንደማይሰጥ ይዘነጋል፡፡ ይልቁኑ የሌሎች አገሮች ታሪክ እንደሚያሳየን ልዩነት ሲበወዝ ነው የአንድ አገር ችሎታ የሚያድገው፡፡ በተጨማሪ ንጹህ የሆነ ባህል፣ ድሮም ኖሮ አያውቅም፤ ወደ ፊትም አይኖርም፡፡ በተለይ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ የባህሎች መደበላለቅ (በአመዛኙ ከምዕራባዊ ሥልጣኔ በተወሰዱ እሴቶችና አሠራሮች) አይቀሬ ክስተት ነው፡፡ ሌላው መጠቀስ ያለበት ዘውግ የማንነት ተቀዳሚ መገለጫ ማድረግ የሚረዳው፤ አንድ ሰው ማንነቱን የሚያበጀው የተለያዩ መግለጫዎች በማዳመር መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ኦሮሞ፣ ኢትዮጵያው፣ አፍሪካዊ፣ አስተማሪ፣ ክርስቲያን ወይም እስላም ወዘተ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ መሰረት ግን ግለሰቡን የሚለየው ሳይሆን ከሁሉ ጋር የሚያጋራውና ሰው የሚያደርገው የሰው ተፈጥሮ ስለሆነ የተቀዳሚነት ቦታ የሚይዘው የሰው ተፈጥሮ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የግለሰብ መብቶች ከዘውጋዊ መብቶች ቅድሚያ እንዳላቸው ብቻ ሳይሆን በሕዝቦች መካከል ምንም መሰረታዊ ቅራኔ እንደሌለ ያረጋግጣል፡፡

## ዘውግ መሳሪያ ነው የሚለው አመለካከት ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ያስተምራል

1) ዘውጋዊ መለያዎች ክብደት የሚያገኙት ልሂቃኖች ለሥልጣን ፉክክር ሕዝብን ለማነሳሳትና ለማደራጀት ሲጠቀሙባቸው ነው፡፡

2) ችግሩ የማንነት አለመጣጣም ሳይሆን፤ የሥልጣን ጥያቄ በመሆኑ አስፈላጊ የሆነውን የፖለቲካ ለውጥ በማድረግ ዘውጋዊ ግጭቶች ለማቆም ይቻላል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው፣ ይህ አመለካከት ለምን ሕዝቦች የልሂቃኖችን አመራርና እቅድ እንደሚቀበሉ አያስረዳም፡፡ ለዚህ ጥያቄ ነው ሶስተኛው ንድፈ ሃሳብ መልስ የሚሰጠው፡፡

> ...እንደ ምሳሌ የኦሮሞነትን ፖለቲካ ብንወስድ፤ ለብዙ አስተያየት ሰጪዎች ግልጽ ያልሆነው የዛሬው ኦሮሞ ከቀድሞው ኦሮሞ የተለየ መሆኑ ነው፡፡ “የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ አደረጃጀት እንለውጥ” የሚሉ ፓርቲዎችና ምሁራን የሚረሱት ይህ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሂደት የወለደው ባሕላዊ ለውጥ መፈጸሙን ነው...

## የፈጠራ ኃይል ድርሻን ስለሚያካትት ሶስተኛው ንድፈ ሃሳብ ሶስት ቁም ነገሮችን ያስጨብጠናል

1) ሕዝብንና ልሂቃኖችን የሚያጣምረው የዘውጋዊ አመለካካት የመለየት ስልት ነው፡፡ የተወሰኑ መለያዎች ላይ በመመርኮዝ አመለካካቱ አንድን አገር በተበዳይና በበዳይ የሚከፋፍል ብቻ ሳይሆን፤ የበደሉ ምክንያት ማንነት ነው ይላል፡፡ በደሉን ከማንነት ጋር ስለሚያቆራኝ ኃይለኛ ስሜቶችን ይቀሰቅሳል፤ በዚህም የተነሳ ከፍተኛ የማነሳሳት ችሎታ አለው፡፡

2) ተበደለ የተባለውን ማንነት በአዲስ መልክ ስለሚያድስና ስለሚያሸበርቅ፣ ዘውጋዊ ንግግር የአመለካከት ለውጥ ያስከትላል፡፡ እንደ ምሳሌ የኦሮሞነትን ፖለቲካ ብንወስድ፤ ለብዙ አስተያየት ሰጪዎች ግልጽ ያልሆነው የዛሬው ኦሮሞ ከቀድሞው ኦሮሞ የተለየ መሆኑ ነው፡፡ “የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ አደረጃጀት እንለውጥ” የሚሉ ፓርቲዎችና ምሁራን የሚረሱት ይህ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሂደት የወለደው ባሕላዊ ለውጥ መፈጸሙን ነው፡፡ በተጨማሪም የባሕል ለውጥ ሁሉን ዘውጎች ስለሚመለከት የወደፊቷን ኢትዮጵያ ስናስብ በትዝታ ሳይሆን በፈጠራ ችሎታችን ዓይን ቢሆን ውጤት ይገኛል፡፡ ጊዜው የሚጠይቀው የኢትዮጵያ አንድነትን ማቆየት ብቻ አይደለም፤ ምክንያቱም ልትቆይ የምትችለው በፈጠራ ስንቀይራት ነው፡፡

3) የባሕል መለወጥ ባሕሪይ የሚያሳየን ምንም ግትር ወይም የማይለወጥ ማንነት እንደሌለ ነው፡፡ በመሆኑም የምናቀርበው መፍትሄ የማይሆን አቅጣጫ በመያዝ ዘውጋዊነት ባለበት ደርቆ እንዲቀር ከማደረግ መጠንቀቅ አለብን፡፡ አዎንታዊ ውጤት የሚገኘው ዘውጎች ሁሉ የተከሰተውን ለውጥና የማንነትን ተለዋዋጭነት በመቀበል አንድነትን በአዲስ መልክ የሚቀርጽና የሚያሳምር ኢትዮጵያዊነት ሲፈጥሩ ነው፡፡ ልክ የአንድ ወንዝ ስፋትና ኃይል የብዙ መጋቢ ወንዞች መደበላለቅ ውጤት እንደሆነ ሁሉ፤ ዘውጎችም ከመገፋፋት ይልቅ ሲዋሃዱ ከእነሱ በላይ የሆነ ውጤት፣ ማለትም ብሄራዊ አንድነትና ችሎታ ይፈጥራሉ፡፡ እዚህ ላይ አንድነቱ የዘውጎች ስብስብ ሳይሆን የእነሱ አስተዋጽኦና ውህደት የሚያስገኘው የበላይና አዲስ ውጤት መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**መሳይ ከበደ**
https://udayton.academia.edu/MessayKebede

# “የማይታፈን ጩሽ” ሆኖ ብቅ ያለው ኢሳትና፤ ከአነጋጋሪው የቦርዱ ውሳኔ ጀርባ ያሉ እውነታዎች!



ጃፋር ሰዩም

## ቅድመ ታሪክ

የዛሬ 9 አመት፣ በምርጫ 2002 ዋዜማ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመርያ የሆነው የህዝብ ቴሌቪዥንና ሬዲዮጣቢያ የሆነው፣ “የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን”(በእንግሊዘኛው ምህጻረ ቃል “ESAT”) የተሰኘው የቴሌቪዥን ቻናል ፣በአረብ ሳት የቴሌቪዥን ማስተላለፊያ ሞገድ የኢትዮጵያን አየር የተቆጣጠረው።

ወቅቱ ሀገሪቷ በነበረችበት ከባድ አፈና ምክንያት፣ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመነበር የነበሩትን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ወህኒ ተቆልፎባቸዋል። ሕወሓት/ ኢህአዴግ በፓርላማው ባጸደቀው አዲሱ ጸረ ሽብር ህግ ምክንያት፣ የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች አገራቸውን ለቅቀው ለስደት ተዳርገዋል።

ሀገሪቷ ከባድ የፍርሃት ደመና አጥልቶባታል፡ ፡ አፋኙ ሕወሓት/ኢህአዴግ ከ1997ቱ ምርጫ “ስህተቱ ተምሮ”፤የትኛውንም የተቃውሞና የህዝብ ድምጽ ለማፈን ሙሉ ጉልበቱን በመጠቀም ጨፍልቆ በማሰር፣ በመግደልና በማሰደድ ጸጥ ረጭ አድርጎ ምርጫ 2002ን ሊወጣ ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ “ምርጫው” ሊገባ ሳምንት የማይሞላ ጊዜ ሲቀረው፤“ጥቂት ጩሶች” በሕወሓት የታጠረውን የፖለቲካ አየር ጥሰው ገቡ።

ከዘጠኝ አመት በፊት በምስረታው ወቅት ዋሽንግተን ዲሲ በተዘጋጀ መድረክ ላይ፣ የአሁኑ የኢሳት ስራ አስኪያጅ አርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ ሁኔታውን ሲገልጽ እንዲህ አለ፦“ኢትዮጵያ ውስጥ ነጻ ሚድያ፣ ነጻነት እስኪመጣ ድረስ አናቆምም ያሉ፣ የወሰኑ፣ የቆረጡ ጩስ ሆነው መጡ፤ ደፋርና ጩስ መውጫ አያጣም እንደሚባለው ጥቂት ጩሶች ይሄን ቴሌቪዥን ፈጥረዋል። ጩስ! ማፈን የማይቻል

ጩስ!” በማለት ዳያስፖራው በታሪኩ ከሰራቸው ትልቅ ነገሮች ውስጥ አንዱ የሆነውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ምስረታን አብስሯል።

## ድጋፍ ሰጪ ቻፕተሮች

60 የድጋፍ ቻፕተሮች በመላው ዓለም ያለው ኢሳት፣ የገቢ ምንጩን በዋነኝነት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ በማድረጉ ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን ለዚህ ቴሌቪዥን ውድ ጊዜያችውን፣ ገንዘባቸውንና እውቀታቸውን ለዓመታት ዋጋ ከፍለውበታል። እህቶቻችን በአውሮፓ፣ አሜሪካና አውስትራሊያ በየከተማው የኢሳት ገቢ ማሰባሰቢያ ላይ ተገኝተው፣ገንዘባቸውን አዋጥተው፣ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው፣ ሳንቡሳና ቡና ሸጠው ያቋቋሙት የኢትዮጵያውያን የሚዲያ ተቋምነው ኢሳት።

ከጠንካራ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ቻፕተሮች ውስጥ አንዱ የሆነውን የዳላስ ድጋፍ ሰጪ ቻፕተርን ለማሳያነት ልጠቀም፦

ትደግ(እናትዬ) ኑሮዋን በአሜሪካን ሀገር ዳላስ ከተማ ካደረገች 12 ዓመታት አስቆጥራለች። የኢሳት የዳላስ ድጋፍ ሰጪ ቻፕተር አዘጋጅ ኮሚቴ ናት። በዳላስ የኢሳት የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ሲካሄድ ከዳላስ የኢሳት ደጋፊዎች ጋር በመሆን አዳራሽ ያመቻቻሉ፣ ማስታወቂያ ይሰራሉ፣ በጸሐይና ብርድ እየተንከራተቱ፣ በየስቶሩና አብያተ ክርስትያኑ ማስታወቂያ ይሰጣሉ/ይለጥፋሉ፣ የመግቢያ ቲኬት ይሸጣሉ፣ ፍላየር ይበትናሉ፣ ከሌሎች ግዛቶች ተጋባዥ እንግዶች ሲመጡ ኤርፖርት ሄደው፣ ተቀብለው ወደ ሆቴል ማድረስ፣ እንዲሁም እንግዶቹን ከሆቴል ወደ ስብሰባ አዳራሹ ማምጣት የትደግና ጓደኞቿ የዳላስ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ አዘጋጆች ለ9 አመታት ያለፉበት ጉዞ ነው።

ኮሚዲያኖቹ ክበበው ገዳና መስከረም በቀለ፣ ሻምበል በላይነህ፣ አበበ ፈቃደ፣ ኤርሚያስ ለገሰ፣ መሳይ መኮንን፣ ሲሳይ አጌና፣ ምናላቸው ስማቸው፣፣ ርዕዮት አለሙና ሀብታሙ አያሌው በእንግድነት ዳላስን ከረገጡ ሰዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

እነ ትደግ ስራቸው በዚህ ብቻ አይቆምም። ከመግቢያ ቲኬት ከሚገኘው ገንዘብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመፍጠር፤የኢትዮጵያውያን አይንና ጆሮ የሆንውን ኢሳትን መደገፍ የሚችሉበትን የተለያየ ዘዴ ይጠቀማሉ፡ ፡ የአባላት ወርሃዊ መዋጮ፣አመታዊ በአሉ ላይ የሚሸጡ ባንዲራዎች፣ ቲሸርቶች፣ ቁልፍ መያዣዎች፣መፅሃፎች፣ኩባያዎችን ለሽያጭ በማቅረብ ከዛ የሚገኘው ገቢ ለኢሳት እንዲውል ይደረጋል። ሌላኛው ጨረታ ነው። የአንድን በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ተጽዕኖ ፈጣሪ ወይም ታሪካዊ ግለሰብ ምሥል፣ለጨረታ ያቀርቡታል። በጨረታው የሚያሸንፈው ሰውም ያሸነፈበትን ምስል ወስዶ ገንዘቡን ለኢሳት ገቢ ያደርጋል። በዚህም ሳይቆሙ ቡናና ሳንቡሳ በመሸጥ ለኢሳት ገቢ ያስገባሉ። ቡና አፍልተው ለታዳሚው በሚሰጡበት ወቅት፣ ቡናውን የሚጠጣው ሰው ደስ ያለውን ገንዘብ እየከፈለ ይወስዳል። “አንድ ሲኒ ቡና እስከ 100 ዶላር ድረስ የሚሸጥበት አጋጣሚ በርካታ ነው” ትላለች፣ ትደግ ያለፈውን ስታስታውስ።

ኢሳት በጠንካራ አመራሮቹና ደጋፊዎቹ ምክንያት በ9 አመት ውስጥ ዳላስ ላይ 10 ግዜ ሻማ አብርቶ፣ ኬክ ቆርሶ፣ የምስረታ በአሉን ማክበሩን ለማሳያነት በመጥቀስ፣ “ዳላስን ከኢሳት፣ ኢሳትን ከዳላስ መነጠል አይቻልም” ይላል ከዳላስ ቻፕተር አስተባባሪዎች ውስጥ አንዱ የሆነው ሰለሞን።

የዳላስን ለማሳያነት ብናነሳም ከአሜሪካ እስከ ካናዳ፣ ከአውሮፓ እስከ አውስትራሊያና ደቡብ አፍሪካ በመላው ዓለም ያሉ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ቻፕተሮች፣ ዋጋ ከፍለው የህዝብ ድምጽ በመሆን ትልቅ ሰርተዋል። ያለምንም ክፍያ ያለፉትን 9 አመታት የቦርድ አባል ሆነው በመምራት ለሀገራቸው ትልቅ ውለታን የዋሉ፣ ሚድያው እንደሚድያ የገለልተኝነት ሚናውን እንዲወጣ ቦርዱ ትልቅ ሀላፊነትን ተወጥቷል።

## የኢሳት ቦርድ አባላት እነማን ናቸው?

ሰማኽኝ ጋሹ የተባለ ግለሰብ በፌስቡክ “ኢሳትን የሚመሩት የቦርድ አባላት እነማን እንደሆኑ ይነገረን? እንደ ጌታቸው አሰፋ መደበቁን ምን አመጣው?” የሚል ጥያቄ ባነሳበት ፖስት፣ የቀድሞው የኢሳት ስራ አስኪያጅ ጋዜጠኛ አበበ ገላው በፈረንጅ አፍ “ይሄ የሚልዮን ዶላር ጥያቄ ነው” የሚል ጠንከር ያለ አስተያየትን ሰጥቶታል። ብዙ ሰዎች የኢሳት የቦርድ አባ ላትን ማንነት በተመለከተ፣ በተለይ ከቅርብ ጊ ዜ ወዲህ ሲያነሱ መመልከት የተለመደ ነው።

በሕወሓት የአገዛዝ ዘመን ከገዢው ፓርቲ የሚደርስባቸውን የስለላ መዋቅር ለማለፍ በአውሮፓና አሜሪካ የሚኖሩት የኢሳት ቦርድ ሀላፊዎች ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው። ሁሉም ስለማንነታቸው የየራሱን ግምት ይሰነዝራል እንጂ በትክክል የሚያውቃቸው ሰው በጣም ጥቂት ነው። ሕወሓት ከአሜሪካ የደህንነትና መከላከያ ኃይል ጋር በመመሳጠር በፓርላማው በአሸባሪነት ፈርጆ የቦርድ አባላቱን ለማጥቃት፣ ሚድያውንም ለማዘጋት ስለሚንቀሳቀስ የቅጽል ስሞችንና ኮዶችን በቋሚነት ይጠቀሙ እንደነበር የቦርድ አባላቱ ያስታውሳሉ።

1) ዶ/ር አዲሱ መንገሻ (የኢሳት ቦርድ ሰብሳቢ)
2) ዶ/ር አዚዝ መሐመድ (ቴክኒካል ዲፓርትመንት ሀላፊ፣ ዳላስ )
3) ዶ/ር ሙሉዓለም አዳሙ (የድጋፍ ሰጪ ዲፓርትመንት ሀላፊ፣ ኖርዌይ)
4) አቶ ዘላለም ተሰማ (የስራ አስፈጻሚ አባል፣ ለንደን)
5) አቶ ነአምን ዘለቀ(የስራ አስፈጻሚ አባል፣ ዲሲ)

እነዚህ የኢሳት የቦርድ አባላት ሆነው ሚድያውን እያንቀሳቀሱ በበላይነት እያስተዳደሩም ይገኛሉ፡ ፡ ከኢሳት ጋር ላለፉት 9 ዓመታት የሕወሓትን ጃሚንግ ጨምሮ በርካታ ውጣ ውረዶችን አብረው አሳልፈው፣ ዛሬ ላይ ደርሰዋል። ▶

## የኢሳት ወቅታዊ ፈተና

*ሀገራዊ ለውጡ ወደ ኢሳት ገባ። ኢሳት ላለፉት 9 አመታት ያደረገው ጸረ ሕወሓት ተጋድሎ በድል ተደምድሞ፣ በሀገሪቷ ኢሳት ሲታገልላቸው የነበሩት ነገሮች አንድ በአንድ እየተመለሱ መጡ። ሕወሓትን በመታገል ተጠምዶ የነበረው የዳያስፖራው ሕብረተሰብም ከተቃውሞ ፖለቲካው ጎራ በግማሽ ቀነሰ። በየስቴቱ ያለው የደጋፊ ቡድንና ተቃዋሚ ድርጅቶች ለኢሳት የሚያደርጉት ድጋፍ እየቆመ መጣ። የሕወሓት ፖለቲካ ቀዘቀዘ። የኢሳት ቦርድም ሚድያውን ለአመታት ከሄደበት መንገድ በተለየ መልኩ ወደ ፕሮፌሽናል ጋዜጠኝነት ማምጣትን ፈለገ።*

ለውጡ ጥቂት ወራትን ካስቆጠረ በኋላ፣ ኢሳት በዋሽንግተን ዲሲ፣ ለንደን እና አምስተርዳም ስቱዲዮዎች ያሉ ከ40 የማያንሱ ጋዜጠኞችን ደመወዝ ለመክፈል መንገዳገድ ጀመረ። ቦርዱም የዲሲ ስቱዲዮ ስራ አስኪያጅ የሆነው አርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ በተገኘበት ከሰራተኞች ጋር ከ3 ወራት በፊት ባደረገው ስብሰባ ባጋጠመው ወቅታዊ ችግር ዙሪያ መክሮ በጀት ለመቀነስ አንዳንድ ፕሮግራሞችን ለማጠፍ ወሰነ። የሚወጣበትን ወጪ ያህል እምብዛም አድማጭ የሌለው የኢሳት ሬዲዮ ፕሮግራም ታጠፈ። የዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብን ለመወትወት(lobby) ለማድረግ ተብሎ ለአመታት ይተላለፉ የነበሩት የእንግሊዘኛ ፕሮግራሞች እንዲቆሙ ተደረገ። በጦማር ጋዜጣ የምናውቀው አንጋፋው ጋዜጠኛ በፍቃዱ ሞረዳ በኦሮምኛ ቋንቋ የሚቀርቡ ፕሮግራሞችና የትግርኛ ዜና አዲስ አበባ በተከፈተው የኢሳት ስቱዲዮ እንዲቀርቡ ተደርጎ፣ ከዋሽንግተን ዲሲ በነዚህ ቋንቋዎች የሚተላለፉ ፕሮግራሞች ቦርዱ እንዲቋረጡ አደረገ።

የወጪውን 45 በመቶ ለመቀነስ እየተንቃሳቀሰ ያለው ቦርዱ፤ በነዚህ የሬዲዮ ፕሮግራሞችና ሌሎች ቋንቋዎችን፣ፕሮግራሞችን በማቋረጡ ብቻ የሚፈልገውን ማሳካት አልቻለም። ቀጥሎ ያደረገው ነገር በሁሉም ስቱዲዮ ያሉ ሰራተኞችን ሰብስቦ የቴሌ ኮንፍረንስ በማድረግ ወቅታዊውን ችግር በመግለጽ አካሄዶች ሊቀየሩ እንደሚችሉ በመግለጽ ጋዜጠኞቹ ፕሮግራሞችን አዘጋጅተውና ራሳቸው ስፖንሰር ፈልገው ለኢሳት ማቅረብ የሚችሉበትን መንገድ ጠቆመ። ይህ ካልሆነ ግን ስቱዲዮዎቹን ለማስተዳደር እንደሚቸገሩ የቦርድ አባላቱ ገለጹ። ቦርዱ የአዲስ አበባውን ስቱዲዮ በማቋቋም ላይ ትኩረት አድርጎ፣ ወጪ ከመቀነስ ጎን ለጎን የሙያ ስነምግባር የሚከበርበት ፕሮፌሽናል ሚድያ ለማድረግ እቅዱን ማስፈጸም ላይ ጠንክሮ መስራትን ቀጠለ።

## የውስጥ ውዝግብ

የኢሳት ማኔጅመንትና ቦርድ በዚህ እንቅስቃሴ ላይ እያለ በኢሳት ጋዜጠኞች መካክል አወዛጋቢ አስተያየቶችና ሽኩቻዎች መመልከት ተጀመረ። ልክ እንደየትኛውም ተቋም ኢዲቶሪያል ቦርድ ያለው ኢሳት፣ በኢዲቶርያል የሚወሰነውን ውሳኔ የመቃወም ብቻ ሳይሆን፣ ተቋሙን አፉኝ የማስመሰል አዝማሚያዎች መታየት ጀመሩ። ኢዲቶሪያል ቦርዱ 2 አካላት መካተት ያለባቸውን ነገሮች ሚዛናዊ ሆነው እንዲቀርቡ ይቆጣጠራል። የሚቀርቡ ፕሮግራሞችን ሚዛናዊነትንም መከታተል ሌላኛው የኢዲቶሪ ያሉ ቦርዱ ሀላፊነት ነው። በጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙና በጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ጸጋዬ መካከል

የተደረገው ቃለ ምልልስ መታገድ በማህበራዊ ሚዲያ በከፍተኛ ድምጽ እንዲጮህ ተደረገ። በርግጥም እንደ አቦይ ስብሃት ያሉ የሕወሓት መስራቾችን ጨምሮ ያቀረበው ኢሳት የአንድን ፕሮግራም አዘጋጅ ኢንተርቪው ማገዱ ያልተለመደ ቢሆንም፤ ቦርዱ ግን በራሱ ምክንያት ቃለ መጠይቁ እንዳይተላለፍ አደረገ። ከዚህ በኋላ ቃለ መጠይቅ ያደረገችው ጋዜጠኛ ርዕዮት በሌላ ሚድያ ቀርባ አስተያየትን ሰጠች። ይህም የአንድን ሚድያ ውስጣዊ ችግር በሌላ ሚድያ ማውጣቱ የጋዜጠኝነትን መርህ ከመጻረር ባለፈ ተቋሙን ኢሳትን ቡሁሉም መንገድ የሚጎዳ ሲሆን፣ የርዕዮት ድርጊት የሙያውን ስነምግባር ጠንቅቃ የማወቋን ጉዳይ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከተዋል። እነዚህ ነገሮች እየተካረሩ "ለውጡን የሚደግፉ" እና"ለውጡን የሚቃወሙ" የሚል የ2 ወገን ቡድናዊ አስተሳሰብ፣ በኢሳት ጋዜጠኞች መካከል መፈጠሩን እየጎላ ወጣ።

## የሰራተኞች ቅነሳ

የኢሳት ሰራተኞች የቀረበላቸውን ራሳቸውን ችለው ፕሮግራም እንዲያዘጋጁ የሚያደርግ ዕድል የአምስተርዳም ስቱዲዮ ሰራተኞች የአንድ ወር ጊዜ ብቻ ከተሰጣቸው እንደሚቀበሉት ገለጹና ከኢሳት የደመወዝ መክፈያ ፔይሮል ላይ ሲሰረዙ፣የለንደን ስቱዲዮ ግን ከሰመ። በዚህ ጊዜ የኢሳት ስራ አስፈጻሚ ትልቁን ወጪ ወደሚያወጣበት የዋሽንግተን ዲሲ ስቱዲዮ ፊቱን አዞረና ይህን በትህትና የተሞላ አጭር ኢሜይል ለ5 ሰራተኞቹ ላከና ከስራ ቀነሳቸው።

*"በኢሳት ባጀት ቅነሳ ምክንያት ሥራችሁ የታጠፈባችሁ ሰዎችን ይመለከታል፦*

*ኢሳትን በሚመለከት ባለፉት ዓመታት ላደረጉት አስተዋጽኦ የልብ ምስጋናችን ይድረሰዎ። ኢሳት በአሁኑ ወቅት በገጠመው የገቢ ምንጮች መቀነስን ተከትሎ በወሰደው የባጀት ማስተካከያ እርምጃ ምክንያት የተወሰኑ የሥራ ቦታዎችን ለማጠፍ ተገዷል። ይህን ቅነሳ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማሳነስ በተቻለ ሁሉ መሞከሩን ልንገልጽለዎት እንወዳለን። ሆኖም ግን የኢሳት ባልደረቦችን በየሥራ ዘርፉ ያላቸውን የአገልግሎት ዘመን (seniority) ወይም የፕሮግራም መቀነስን መመዘኛ አድርገን በወሰነው ውሳኔ መሰረት ካዛሬ ከሜይ 31፣ 2019 ጀምሮ የእርሰዎን የሥራ ቦታ ለማጠፍ ተገደናል። ስለዚህ ዛሬ ቀኑ ከማለቁ በፊት የመጨረሻ የሆነውን ክፍያዎን እንዲወስዱ እየጠየቅን ኢሳት ለወደፊትበሚኖረው የሥራ ዕድገት ቅድሚያ ለመስጠት ዝግጁ እንደምንሆን ለመግለጽ እንወዳለን።"*

ሜይ 31፣ 2019

## የኢሳት ስራ አስፈጻሚ

በኢሜይሉ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጡት የቦርዱ ስራ አስፈጻሚ የአገልግሎት ዘመንን ብቻ በመመዘኛነት ተጠቅመው ሰራተኞችን ሲቀንሱ፣ ቅነሳው የጣቢያውን አንጋፋ ጋዜጠኞች አይነካም ነበር። ቦርዱ ይህንን መመዘኛ የተጠቀመበት ምክንያት ላለፉት ዓመታት ምንም አይነት የስራ ብቃት መመዘኛዎችን ባለመጠቀሙ ሲሆን ኢሳት ላይ መጨረሻ የተቀጠረውና በዚህ መመዘኛ የመጀመርያው ከስራ የተቀነሰው ግለሰብ የቀድሞው የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል የነበረው ሀብታሙ አያሌው ነበር። ምናላቸው ስማቸውና እየሩሳሌም ተክለጻዲቅ፣ ልዩ ጸጋዬና ጌታቸው አብዲም ከስራ ተቀነሱ። ይህንን ተከትሎ ውስጥ ለውስጥ ሲብሰለሰል የነበረው ነገር ወደ አደባባይ ወጣ። የተወሰኑት ጉዳዩን

ከአመለካከትና ማንነት ጋር አያያዙት። ምናላቸው ስማቸው ውሳኔውን ሲቃወም "ሀሳቤን በማንም ተፅእኖ አልገድብም:: ምንም ቢመጣ ምን ሁሌም ከእውነት ጋር እቆማለሁ:: በማንነቴም እኮራለሁ:: የሚያጭበረብሩትን ደግሞ ምንጊዜም እጠየፋለሁ" በማለት በፌስቡክ ገጹ አጋርቷል። ይህንን አስተያየቱን የኢሳት ቦርድ አባል የሆነው ዶ/ር አዚዝ አይቀበለውም፤ "ውሳኔው በማንም ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የተደረገ አይደለም። የመንግስት ደጋፊ፣የመንግስት ተቃዋሚ የሚባል ሚድያ የለም። ኢሳት ለዲሞክራሲና ለኢትዮጵያዊነት ጠንክሮ የመስራት ራዕይ አለው።ከዚህ በኋላ እንደከዚህ ቀደሙ የተቆርቋሪነት ስራን ብቻ ሳይሆን እውነተኛ የሆነ የጋዜጠኝነት መርህ የሚተገብርበት ፕሮፌሽናል ሚዲያ እንዲሆን ነው የምንሰራው።" ብሏል። ይህን አመለካከቱን የሚጋሩም ሆነ ከሱ አመለካከት በተቃራኒ የቆሙ ሰዎች፣ በዚህ ቅነሳ ስራቸው ታጥፏል በማለት አስተያየቱን ውድቅ ያደርጉታል።

"ኢሳት የተለየ አስተያየትን ለማስተናገድ ምንጊዜም ዝግጁ ነው። ለውጡን ተከትሎ እንኳ በተለይ ላለፈው ስምንት ወር ያለምንም ከልካይ የተሰማቸውን ሲገልጹ ነበር። ሆኖም ኤዲቶሪያሉ አንድ ፕሮግራም ላይ በወሰደው እርምጃ ተመርኩዞ ብቻ ኢሳትን አፋኝ ተቋም አስመስሎ ማቅረብ ተገቢ አይደለም" በማለት ሌላኛው የኢሳት የቦርድ አባል ዶ/ር ሙሉዓለም የዶ/ር አዚዝን ሀሳብ ያጠናክሩታል።

ኤርምያስ ሰገሰ፣ ብሩክ ይባስ፣ ርዕዮት አለሙ፣ ተወልደ በየነ እና ግርማ ደገፋ ደግሞ ጓደኞቻቸው ከስራ መቀነሳቸውን ተቃውመው ኢሳትን ለቀው ወጥተው ethio 360 media የሚል በፌስቡክና ዩቱብ የሚተላለፍ ቲዩብ መስርተዋል። ቦርዱ ግን ኢሳትን ፕሮፌሽናል ሚዲያ በማድረጉ ጉዳይ በፍጹም ወደኋላ የሚመለስ እንዳልሆነ መመልከት እንችላለን።

## ኢሳትን ወደ ህዝብ ለመመለስ

ዶ/ር አዚዝ ቀጣዩን የኢሳት እጣ ፈንታ በ3 አካላት ላይ ያስቀምጣሉ፦ "ከኢሳት ሰራተኞች መካከል 5 ሰዎች፣ ከኢሳት ድጋፍ ሰጪዎች መካከልም እንዲሁ 5 ሰዎች፣ እንዲሁም ከኢሳት ቦርድ ውስጥ 5 ሰዎች ተወክለው 15 ሰዎች ተወካይነት በሚቋቋመው ኮሚቴ በቀጣይ ኢሳትን ወደ ህዝቡ በመመለስ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት በሚድያ ተቋምነት ተመዝግቦ ለህዝብ በየጊዜው ሪፖርቱን እየገለጸ በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ ፕሮፌሽናል ተቋም ይሆናል" የሚል አቅጣጫን ማስቀመጣቸውን ይገልጻሉ።

ኢሳትን ፈተና ውስጥ የከተተው ፕሮፌሽናል ሚዲያ የመሆን ጉዞው ይሳካለት ይሆን? በጊዜ ሂደት የምንመለከተውይሆናል። ከኢሳት ከለቀቁ ሰዎች ኤርሚያስ ለገሰን እንዲሁም ከማኔጅመንቱ ደግሞ ታማኝ በየነን አነጋግሬ የነሱን አስተያየት ለማካተት ያደረግሁት ጥረት አልተሳካም። ቦርዱ ላደረገልኝ ትብብር ግን ከልብ አመሰግናለሁ።

**ቸር እንሰንብት!**

# ይድረስ ለኢሳት ባልደረቦቹ፣ በመላው አለም ለምትገኙ የኢሳት ደጋፊዎችና ለነጻ ሚዲያ መኖር የምትታገሉ ዜጎች ሁሉ



በኢሳት ውስጥ የተከሰተውን ችግር አስመልክቶ በተለያዩ የመልክት ማድረሻ ዘዴዎች ምላሽ እንድሰጥ ጠይቃችሁኛል።

አሁን አዲስ አበባ የነበረኝን ስራ ጨርሼ በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ አሜሪካ ስለምመለስ ነገሮችን በተገቢው መልኩ እውነታውን ለህዝብ እንደማሳውቅ ቃል እገባላችኋለሁ።

ኢሳት ከለውጡ በኋላ ያጋጠመው ከባድ የገንዘብ ችግር እየተንከባለለ መጥቶ ከጊዚያዊ ችግሮች ጋር ተዳምሮ ሁኔታው ለአደባባይ እንዲበቃ አድርጎታል።

በሌላ በኩል በተፈጠረው ችግር ልባችሁ የተሰበረ ወገኖች በትግል ውስጥ መውደቅ መነሳት የነበረና የሚቀጥል ነውና አሁን ብንወድቅ አቧራውን አራግፈን ተነስተን ወደፊት እንራመዳለን እንጅ እንደወደቅን የምንቀር አይደለንምና ተስፋ አትቁረጡ።

ኢሳት ሞተ፡ ቀብሩ ተፈጸመ እያላችሁ ሟርት ቢጤ የተናገራችሁም የእናንተ ሟርት የበለጠ እንድንሰባሰብ እንድንነጋገር በር ይከፍትልናልና በሟርታችሁ ቀጥሉበት።

በተረፈ በተለያዩ ጎራ የተሰለፋችሁ የኢሳት ባልደረቦቼ ለኢሳት ማደግ ቀን ከሌሊት የደከማችሁ ደጋፊዎቻችን ያለምንም ክፍያ ለዘጠኝ አመት የሰራችሁ የቦርድ አባሎች የተነሳነው እዚህ ለመድረስ አይደለምና ከጊዚያዊ ስሜት በመውጣት ለመጨረሻ ጊዜ በአካል ተገናኝተን ለችግሩ መፍትሄ እንድንሰጥ እኔ እስከመጣ ድረስ የአደባባይ ምልልሶችንም ሆነ ምንም አይነት መግለጫ እንዳትሰጡ አብረን ታግለን ያሳለፍናቼውን የመከራ ቀኖች እያስታወስኩ በቅንነትና በትእግስት እንድትጠብቁኝ እለምናችኋለሁ።

ካሰብነው ሳንደርስ አንቆምም!

**ታማኝ በየነ**

## ሁለት ዓይነት አቀባበል



አንድ ግለሰብ አንድን ቦታ ለመጎብኘት አመ ለካከቱ፣ አዝማሚያውና ማንነቱ አይጠየቅም። እስካሁን የኢትዮጵያን ቅዱሳት ቦታዎችን የጎበኙት ሰዎች ግብረ ሰዶማውያን ይሁኑ አይሁኑ አናውቅም።

በተደራጀ መልኩ፣ የተለየ ዐቋሙን በይፋ እየገለጠና ለተለየ ዓላማውም ለመጠቀም እየተዘጋጀ ቅዱሳት መካናቱን ለመጎብኘት መምጣት ግን ጠብ ያለሽ በዳቦ ነው። ይህንን ቦታ ለመጎብኘት የጎብኚውና ያስጎብኚው ብቻ ሳይሆን የቦታው ታሪካዊ፣ ዜጋዊና መንፈሳዊ ባለቤትም ሊፈቅድ ይገባዋል።

ግብረ ሰዶማውያኑ እንመጣለን ካሉ በአካባቢያችን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን መከታተል አለብን። ቡድኖችን ፣ ምልክቶችን ፣ የፎቶና የቪዲዮ ቀረጻዎችን፣ ትርዒቶችንና ሌሎችንም መከታተል ይገባናል።

ኢትዮጵያ ግብረ ሰዶማዊነትን በባሕሏም፣ በእምነቷም፣ በሕጓም አትፈቅድም። ካልመጣን ሞተን እንገኛለን ካሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት ዓይነት የእንግዳ አቀባበል አለ በሏቸው።

**ዳንኤል ክብረት**

## በአክሱም ጦር ግንባር አንድ ተማሪ መገደሉን ስማን በጣም ያሳዝናል



ይሄ እንግዲህ ከደብረማርቆሱ የጦር ግንባር የቀጠለ ሌላ መርዶ መሆኑ ነው። (መቼም ግድያ የሚፈፀምባቸውን ዩንቨርስቲዎች ትምህርት ቤት ብሎ መጥራት እያሳፈረን ነው) ገዳይ ተማሪዎችም ተማሪዎች ሳይሆኑ ሽብርተኞች ናቸው። ይሄንን አይነት የሽብር ወንጀል መንግስት በጣም ትኩረት ሰጥቶ ሊያስቆም ይገባል። በዩንቨርስቲዎች ከዚህ በፊት ተቀጣጥሎ የነበረውን የዱላ አብዮት ጋብ በማለቱ አመስግንነን ሳንጠግብ አሁን ደግሞ በድንጋይ አብዮት መቀየሩ የቁልቁለታችን ማሳያ ነው።

አንዳንዴ መንግስት ይሄንን አይነት ግድያ እንዴት መቆጣጠር ይቻለዋል? ብዩ ሳስብ ይጨንቀኛል። ተማሪ ተብዬዎቹ ሰልጥነው መግደል በህግም ወንጀል በሞራልም ውድቀት መሆኑን ተረድተው በመነጋገር ካላመኑ እያንዳንዱ መኝታ ክፍልን በወታደር ለማስጠበቅ የሚያስችል አቅም ሃገሪቷ ከየት ታመጣለች?

ቢሆንም ግን ትምህርት ቤቶችን የጦር ቀጠና የሚያደርጉ ደነዝ ተማሪዎች ህግ ፊት ቀርበው ህዝብ በቴሌቪዥን ሆነ በሌላ መንገድ ሊያያቸው እና ግልፅ የሆነ አስተማሪ ፍርድ ሊሰጣቸው ይገባል።

ወንጀለኞችን እሹሩሩ ማለት ይቁም። በቁጥጥር ስር ውለው የፍርድ ሂደቱንም አሳዩን! አንዱ ማስተማሪያ መንገድ እርሱ ነው!

**አበበ ቶላ (አቤ ቶኪቻው)**

# ሰላም ለእናንተ ይሁን በድጋሚ - ለኢሳት ደጋፊዎችና ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሁሉ



ኢሳት ምስጢሩ ዛሬ ግልጽ ሆኖአል። ካልተቆጣጠርነው አፍርሰን ሌላ ሚዲያ እናቋቁማለን የሚል እንቅስቃሴ እንደነበር ጉዳዩን ለወራት የተከታተሉ የኢሳት ባልደረቦች ይህ ችግር ከተፈጠ በኋላ እየተናገሩ ነው። በቅርብ ቀናት ደግሞ ከኢሳትም ውጭ የሚገኙ የኢሳት ደጋፊ ኢትዮጵያውያን በርካታ መረጃዎች እያገኘን መሆኑ ለማሳወቅ እወዳለሁ። አዲስ ሚዲያ የመሰረቱ ግለሰቦች በሰላም ተለይተው ያሰቡትን ሚዲያ መመስረት ይችሉ ነበር፣ መልካም ምኞት ከመግለጽ አልፈን ልንተባበራቸው እንችል ነበር።

ነገር ግን ጉዳዩን በደምብ አስበውበት ፣ ተዘጋጅተው ሲያበቁ፣ የፓለቲካ እንዲመስል፣ "የብርሃኑ፣ የዐቢይ ስራ" ነው ብለው በነገሯቸው አክራሪ ብሄርተኛ ግለሰቦች አማካኝነት ዘመቻ ተከፈተ። በፖለቲካ ኣቋማቸው ሳቢያ እንደተገፉ ለማስመሰል ብዙ ውስጥ ውስጡን ዘመቻ እንዲደረግም ተደረገ። እኛንም በ"አጎብዳጅነት በቅጥረኝነት" በማስፈረጅ ሲያዘልፉና ሲያሰድቡን ከረሙ። ይህም የተደረገበት ዋና አላማ በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ በስልጣን ላይ የሚገኘውን ቡድን ከሚጠራጠረው ኢትዮጵያዊ ማሕበረሰብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ስለተፈለገ ነው።

ሰሞኑን የደረሱ መረጃዎች ምን ርቀት እንዳሰቡበት በርካታ ፍንጮች ሰጥተውናል። እነሱ እንደሚሉት "የመርህም፣ የሀቅም" መሰረት የለውም። እንነጋገር ከተባለ ሁሉንም አፍረጥርጠን በአደባባይ ለበርካታ ወራት በኢሳት የገንዘብ አቅምና በሌሎች አጀንዳዎች ዙሪያ የተደረጉትን የውይይት ቃለ ጉባኤዎች እንዲሁም ከሌሎች ሰነዶች ጋር አባሪ እያደረግን ለሕዝብ ማቅረብ አያቅትም። ሀቁ፣ እውነቱና፣ ቅንነቱ እኛ ጋር እንዳለ ሙሉ እምነት በራሳችን ላይ ስላለን።

ኢሳትን በሞኖፓል አንድ የፓለቲካ አመለካከት ካልያዘው ተብሎ ለማፍረስ መዶለት ፣ መንቀሳቀስ ሞራል የሌለው፣ በጣም አሳፋሪ ተግባር ነው። ወንጀልም ነው። በተለይ በምን ሁኔታ ወደ ኢሳት እንደመጡ በደምብ የምንተዋወቅ ሰዎች፣ የነሱንም ጥያቄና ስጋት ለመመለስ ምን ያህል ርቀት አንዳንዶቻችን የሄድን እንዳለን ውስጣቸው እያወቁ።

አርቲስት አክቲቪስት ታማኝ በየነ የኢሳት የዋሽንግተን ዲሲ ዳይሬክተር አሁን በፊሰ ቡክ ፖስት አድጎ በጠየቀው መሰረት በርካታ ዝርዝር ጉዳዮችን ወደ አደባባይ ከማውጣት እቆጠባለሁ።

1. ኢሳት እንደቀደሙት አመታት ከዚህ በፊት በነበረው መጠነ ሰፊ በጀት ሊቀጥል ፈጽሞ የማይችልበት ደረጃ መድረሱን ለበርካታ ወራት ለኢሳት አለምአቀፍ ባልደረቦች ሁሉ ሲገለጽ ነበር። ሁሉም የመፍትሄ ሃሳብ እንዲያመጡም የተደረጉ ስብሰባዎች ነበሩ። የዋሽንግተን ዲሲ ስቱዲዮን ተከትሎ በአውሮፓ በለንደንና በአምስተርዳም የሚገኙ ስቱዲዮችንም ላይ የበጀትና የቅነሳ እርምጃ በቀጣይነት ይወስዳል።

2. ለዋሽንግተን ዲሲ ኢሳት ባልደረቦች የተሰጠው አማራጭ የራሳቸውን ፕሮግራም በማስታወቂያና በስፖንሰሮች እንዲሸፍኑ ለመንቀሳቀስ እንደሚችሉ ከሁለት ወር በፊት ተገልጾአል ። እሁንም ቅነሳው የግድ ሲሆን የተላከው ደብዳቤ የሚገልጸው ይህንኑ ነው።

3. ኢሳት በርካታ ባለድርሻዎች አሉት ማለትም አሁን በስራ ላይ የሚገኘው ቦርድ ፣ አስተዳደር፣ ጋዜጠኞች፣ እንዲሁም በአለም ዙሪያ የሚገኙ የድጋፍ ኮሜቴዎች። እንደማንኛውም ተቋም አንድ ብቸኛ ባለድርሻ አካል (ለምሳሌ ከዚህ ወይንም ከዚያ ወገን ያሉ ጥቂት ጋዜጠኞች) ወይንም ሌላ ባለድርሻ በአንድ ጉዳይ ካልተስማማ እንደፈለገና እሱ በተመቸው መንገድ ብቻ ሊሆን አይችልም ።

የኢሳት የስራ አሰፈጻሚ ቦርድ አባል (በግል)

**ነአምን ዘለቀ**

# “ኢትዮጵያ ዛሬ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ፤ እንደ ኢድ ጀምዐ አንድነትን ትፈልጋለች!”

## ጠ/ሚ/ ር ዐቢይ አህመድ ለኢድ አል ፈጥር በዓል ያስተላለፉት መልዕክት

በረመዳን ወር መጨረሻ እና በሸዋል ወር የመጀመሪያ ቀን ላይ የሚውል በዓል ነው፤ ዒድ-አልፈጥር። በቅዱሱ የረመዳን ወር ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ፤ ሕዝበ ሙስሊሙ ራሱን ከመብልና መጠጥ ከማቀብ ባለፈ፣ በመልካም እና በጎ ተግባርም መትጋት ይጠበቅበታል።

በዚህ ረገድ፣ ነቢዩ መሐመድ (ሠለላ አለይሀ ወሠለም) “አስከፊ ንግግር እና ተግባራትን ያልተወ ሠው፣ ከምግብና ከመጠጥ መታቀቡ ብቻ በአላህ ዘንድ ከቁምነገር የሚገባ አይደለም” በማለት ትክክለኛውን መንገድ ማመላከታቸው፤ በሐዲስ ሰፍሮ ይገኛል።

በመሆኑም በጾምና ሰላቱ፣ በምስጋናና በልግስና ታጅቦ፤ ሠላሳ ቀናትን የሚዘልቀው የረመዳን ወር ነፍስን አለምላሚ፣ ሥጋን ግን ጎሳሚ፣ ከዚያም በተጨማሪ ፈታኞቹ ቀናት ካለፉ በኋላ የሚመጣው አዲስ ቀን፤ የኢድ በረከትን የታደለና ድካምንም የሚያስረሳ ተደርጎ ይወሰዳል።

በእምነታችን የተነሳ ትዕዛዛቱን ለመፈፀም በጽናት የምንቀበለው መከራ ሁሉ ከባድ ቢሆንም ማለፉ ግን አይቀሬ ነው። ያልፋል። አስተላለፉ ግን “ሲምር ያስተምር” እንደሚባለው ምሕረትም፣ ትምህርትም አግኝተንበት ነው። የረመዳን ወርና መሸኛው ኢድ አል ፈጥር በዓል ከመነሻ እስከመድረሻ ያለው ሥርዓት በእንዲህ ዓይነቱ በረከት የታደለ ነው።

የረመዳን ወር የጾምና የመታዘዝ፣ የድካ ምና የመፈተንም ወቅት ነው። ነገር ግን ከሚበላባቸውና ከሚጠጣባቸው ወሮች ይልቅ ቅዱሱ ወር ደግሞ እርሱ ነው። ይህ ወር በሥጋዊ ዕይታ ሲቃኝ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሁለት ጉዳዮችን በውስጡ አቅፎ የያዘ ይመስላል፤ ፈተናና በረከት።

ከጠዋት እስከ ማታ በጾም፣ በጸሎት እና በመልካም ምግባር ማሳለፍ ከባድ ፈተና ነው። በጾሙ ወቅት የሚገኘው ስጦታ ደግሞ በረከት ነው። አንድን ወቅት ጥሩ ጊዜና ጥሩ ወቅት ነው የምንለው እየተፈተንን የምናልፍበት፣ አልፈንም የምንሸለምበት ጊዜ ሲሆን ነው።

ከእጭና ኩብኩባ ተሸጋግሮ ወደ ቢራቢሮነት ለመለወጥ እንደሚታገል፤ “ኢትዮጵያ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ ተንፏቃቂ ነፍስ፣ ክንፍ አብቅሎ የሚበር ነፍስ” እስከመሆን ባለው ጉዞ፤ በትግልና ፈተና ማለፍ ግድ ነው። ትግሉ ግን በረከት ያለበት ፈተና ነው።

ሀገራችን አሁን ያለችበት ወቅት የፈተናና የበረከት ወቅት ነው። ከነባርና ወቅት አመጣሽ ፈተናዎቻችን ተላቅቀን ለማለፍ የምናደርገው ትግል በፈተና የተሞላ ነው። ከባድና የማይቻል ቢመስልም ማለፉ ግን አይቀርም። ይህ ተጋድሏችን ብዙ ነገሮችን ተምረን፣ በብዙ ጠባዮቻችንም የተነሣ እስከ ተስፋ መቁረጥ አስመርረውን የምናልፍበት ጉዞ ነው።

ክፉ የተባሉትን ነገሮች ሁሉ ፈጽመናቸው፣ ክፉ ከዚህ በኋላ አያሳየን የምንልበት የፈተና ወቅት ነው። ወቅቱ ግን የፈተና ብቻ አይደለም። የትናንቱን እንደ ወንፊት የምናጠራበት፣ ለነገውም ኃይል የምንሰንቅበት እንጂ።



የተጠራቀመውን ችግር ሁሉ ጠርገን የምንጨር ስበት የጽዳት ወቅት ነው። ለዚህም ነው ይህን የታሪክ ወቅት ፈታኙ ቅዱስ ጊዜ የምንለው። ቀዶ ጥገና ለሚያደርግ ሰው ያ ጊዜ ፈታኙ ጊዜ ነው። ሰመመኑም የሞት ታናሽ ወንድም ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ለሕመምተኛው በሽታውን ነቅሎ የሚገላገልበት የበረከቱ ጊዜም ነው። ለሀገራችንም እንዲሁ ነው። ይህ ወቅት ውዲቱ ሀገራችን በሁሉም መስክ ከባድ ሕክምና የምታደርግበት፤ ፈታኙ ጊዜዋ ነው። ግን የተሻለ መድኃኒትና ጤና የምታገኝበት፣ ቅዱሱ ጊዜዋም በዚህ ውስጥ ተፀንሶ ይወለዳል።

የዒድ በዓል ከመከበሩ በፊት ባሉት የመጨረሻ ቀናት፣ ሙስሊሞች “ዘካት አል ፈጥርን” ማውጣት አለባቸው። ዘካት ለድኾች የሚሰጥ እርዳታ ነው። ይህ ዘካት ከራስ በፊት ለሌላው ማሰብን የሚያስተምረን ሥርዓት ነው። ያውም በሁለንተናዊ ዐቅሙ ከኛ የሚያንሰውን ሰው በማሰብ። በሀብት፣ በዕውቀት ወይም በአካላዊ ዐቅም ሊሆን ይችላል። ይህንን ወገን ለማስቀደም ነው የ”ፈጥር ዘካ” ከዒድ በፊት መከናወን ያለበት።

የአንድ ማኅበረሰብ የሥልጣኔ መገለጫዎች ከሆኑት ነገሮች አንዱ በሁለንተናዊ መልኩ የተጎዱ የማኅበረሰቡን ክፍሎች ለመደገፍ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ መቻሉ ነው። አካል ጉዳተኞችን፣ ድኾችን፣ ዐቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ሕጻናትን፣ የተገለሉ ማኅበረሰቦችን ለመደገፍና ማኅበረሰባዊ ተሳትፏቸውን ከፍ ለማድረግ ምን እየሠራን ነው? ብለን መጠየቅ አለብን።

እንደ ዒድ ያለውን የደስታ ወቅት በሚገባ ለማጣጣም ከእኛ በፊት መቅደም ያለባቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች ማየት፣መጎብኘትና መደገፍ አለብን ። የእኛ አውራ ዶሮ ሌቱ ወደ ንጋት የመሸጋገሩን ብሥራት ከእኛ በተጨማሪ ለሌሎች መንደርተኞችም በ”አኩኩሉው” ማገልገል እንደሚችል ሁሉ፤ እኛም በእምነት አስተምህሮቱ መሠረት ዘካቱል ፍጡር በማውጣትና የተቸገሩ ወገኖቻችንን በመርዳት ድርብ ድርብርብ ተጠቃሚ እንሁን።

የዒድ በዓል በሚያስገርምና በሚያስደንቅ መልኩ የአዲሶች ኅብረትና አንድነት ግጥምጥ ሞሽ ነው ። ከአዲስ ጨረቃ መወለድ፣ ከአዲስ የንጋት ጀንበር መፈጠር፣ ከወርቃማ ጮራዎች መፈንጠቅ ጋር በመደመር፤ አዲስ ቀንና አዲስ ወር በአድማሱ ላይ በበዓል ድባብ ይዘረጋል።

የረመዳን ወር የጾም ፍቺ እና የዒድ አል-ፈጥር በዓል ሠላት በአብሮነት እና በአንድነት በጀምአ የሚሰገድበት ወቅትም ነው። በዓለም ዙሪያ ከቢሊየን በላይ በሚሆኑ ሙስሊሞች፣ በተመሳሳይ ቀን በሚከበረው የዒድ በዓል ጀምአና አብሮነት ከምንም ጊዜ በላይ ይፈለጋል፣ይፈቀዳል፤ ይወደዳል። በዓሉ ለብቻ አይከበርም።

በየአካባቢው ያለውን ሕዝብ ሁሉ ሊሰበስብ በሚችል ቦታ ላይ በጀምዐ፣ በመስገድ እና ተክቢራ በማሰማት ይከበራል። በመንደር፣ በሰፈርና በቤት ውስጥም ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት ከወዳጅ ዘመድ በተጨማሪ ከሌሎች የእምነት ተከታዮች ጋር በመሆን በሃላል ምግብና መጠጥ፣ በዓሉን በአንድነትና በጋራ በደስታ ያከብሩታል፣ ያሳልፉታል።

ኢትዮጵያውያን በሚከተሉት ሃይማኖት ሳቢያ በመካከላቸው የሚለያይና የሚያራርቅ ግንብ ከመገንባት ይልቅ፤ እምነታቸውን በየግላቸው በመያዝ፣ በአንድነትና አብሮነት ዘመናት የተሻገሩ ታላቅ ሕዝቦች ናቸው።

የኢትዮጵያን ችግሮች ለማለፍና ከደስታው ወቅት ለመድረስ፤ ጀምዐ ኅብረትና አንድነት ወሳኝ ነገር ነው። ኢትዮጵያ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ዛሬ እንደ ዒድ ጀምዐ ያለ አንድነትን ትፈልጋለች።

ከባድ አቀበት በመውጣት ላይ በመሆኗ ጉልበት እንድታመጣ፣ በአንድ ብቻ ሳይሆን በሁለቱም ሳንባዎቿ መተንፈስ ይኖርባታል። ለዒድ ሰላት ሕዝበ ሙስሊሙ አንድ ሆኖ “ማነህ? ማነሽ? ከየት ነህ? ከየት ነሽ?” ሳይል ለአንድ ዓላማ በጀምዐ እንደሚወጣው ሁሉ፤ ኢትዮጵያውያንም “ማነህ? ማነሽ? ከየት ነህ? ከየት ነሽ?” ሳንል ለአንድ ሀገራዊ ዓላማ አንድ ሆነን ከምንሰለፍበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ለሀገራዊ ጥሪ ሀገራዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል። በሀገራችን የሚከሠቱ ግጭቶች፣ መፈናቀሎች፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ሁሉ እንደ ረመዳን ጾም ቀናቸውን ቆጥረው ይጠናቀቃሉ። ያልፋሉ።

ኢትዮጵያም እንደ ዒድ የደስታ ዘመን ይጠብ ቃታል። ረመዳን ምንም እንኳን ፈታኝና ከባድ ወቅት ቢሆንም፤ ብዙ አረጋውያን ሙስሊሞች ግን ሲያልቅ ትዝታው በአዕምሯቸው ተስሎ ይቀራል። ጽናትና ቆራጥነታቸውን ያስታ ውሱበታልና። ይህ ሀገራችን እያለፈችበት ያለችው ወቅትም ያልቃል። ይሸኛል። በጽ ናትና በሀገራዊ ስሜት የጸኑ ዜጎቿ ሁሉ ወቅቱን በተጋድሎ ታሪክ፤ ትናንት በማለት የሚያስታውሱት ትዝታ ይሆናል።

በመጨረሻም ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በሙሉ ለ1440ኛው የዒድ አል - ፈጥር በዓል እንኳን አደረሳችሁ በማለት በዓሉ የደስታ፣ የሰላም፣ የይቅርታ ፣ የፍቅር እና የአንድነት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ።

***ኢድ ሙባረክ!***

# “የቅዱስ ሲኖዶሱ...

*ከገጽ 4 የዞረ*

የቅዱስ ሲኖዶሱን ውሳኔ፣ በጉጉት ሲጠባበቁ የቆዩትን የሀገረ ስብከቱን ምእመናን አላስደሰተም፤ በእጅጉ አስቆጥቷቸዋል፤ ብፁዕ አባ ያዕቆብ አይኹኑ እንጂ አንድ አድርጎ በፍቅር የሚመራንንና የሚባርከንን ሌላ አባት እንቀበላለን፤ በማለት በምልአተ ጉባኤው ላይ ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ የአኹኑን ጨምሮ ለኹለት ጊዜያት በተደረጉ ማጣራቶች፣ ሊቀ ጳጳሱ ለደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት አባት መኾን እንደማይችሉ እየተረጋገጠ፣ ለሦስተኛ ጊዜ ይጣራ ማለት ከቧልት እንደማይተናነስ አስረድተዋል፡፡

እንዲያውም ሊቀ ጳጳሱ፣ ለጊዜውም ቢኾን በእግድ መቆየታቸው፣ የበለጠ ሊጎዳቸው እንደሚችል ነው የተናገሩት፡፡ ጉልበተኞችን እየቀጠሩ የተቃወሟቸውን በማስደብደብ ካላቸው ልምድ አኳያ፣ በተለይ ስማቸው በሪፖርቱ ለተጠቀሱት ካህናትና ምእመናን ደኅንነት አስጊ እንደኾነ አስታውቀዋል፡፡ “ሲኖዶሱ ለሊቀ ጳጳሱ ቅሬታ የተጨነቀውን ያህል ለእኛም ሕይወት ማሰብ ነበረበት፤” ያሉት ምእመናኑ፣ ቢያንስ የሀገረ ስብከቱንና የአብያተ ክርስቲያናቱን ሒሳብ እንዳያንቀሳቅሱ ጨምሮ ሊያግዳቸው እንደሚገባ ጠይቀዋል፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ረቡዕ፣ ግንቦት 22 ቀን የቀትር በፊት ስብሰባው፣ አምስት የሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት ያቀረቡትን የድልድል ማስተካከያ ጥያቄ መርምሮ ውሳኔ አሳለፏል፡፡ በቋሚ ሲኖዶስ የሚታዩ አቤቱታዎችን አግባብነትና ሥልጣኑን በተመለከተም ደግሞ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

የአባቶች ዕርቀ ሰላምን ተከትሎ፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድነት ባካሔደው ያለፈው ጥቅምት ምልአተ ጉባኤው፣ አዲስ የአህጉረ ስብከት ድልድልና የ34 ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ምደባ ያደረገ ሲኾን፣ በካናዳ እና በሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስብከት የተመደቡ አምስት አባቶች፣ ይስተካከልልን የሚል ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

በዋሽንግተን ዲሲ የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል እና ደብረ ኀይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል፤ የፔንሲልቫኒያ ስቴት ሊቀ ጳጳስ እና በባልቲሞር የመካነ ሰላም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ፤ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የገዳማት መምሪያ የበላይ ሓላፊ እና በዋሽንግተን ሲያትል የመካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ፤ የዋሽንግተን ስቴትና አካባቢው ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብፁዕ አባ ማርቆስ እንዲሁም በካናዳ የኤድመንተን ከተማ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ናቸው፡፡የድልድል ማስተካከያ ጥያቄአቸው፥ ከአገልግሎት አፈጻጸም፣ የአገልግሎት ቅድምናን ከመጠበቅና ከጤና እክል ጋራ የተያያዘ እንደኾነ ተገልጿል፡፡

ኾኖም ቅዱስ ሲኖዶሱ፣ በኹለት ምደባዎች ብቻ መለስተኛ ለውጦች በማድረግ ብዙዎቹ ሊቃነ ጳጳሳት ባሉበት እንዲጸኑ ነው የወሰነው፡፡ ከሀገር ውስጥም ከውጭም በተውጣጡ ስድስት ብፁዓን አባቶች ጥምር ኮሚቴ በጥናት የተሠራ ድልደላ እንደኾነና መሠረታዊ ማስተካከያ እንደማያስፈልገው በውሳኔው አስታውቋል፡፡

በዚህም መሠረት፡- ብፁዕ አቡነ ሉቃስ፣ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የገዳማት መምሪያ የበላይ ሓላፊነቱን ብቻ እንዲይዙና ከዋሽንግተን ሲያትል መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂነት እንዲነሡ ወስኗል፡፡ የኤድመንተን ከተማ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ራብዕ፣ በከተማው የሚገኘውንና ቀድሞም መቀመጫቸው የኾነውን የመድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን እንደያዙ፣ ወደ መካከለኛው ካናዳና አካባቢው ሀገረ ስብከት እንዲዛወሩ ወስኗል፡፡ የኤድመንተን ከተማም እንደ ቀድሞው፣ የምዕራብ ካናዳና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በኾኑት ብፁዕ አቡነ ማትያስ ሥር(ብሪቲሽ ኮሎምቢያ፣ አልበርታና ኤድመንተን) እንዲኾን ወስኗል፡፡

የዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል እና የባልቲሞር መካነ ኢየሱስ የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ(የፔንሲልቫኒያ ስቴት ሊቀ ጳጳስ)፣ ባሉበት ሓላፊነት ይቀጥላሉ፡፡ ከአምስቱ ቅሬታ አቅራቢዎች ውስጥ፣ የአድባራት የበላይ ጠባቂ ለኾኑት ሦስቱ ብፁዓን አባቶች፣ ሓላፊነታቸውና ተግባራቸው በውሳኔው ቃለ ጉባኤው በዝርዝር ተገልጾ እንዲሰጣቸው ቅዱስ ሲኖዶሱ አዟል፡፡

በዕለቱ ከቀትር በኋላ የተመለከተውና ሙሉ ክፍለ ጊዜ የወሰደው፣ በአትላንታ የሰዓሊተ ምሕረት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ በሊቀ ጳጳሱ ብፁዕ አባ ያዕቆብ እና በምእመናን መካከል ስለተፈጠረው አለመግባባት የቀረበው ሪፖርት ነው፡፡ የአጣሪ ልኡኩ አባልና የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ባልደረባ ቀሲስ በላይ ጸጋዬ፣ ሪፖርቱን ለምልአተ ጉባኤው በንባብ አሰምተው መነጋገር የጀመረ ሲኾን፣ ሳይቋጭ በይደር ተነሥቷል፡፡

በ26 ገጾች የተጠናቀረው የልኡኩ ሪፖርት፣ ሊቀ ጳጳሱን በመቃወምና በመደገፍ የተሰለፉ ካህናትንና ምእመናንን አቤቱታዎች በንጽጽር በመጥቀስና የደረሰበትን ግንዛቤ በማስፈር ውሳኔውን ለቅዱስ ሲኖዶስ የሚተው ነው፡፡ ከሪፖርቱ ለመረዳት እንደተቻለው፣ ብዙኀኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናትና ምእመናን፣ ሊቀ ጳጳሱን የሚቃወሙና እንዲነሡላቸው የሚጠይቁ ናቸው፤ በአንጻሩ ለተቃውሞው ማኅበረ ቅዱሳንን በመክሠሥና ሊቀ ጳጳሱን ንጹሕ በማድረግ እንዲቆዩላቸው የሚፈልጉ ጥቂቶች ናቸው፡፡

በሊቀ ጳጳሱ ላይ ከተሰሙት አቤቱታዎች ከአንዱ በቀር ከፊሎቹን፣ በማስረጃም በትዝብትም ማረጋገጡን ልኡኩ በሪፖርቱ አስፍሯል፡፡ ሊቀ ጳጳሱ፥ የዘረኝነትና ወገንተኝነት ችግር እንደተስዋለባቸው፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም ስሕተት መፈጸማቸውንና “ተኣምረ ማርያም አይነበብም” ለተባለውም ማረጋገጫ ማግኘቱን ገልጿል፡፡ በቅዱስ ሲኖዶስ ከተወገዘውና ዛሬም በኑፋቄው ከቀጠለው ልዑለ ቃል አካሉና ሌላው መናፍቅ መላኩ ባወቀ፣ ከቴክሳሱ ትዝታው ሳሙኤል እና ከመሳሰሉት ግብረ አበሮቻቸው ጋራ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከባድ ፈተና ላይ እንደጣሏት ነው ብዙኀኑ ያስረዱት፡፡

አሁን፣ ካህናቱና ምእመናኑ በኹለት ወገን ተከፍለው እየተፈራረቁ ቤተ ክርስቲያኑን እየተገለገሉበት ይገኛሉ፡፡ ይህም በተለይ ለተተኪው ትውልድ ከሚያስተላልፈው መጥፎ ጫና አንጻር መቀጠል እንደሌለበት ነው የሚታመነው፡፡ ሊቀ ጳጳሱ ከሚበዛው ወገን ጋራ ከፈጠሩት አለመግባባትና በማጣራቱ ከተረጋገጠባቸው ድክመት አንጻር፣ ምልአተ ጉባኤው ለቤተ ክርስቲያን ያደላ ውሳኔ ሊያሳልፍ ይገባል፡፡ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት አምርቶ ከ700ሺሕ ዶላር በላይ ወጪ ከኾነ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ከቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ ባለፈው ግንቦት 10 ቀን 2011 ዓ.ም(May 18, 2019) ፍርድ ቤቱ ምዕመኑን ስብስቦ ድምፅ አስጥቶአል፡፡ ቁጥሩ ከ400 በላይ የኾነው ምእመን፣ ሊቀ ጳጳሱ ብፁዕ አባ ያዕቆብ፣ ከአትላንታና አካባቢዋ እንዲነሡ ድምፅ ሲሰጥ፣ አይነሡ በማለት ድጋፍ የሰጧቸው 100 እንኳን አይሞሉም፡፡

ምእመናኑ፣ ይህን ተጨባጭ ኹኔታ በመጥቀስ ለቅዱስ ሲኖዶስ ባስተላለፉት መልእክት የሚከተለውን ተማኅፅኖ አቅርበዋል፡- “አቡነ ያዕቆብ ወደዱም ጠሉም፣ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከዚህ አካባቢ መባረራቸው አይቀርም፡፡ በመኾኑም ቅዱስ ሲኖዶስ በዚሁ ምልዓተ ጉባኤው፣ በአንድ ጳጳስ ምክንያት ከ4,000 ቁጥር በላይ ያለው በ7 ስቴት ውስጥ የሚገኘውና የቤተ ክርስቲያኒቱን ዕዳ እየከፈለ ያለው ምስኪን ምእመን እንዳይበተን ያስብለት፤ አቡነ ያዕቆብ ተነሥተው በምትካቸው የምእመናን አንድነትና ፍቅር የሚገደው መልካም እረኛ የሚኾነን እንዲመድብልን፣ የተበተነው እንዲሰበሰብ፣ የተከፋፈለው አንድ እንዲኾን እንዲያደርግልን አጥብቀን እንማፀናለን፤” ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ ቅዱስ ሲኖዶሱ፣ ከእኒህ ኹለት አጀንዳዎች ቀደም ሲል ሲያከራክር በቆየውና በተ.ቁ.(6) በሰፈረው፣ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጉዳይ ትእዛዝ የሰጠው፣ ከትላንት በስቲያ ከቀትር በኋላ ነበር፡፡ የካቴድራሉ ሦስት የአስተዳደር ሓላፊዎች ከቦታው ተነሥተው እንዲዛወሩ ቋሚ ሲኖዶስ ያስተላለፈውንና ከፓትርያርኩ ጋራ አለመግባባት ያስከተለውን ውሳኔ አሰጣጥ መርምሯል፡፡ በአስተዳዳሪው፣ ዋና ጸሐፊው እና ሒሳብ ሹሚ ላይ አቤቱታ ያቀረቡት ሠራተኞችና ምእመናን ጥያቄ፥ የቅርስ ማውደሙ፣ ምዝበራው፣ አድልዎው፣ የአሠራር ጥሰቱ ይጣራልን፤ የሚል እንደኾነና ሓላፊዎቹ እንዲዛወሩ መወሰን ጊዜውን ያልጠበቀ በመኾኑ ማጣራቱ መቅደም እንደነበረበት አስገንዝቧል፡፡በመኾኑም፣ በኹሉም ወገን የቀረቡ አቤቱታዎችን አጣርቶ በአስቸኳይ የሚያቀርብ፣ ከሀገረ ስብከትና ከጠቅላይ ጽ/ቤት የተውጣጣ ሦስት አባላት ያሉት ልኡክ ሠይሟል፡፡ ከ ዚሁ ጋራ በተያያዘ ምልአተ ጉባኤው፣ በአጀንዳ ተ.ቁ.(7) በሰፈረው፣ የቋሚ ሲኖዶስ ሥልጣንና የሥራ አፈጻጸም ከተነጋገረ በኋላ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

ስብሰባ ላይ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ረቡዕ ዕለት በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ግብረሰዶማውያን ቡድን ሊያደርግ ያሰበውን ጉብኝት በእጅጉ አውግዟል፡፡ ሃይማኖተኛ ሕዝብ ባለበት አገር እንዲህ ዓይነቱ ነገር መታሰቡ ድፈረት መሆኑን በመግለጫው ያሳወቀው ቅዱስ ሲኖዶስ መንግስት በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ መልዕክት አስተላልፏል፡፡

***ምንጭ- ሐራ ተዋህዶ***



# ሪታ ፓንክረስ፤- ከነቤተሰባቸው ዕድሜያቸውን ለኢትዮጵያ የሰጡ ባለውለታ

ሪታ ፓንክረስ የተወለዱት ሮማንያ ውስጥ በ1927እ.ኤ.አ ነው፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ወደ ብሪታንያ በ1938እ.ኤ.አ አምርተዋል፡፡ በካምብሪጅ ፐርሴ የሴቶች ትምህርት ቤት ከተማሩ በኃላ፣ በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ ደግሞ ዘመናዊ ቋንቋን (ፈረንሳይኛ እና ሩሲያኛ) አጥንተው በ1948 የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ በካታነም ሃውስ ፕረስ ቤተ መፃሕፍት ውስጥ ስራቸውን ሀ ብለው የጀመሩ ሲሆን፤ በ1956 ዓ.ም በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ሪቻርድንና እናታቸውን ሲልቪያ ፓንክረስትን እስከሚያገኙም ድረስ በዚያው ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት( ወመዘክር) ስራ በመጀመር፣ ከቤተመጻሕፍት ስራ ጋር ተያያዥ የሆነውን የቤተመጻሕፍት ትምህርት አብረው መውሰድ ጀመሩ፡፡ በ1957እ.ኤ.አ ከሁለት አመት የአዲስ አበባ ቆይታ በኃላ ከሪቻርድ ፓንክረስ ጋር ትዳር የመሰረቱ ሲሆን፤ በትዳራቸው ሁለት ልጆችን፡- አሉላ አንድሪውን እና ሄለን ሲልቪያን ወልደዋል፡፡ ልጆቻቸውም እንደ ወላጆቻቸው ሁለት ሁለት ልጆችን ወልደዋል፡፡ ሪታ ፓንክረስ ከዓመታት በኂላ በወሊድ ምክንያት ያቋረጡትን ትምህርት የቀጠሉ ሲሆን፣ በ1964እ.ኤ.አ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

ከዚህ ጊዜ በኂላ ሪታ አብዛኛው የስራቸው ህይወት በቤተመጻሕፍት የትምህርት ዘርፍ ውስጥ ነበር፡፡ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ላይብረሪያን በመሆን ለአስር ዓመት በኃላፊነት አገልግለዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሳሉ በ1976እ.ኤ.አ የነበረው የመንግስት ለውጥ ለልጆቻቸው የትምህርት ምቹ ባለመሆኑ ወደ ለንደን ተመልሰዋል፡፡ በዚያም ሳሉ በለንደን ከተማ ፖሊቴክኒክ የቤተመፃሕፍት አገልግሎት ኃላፊ ሆነው ተሹመው፣ ከባለቤታቸው ከሪቻርድ ጋር ወደ አዲስ አበባ እስኪመለሱ ድረስ ለአስራ አንድ ዓመት አገልግለዋል፡፡

> ...በተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የነበሩት ሲልቪያ የኢትዮጵያን በጣሊያን መወረርም በመቃወም ኢትዮጵያን ወግነው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር በመተባበር ድምፅ ሆነዋል፡፡ ከዚያም በኋላ በኢትዮጵያ ባህል እና ጥበብ የተመሰጡት ሲልቪያ የተለያዩ ተግባራትን በኢትዮጵያ አካሂደዋል...

ሪታ እና ሪቻርድ ፓንክረስ ልጆቻቸውን በብሪታንያ ውስጥ ባለ ዩኒቨርሲቲ ትተው ወደ ኢትዮጵያ በ1987እ.ኤ.አ ተመለሱ፡፡ በተለያዩ ትምህርታዊ መጻሕፍት እና የዩኒቨርሲቲ ምርምር ስራዎች ላይ የእርምት እና ለቤተ መጻሕፍትም የአማካሪነት ሚና በመጫወት ቆይተዋል፡፡ ለበጎ አድራጎት ስራዎች ከቀድሞው በተለየና በበለጠ አቅም ራሳቸውን በመስጠት አገልግለዋል፡፡

በሲልቪያ (የሪቻርድ ፓንክረስ እናት) ላይ እንዲሁም ከሴትነት ጋር በተያዩዙ ጉዳዮች ላይ የሰሯቸው ለህትመት የበቁ ስራዎቻቸው ውስጥ፣ ሲልቪያ ፓንክረስ በሴቶች የመብት ጥያቄ ይዘት ላይ የነበራቸው እይታዎችን የሚመለከቱ፣ በስንዱ ገብሩ ለሴቶች አርአያነት ላይ የተመረኮዘ፣ የሴቶች ኃይል በኢትዮጵያ ታሪክና ጅብድ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ የተረሱ ሴቶች እና የመሳሰሉትን ስራዎች አበርክተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ለመማረክ ቅድምያውን የሚወስዱት ሲልቪያ ፓንክረስት፣ በሃገራቸው እውቅ የሴቶች መብት ተሟጋች እና የአንደኛውን የአለም ጦርነት ተቃዋሚም ነበሩ፡፡ በተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የነበሩት ሲልቪያ የኢትዮጵያን በጣሊያን መወረርም በመቃወም ኢትዮጵያን ወግነው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር በመተባበር ድምፅ ሆነዋል፡፡ ከዚያም በኂላ በኢትዮጵያ ባህል እና ጥበብ የተመሰጡት ሲልቪያ የተለያዩ ተግባራትን በኢትዮጵያ አካሂደዋል፡፡ በንጉሡ በቀረበላቸውም ጥሪ መሰረት ከልጃቸው ከሪቻርድ ጋር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡

በ2017 በ89ዓመታቸው ያረፉት ሪቻርድ ፓንክረስ በአክሱም ተመልሶ የቆመውን "የአክሱምን ሃውልት" የማስመለስ ስራ ላይ የመሪነቱን ሃላፊነት በመውሰድ፣ ትልቅ ድርሻን ተወጥተዋል፡፡ የምጣኔ ሃብት ባለሙያ የሆኑት እኚህ ታላቅ ሰው የኢትዮጵያን ታሪክ ከምጣኔ ሃብት እውቀታቸው ጋር በማጣመር በርካታ ስራዎችን አበርክተዋል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ መሬትና ሀገረመንግስት፣ የከተሞቿ ታሪክ፣ የረሃብ እና ተያያዥ ጉዳዮች፣ በተለያዩ ጊዜያት የነገሡ ነገሥታት ታሪክ፣ በአጠቃላይ ፓለቲካ እና ማህበራዊ እውነቶች ላይ መጻሕፍትን ጥናቶችን እና የሌሎችን ሰዎችም ስራዎች በማረም ሰርተዋል፡፡

በ92 ዓመታቸው ህልፈታቸው ሐሙስ 22 ግንቦት 2019ዓ.ም የተሰማው ሪታ ፓንክረስ በቅድስት ሥላሴ መንበረ ፀባኦት ቤተክርስቲያን ማክሰኞ ግንቦት 27 ስርዓተ ቀብራቸው የተለያዩ የዲፕሎማሲ ማህበረሰብ እና የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት ተፈፅሟል፡፡ ሪታ ፓንክረስና ባለቤታቸው ሪቻርድ ፓንክረስ ከነቤተሰቦቻቸው ለኢትዮጵያ ባላቸው ፍቅር እና ቀናኢ ትጋት የክብር ዜግነትን ያገኙ ሲሆን፤ ዕድሜያቸውንም የኢትዮጵያን ታሪክ በማጥናትና ስለ ኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያ በመቆም አሳልፈዋል፡፡

ሁለቱ የትዳር አጋሮች ሲልቪያ ፓንክረስ እና ሪቻርድ ፓንክረስ በጋራ በመሆን ‹‹ ኢትዮጵያን ረሚኒሰንስ›› የተሰኘ ከፊሉ ግለ ማስታወሻ እና ከፊሉ ታሪክ የሆነ በርካታ አባባሎችን እና የተለያዩ ገላጭ ምስሎችን የያዘ መፅሃፍ ለህትመት አብቅተዋል፡፡